
መልካም የዐድዋ በዓል !



አንደኛ ዓመታችንን ስንዘክር
የሚታሰቡን ተግዳሮቶች

“ባይ ባይ
ኢህአዴግ? ! ”



ልዩ
እትም

ግዮን
መጽሔት
1ኛ ዓመት


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ
ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 46 የካቲት 2011 ዓ.ም ዋጋ 14.99




“የወያኔ ትርክት አፄ ምኒልክን
ከፍ ስለማያደርግ
ዐድዋ ተረስቷል”

(ረ/ፕ/ር አበባው አያሌው)



## የአጼ ምኒልክ
## ነገር

## የእምዬ ሚኒልክ
## የሃይማኖት ፖሊሲና
## የአድዋ ድል

ዘሪሁን ሙላቱ (ዶ/ር)

ግዮን ፩
ቅጽ 1 ቁጥር 46 ቅዳሜ የካቲት 23 2011 ዓ.ም

1ኛ ዓመት





አንደኛ ዓመታችንን ስንዘክር የሚታሰቡን ተግዳሮቶች 2

7 «ከስንት ዓመት በኋላ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እየሸተተን ነው ! »
በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

8 የአጼ ምኒልክ ነገር
ኄኖክ ገለታው

9 የእምዬ ሚኒልክ
የሃይማኖት ፖሊሲና የአድዋ ድል
ዘሪሁን ሙላቱ (ዶ/ር)

11 አድዋ <<የአፍሪካውያን የድል ቀን>>
አፄ ምኒልክ <<የአፍሪካ የነፃነት አባት>>
ሁሴን ከድር

12 የአፄ ምንሊክና የእቴጌ ጣይቱ
የማዘዣ ሰፈር በወሳኟ ዕለት
ብሩክ መኮንን



3
“የወያኔ ትርክት አፄ ምንልክን ከፍ ስለማያደርግ አደዋ ተረስቷል”
(ረ/ፕ/ር አበባው አያሌው)

“ባይ ባይ ኢህአዴግ? ! ” 15
መላክ ቢ.


ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
የካቲት 30
ይጠብቁን!




ቁጥር 45 ዕትም

# አንደኛ ዓመታችንን ስንዘክር የሚታሰቡን ተግዳሮቶች

የኢትዮጵያዊነት መለያ ኅብርን የበለጠ የሚያደምቁ ነባራዊ ሁኔታዎችን ለማጠናከር፣ መጽሔታችን በኢዲቶሪያል ፓሊሲ ደረጃ አቋም ይዞበት ላለፉት ዐሥራ ሁለት ወራት በብርቱ ሲሠራበት ቆይቷል፡፡በዚህም ቀላል የማይባሉ የግዮን ታማኝ ቤተሰቦችን ማፍራት ተችሏል፡፡የመጽሔታችን ውልደት በታላቁ ዐድዋ ድል በዓል ማግሥት መሆኑ ደግሞ ታሪካዊ ግጥምጥሞሹን የተለየ አድርጎት አልፏል፡፡

ግዮን መጽሔታችን የሰነቀውን ሀገራዊ ራዕይ በገቢር ለመግለጽ ገና በአፍላ ዘመኑ የገጠሙት ተግዳሮቶች እንዲህ በዋዛ ተዘርዝረው የሚያልቁ አይደሉም ፡፡የነጻው ፕሬስ አሁንም ፀሐይ አልወጣለትም፡፡በዚህ ድፍን አንድ ዓመት ውስጥ ያለፍናቸው መሰናክሎች፣አስቀድመን በእቅድ ካሰቀመጥናቸው ተጠባቂ ፈተናዎችም ጭምር በእጅጉ የከበዱ ነበሩ፡፡በርግጥ ጠፍ በሆነ ምህዳር ላይ ሌጣችንን ለመፋፋት መሞከር ተራራን በገመድ እንደመጎተት ይቆጠራል፡ ፡በነጻው ፕሬስ ሰማይ ላይ ያጠላው ጽልመት ሁሉንም የዘርፉ አካላት በእኩል ደረጃ ሰለባ ስለሚያደርግ የእኛም ተጎጂነት ተጠባቂ ኹነት ነው፡፡ምንም እንኳን ከሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ዘመን ጋር ሲነጻጸር ለዘርፉ ብሥራት የሆኑ አዎንታዊ እርምጃዎች መወሰዳቸው የአደባባይ እውነት ቢሆንም እርምጃው የነጻው ፕሬስ በዴሞክራሲያዊ ግንባታ ሒደት ውስጥ ከሚጫወተው ሚና አኳያ ሲመዘን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡

የመንግሥት ቢሮክራሲያዊ ማነቆዎች የነጻው ፕሬስ የሕትመት ውጤቶችን ዕለት በዕለት እያቀጨጨ ይገኛል፡፡ በቋፍ ያሉት በጣት የሚቆጠሩ የሕትመት ውጤቶች እንደ ገና ጀምበር ብቅ ብለው ፈጥነው ሲከስሙ እያስተዋልን ነው፡፡ ለዘርፉ መንግሥት ያሳየው ዳተኝነትን ተከትሎ ይህ ሁኔታ ቢከሰት ሊደንቀን አይገባም፡፡በፕሬሱ ላይ የተጫነውን የግብር ሥርዓት መለስ ብሎ በመከለስ፤እንዲሁም ለሕትመት የሚስፈልጉትን ግብአቶች በአነሰተኛ ዋጋ የሚቀርቡበትን አሠራር በማመቻቸት የተጎዳውን ዘርፍ ቢያንስ መደጎም ይቻል ነበር፡፡

የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ዳግም በሀገራችን ለይ እንዳይነግሥ ልጓም በማበጀቱ ረገድ ከፍተኛ ሚና ከሚጫወቱት ተዋኒያን መካከል ይህ ዘርፍ ዋንኛው እንደሆነ ይታወቃል፡፡አዲሱ የለውጥ አስተዳደር እውነተኛ የሕዝብ የልብ ትርታን የሚያዳምጥ፤ከሕዝብ ጋር እጅ እና ጓንት የሆነ፤ለመላው የሀገራችን ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም የሚተጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመትከል ከምር የተነሳ ከሆነ ይህ ዘርፍ እንዲፋፋ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ መጀመር አለበት፡፡የፕሬሱን ክፍል እንደ ትርፍ ወይም ቅንጦት መቁጠር ኋላ ማጣፊያው ከሚያጥር ውስብስብ ሀገራዊ ችግር ውስጥ ሊከትን ይችላል፡፡

መጽሔታችን ግዮን በእነዚህ ተገዳዳሪ ነባራዊ ሁኔታዎች ታጅቦ ያለፉትን ዐሥራ ሁለት ወራት ለሕትመት ብርሃን በመብቃቱ የአንባቢያንን ተአማኒነትን ቢያተርፍም በፋይናንስ ቁመናው ረገድ ግን ጎልውናውን አደጋ ላይ በሚጥል በአንጉል ጎደና መንጎድ ከጀመረ ሰንብቷል፡፡ያነገብነው ታላቅ ራዕይ ፈተና የገጠመው በፋይናንስ ረገድ ብቻ አይደለም፡፡ ካለፈው ሥርዓት የተወረሱ ማነቆዎች አሁንም ዱካቸው አልጠፋም፡፡በዚህኛውም በለውጥ አስተዳደር ዘንድም በገሀድ እያስተዋልናቸው ነው፡፡ የፕሬስ ሴክሬታሪያት ቢሮ አንዱን አቃፊ ሌላው ገፊ የሆነ አሰራርን ይፋ በማድረጉ የተነሳ የእኛም መጽሔት ልክ እንደሌሎች የዘርፉ የሕትመት ውጤቶች ሰለባ ሊሆን ችሏል፡፡ይህን መሰሉ አግላይ መመሪያ ዘርፉን ሳይወለድ እንደሚያጨነግፈው ከማንም የተሰወረ ሐቅ አይደለም፡፡በመናኛ ቢሮክራሲያዊ ማነቆዎች ምክንያት አፈር እንዳይለብስ በስስት የምናየውን ራዕያችንኅ ጎልውናውን ጠብቆ እንዲቀጥል ትግላችንን እንቀጥላለን፡፡

በአሁን ሰዐት አየሩን በሞላው የጎሳ ፓለቲካን ተገን አድርገው በሁለት እግራቸው ለመቆም የሚውተረተሩ በነጻው ፕሬስ ስም የሚንቀሳቀሱ የሕትመት ውጤቶች እንዳሉ ቢታወቅም እኛ ግን የጨበጥነውን የኢትዮጵያዊነት እርፍን አንለቅም፡፡የሙያ ክብራችንን በጎጥ ወይም በጎሳ ለተሸነሸነው የፓለቲካ አውድ አሸንቀጥር ጥለን ዝቅ ብለን ለመንበርከክ መቼም ቢሆን አንፈቀድም፡፡ያነግበነው ራእይ ትልቅ ነው፡፡ኢትዮጵያዊነት፡፡ሁሉን አቃፊ፣ሁሉን ሰብሳቢ፡፡ኢትዮጵያዊነትን ይዞ የተሸነፈ በታሪክ ፊት ተከስቶ አያውቅም፡፡ዐድዋም ያስተማረን ይሄን ነው፡፡ትግላችን ይቀጥላል፡፡

## ግዮን መጽሔት

ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና
ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር
በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ
ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
ሔማስ ታፈረ

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(ከአሜሪካ)

**አምደኞች**
ወንድሙ ነጋሽ(ኢ/ር ከለንደን)
ተረፈ ወርቁ
ሁሴን ከድር
ኄኖክ ገለታው

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ባሳዝነው ወንድምነህ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ

በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች
በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

ዜና

## የኢራን እስላማዊ አብዮት 40ኛ ዓመት በግጥም ተከበረ

የኢራን እስላማዊ አብዮት የተካሄደበትን 40ኛ ዓመት ምክያት በማድረግ የኢራን ኤንባሲ የባህል ክፍል የግጥም ምሽት የካቲት 11/2011በዋቢ ሸበሌ ሆቴል አካሂዷል በፕሮግራሙ ላይ የታላላቅ ኢራናዊያን ገጣሚዎችሰራ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ቀርቧል እንዲሁም ሞውላና የተባለው የኢራን ባህላዊ ሙዚቃ ቡድን ስራውን አቅርቧል፡፡



በፕሮግራሙ ላይ በኢትዩጲያ የኢራን ኤንባሲ የባህል ካውንስለር ጨምሮ የተለያዩ እንግዶች ተሳትፍዋል በኢራን ኤምባሲ የባህል ካውንስለር የሆኑት ዶክተር ስይድ ሃሠን ሃይደሪ ይህ አሁን እያከበርን የምንገኘው 40ኛው የአብዩት ክብረበአል የአምስት ሺሕ ዘመን ባለታሪኳ፣የፋርሶች ስልጣኔ መሠረትዋ፣ የነዳጅ ዘይት ሐብታሚቱ ሐገር ከ2500 ዘመን በላይ የፀናባትንየአምባገነኑን ንጉሳዊ አገዛዝ በይፋ አስወግዳ እስላማዊት ሪፐብሊክ የሆነችበት ነው ብለዋል፡፡

ከዚህ ቀደምም የግጥም ምሽቶች እና ሴሚናሮችን እንዳዘጋጁ ገልፀው በተጨማሪም ኢትዮጵያዊያን የኢራንን ባህል እና ቋንቋ እንዲያውቁ የፐርሺያ ቋንቋ እና ኢራኖሎጂ የተባልውን በኢራን ታሪክ ፣ ስነፅሁፍ፣ ጥንታዊ ስልጣኔዎች ላይ የሚያተኩር ትምህርት ለማንኛውም ፍላጎቱ ላለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በነፃ እየተሠጠ መሆኑን በቅርቡም በአለም ላይ ተፍላጊነቱ እየጨመረ የመጣውን የኢራንን ምንጣፍ አሰራር ለኢትዮጵያዊያን ሴቶች ለማስተማር በዝግጅት ላይ እንደሆኑና ኮርሱም በነፃ እንደሚሰጥ ገልፀዋል፡፡

በነዚህ 40 አመታት ውስጥ ሀገሪቱ ከፍተኛ እድገት አስመዝግባለች ያሉት ዶክተር ስይድ ሃሠን ሃይደሪ

በተለይም በጤናና መድሀኒት መስክ በናኖ ቴክኖሎጂ ኤሮስፔስ በኒውክለር ቴክኖሎጂ ትምህርት ስፖርት አስገራሚ እድገትና መሻሻሎችን እንዳስመዘገበች ገልፀዋል፡፡



# “የወያኔ ትርክት አፄ ምንልክን ከፍ ስለማያደርግ አደዋ ተረስቷል”

## (ረ/ፕ/ር አበባው አያሌው)

*ረ/ፕ/ር አበባው አያሌው በታሪክ ባለሙያነታቸውና በሚሰጧቸው ጥልቅ ሀገራዊና ፖለቲካዊ ትንታኔዎች በብዙዎች ዘንድ ይታወቃሉ፡፡ የካቲት23 ቀን የሚከበረውን 123ኛው የአደዋ ድል ክብረ በዓልን፣ እንዲሁም በድሉ ታሪካዊ ሁነቶችና አደዋ ከዚህ ትውልድ ጋር ያለውን ቁርኝት አስመልክቶ የግዮን ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅ እንዲህ ባለ መልኩ አነጋግሯቸዋል፡፡*

**ግዮን፡- የአድዋ ጦርነት አነሳሱ እንዴት ነበር? ፍፃሜውስ ምን ዓይነት ይዘት ነበረው? ከሚለው ቃለ መጠይቃችንን ብንጀምርስ?**

ረ/ፕ/ር አበባው፡- አድዋ ረዥምም ታሪክ ያለው ነው፤ እንዲሁ ዝም ብሎ በድንገት ተነስቶ ወደ ጦርነት የተገባበት ዘመቻም አይደለም፡፡ ሌሎችን ጦርነቶች ስንወስድ ከመሀዲስት (ሱዳኖች) ጋር፣ ከግብፅ ጋር አፄ ዮሐንስ የተዋጉት ወራሪዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ፣ መሬት ይይዛሉ፤ መስፋፋት ስለሆነ ምክንያታቸው፤ ለዛ ደግሞ አፀፋ ምላሽ መስጠት ይመጣል፡፡ የአድዋ ጦርነትን ግን ካየነው የሚነሳው አስቀድሞ ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የቅኝ ግዛት ፍሎጎት ማሳደሯ ነው፡፡ ያም ወደ ኋላ ስንሄድ ከ1860 ዓ.ም አካባቢ ይጀምራል፡፡

ያኔ ጣልያን የተዋሀደችና አንድ ትልቅ ሀገር አልነበረችም፤ ግን አንድ የጣልያን የመርከብ ኩባንያ አሰብ ላይ የተወሰነ መሬ ከረሂታስ ሱልጣን ይገዛል፡፡ ያቺን ቦታ ለድንጋይ ከሰል ማከማቻ አድርገው ሊጠቀሙበት ነበር ፍላጎታቸው፤ ውሎ ሳያድር ግን ወደ መሀል ሀገር ሸዋ፣ አንኮበር በተለይም ‹‹ልጥ ማረፊያ›› የምትባል ቦታ፣ የኢጣልያ የጆግራፊ ማህበር እዛ ድረስ መጥቶ ሌሎች ሀገሮች እንደሚያደርጉት ሁሉ ለቅኝ ግዛት አሰሳዎችንና ጥናት ያደርግ ጀመር፡፡

**ግዮን፡- የጥናቱ መሰረት ምንድን ነው?**

ረ/ፕ/ር አበባው፡- ህዝቡ ምን ዓይነት ባህል አለው? መሬቱ ምን ዓይነት አዝርት ያበቅላል? የሚሉና እያንዳንዱ ቅኝ ገዢ ሀገር ለቅኝ



ግዛት የተጠቀመባቸው መረጃዎችን መጀመሪያ አሊዚያንቲኖሪ የተሰኘው ሲሰበስብ ነበር፣ በኋላ ደግሞ ፔትሮአንቶኖኒን፡፡ ይህ ሰው መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ዲፕሎማት ሆኖ ሳይሆን የኢጣልያ የጆኦግራፊ ሶሳይቲ መሪ ሆኖ ነው፡፡ ከጊዜ በኋላ የጣልያን ተወካይ ቆንስል ሆኖ ማገልገል ጀመረ፡፡ ይሄ እንግዲህ በዝግጅት ደረጃ የነበረ ነው፡፡

ቀጥሎ የአድዋውን ስምምነት ኢትዮጵያ ተዋዋለች፡፡ ይሄ የአድዋ ወይም የሄዌት ውል የሚባለው በ1874 ዓ.ም የተደረገ ነው፣ በኢትዮጵያና በግብፅ መሀከል፡፡ ግብፅ ራሷን አልወከለችም ነበር፤ ምክንያቱም በወቅቱ ግብፅ ላይ የእንግሊዝ የበላይነት ነበር፡፡ እናም እንግሊዞች ሪድአድሚራል ዊሊያም ሄዊት የሚባል የባህር ኃይል መኮንን ላኩ፣ አፄ ዮሐንስ በኢትዮጵያ በኩል ሆነው ስምምነት ተዋዋሉ፡፡

ግብፅ ይዛቸው ከነበሩት የኢትዮጵያ ግዛቶች ከቦጎ እስከ ሀልሃል እና ሌሎችም የምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢ ለቅቀው እንዲወጡ፣ አንደኛው የአድዋ ውል አንቀፅ ደግሞ የሚያወራው ስለ ምፅዋ ጉዳይ ነው፡፡ ምፅዋን ቱርኮች ለረዥም ጊዜ ይዘዋት ነበር፤ እነሱ ከለቀቁ በኋላ የቱርኮች ተወካይ የሆኑ ናኢብ የሚባሉት ምፅዋን በመያዝ ለቱርክ ይገብሩ ነበር፡፡ ለኢትዮጵያውያን አልፎ አልፎ ነበር የሚገብሩት፡፡ በእነሱ ላይ ግብፆች መጥተው ምፅዋን ያዙ፡፡

በስምምነቱ መሰረት ግብፅ ምፅዋን ስትለቅ ምፅዋ ምን ትሁን? ለሚለው እንግሊዞች “ለግዜው ነፃ ሆኖ የኢትዮጵያ መንግስት ሲፈልግ እቃ ሲፈልግ የጦር መሳሪያ ሊያስገባበት ይችላል አይከለከልም፡፡ ግን በበላይነት ለጊዜው ምፅዋን የሚቆጣጠሩት እንግሊዞች ይሁኑ የሚል ሀሳብ አቅርበው በእዛ ተስማሙ፡፡ በነገራችን ላይ እንግሊዝ ኢትዮጵያ ላይ የቅኝ ግዛት ፍላጎት የላትም፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ▶

ፈረንሳይ ወደ ኢትዮጵያ እንድትገባ አትፈልግም፡፡ ግብፅን ይዘው ስለነበረና ቀጣይ ህልማቸው ሱዳንን መያዝ ስለሆነ እነዚህን ሀገሮች የሚይዙ ከሆነ የኢትዮጵያን አካባቢዎች በተለይ የአባይን ተፋሰስ ማንም ተቀናቃኝ የሆነ አውሮፓዊ ኃይል እንዳይገባበት ይፈልጉ ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳት ፈረንሳይ እንዳትገባ ስለሚፈልጉ ጣልያንን አምጥተው ሰተት አድርገው አስገቡ፡፡ ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ግብግብ የጀመረው፡፡

**ግዮን፡- የኢጣልያ ወታደሮች በቀጥታ ምፅዋ ነበር የገቡት?**

ሬ/ፕ/ር አበባው፡- ትክክል፡፡ የኢጣልያ ወታደሮች ምፅዋ ከገቡ በኋላ ወደ ደጋው መስፋፋት ነው የፈለጉት፡፡ ወደ ዶጋሊ፣ ወደ ሰሀዬ፣ ወደ ሀልሀልና ሀብሀብ መጓዝ ፈልገው ነበረ፡፡ ያ ዶጋሊም ላይ ተቋጨ፤ ሰሀጢ ላይ አፄ ዮሐንስ ጦር አስተባብሮ ዘምቶባቸው ነበር አልተቻለም፡፡ ምክንያቱም ሀዲስቶች በምዕራብ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ መሀል ኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ስላሳሰበው አፄ ዩሐንስ ተመልሶ መጣ፡፡ እንግዲህ በዛች "መተማ" በዘመተበት አጋጣሚም ጦርም ስላልነበረ ከሰሃጢ ተነስተው አስመራ ገቡና ደጋውን አካባቢ ያዙ፡፡

እንግዲህ አፄ የሐንስ ከሞቱ በኋላ ትልቁና ወደ አድዋ ጦርነት የመራው ምክንያት ይጀምራል፡፡ እርሱ ደግሞ የውጫሌ ውል ነው፡፡ አፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ንጉሰ ነገስት ምኒልክ ራሳቸውን የኢትዮጵያ ገዢ አደረጉ፤ ያኔ ከጣልያን ጋር የግድ ስምምነት ማድረግ ነበረባቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ የውጫሌን ውል ተስማሙ፡፡ ያ ውል አንደኛ ወደ ሀያ የሚሆኑ የንግድ ግንኙነቶችን፣ ድንበርን፣ መረዳዳትን ሌሎች ነገሮችን ይዘረዝራል፤ ግን ዋና የሚባሉት ሁለቱ አንቀፆች ናቸው፤ አንቀፅ ሶስትና አንቀፅ አስራ ሰባት፡፡

**ግዮን፡- እስኪ እነዚህን ወሳኝ አንቀፆች በዝርዝር ያስቃኙን?**

ሬ/ፕ/ር አበባው፡- አንቀፅ ሶስት ደግሞ በጣልያን ስር የሚሆነውን ሀገር ሰሜን ኢትዮጵያ ላይ ይደነግጋል፡፡ ከምፅዋ በታች ገልፍ ኦፍ ዙላ የሚባል አንድ ቦታ አለ፤ እዛ "አፋሲ" የምትባል አንድ መንደር አለች፣ ከእዛ ተነስቶ በሀይላይ አድርጎ፣ በሰገናይቱ አድርጎ አስመራ፤ ከአስመራ አንደገና ወደ ምዕራብ በአዲዮሮንስና በአዲፈንስ በኩል የሚሄድ መስመር ላይ፣ ከዛ ወሰን ወደላይ ያለው ቦታ የጣልያን ግዛት ይሆናል፡፡እንደዛም ሆኖ ከዛ ወሰን ወደ ሰሜን ያሉት ደብረቢዛን ገዳም፣ ትልቅ ገዳም ነው "እርሱ የኢትዮጵያ ቦታ ሆኖ ይቆያል፡፡ ግን የኢትዮጵያ መንግስት የጦር መሳሪያ ሊያከማችበት አይችልም" ይላል ውሉ፡፡ ይህቺ ብቻ ናት የተሰጠችው፡፡

ሁለተኛው አንቀፅ አስራ ሰባት በደንብ ታቅዶበት የተሰራ ነው፤ "ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ሀገር መንግስትና ከሌላ መንግስታት ጋር መገናኘት ብትፈልግ ግዴታ በጣልያን ስር መሆን አለበት" ይላል የጣልያንኛው ቅጂ፡፡ የአማርኛው ቅጂ ደግሞ "ከፈለገች ጣልያንን መጠቀም ትችላለች" ይላል፡፡ ያኛው ግዴታ ያስቀምጣል፣ ይሄኛው ደግሞ እንደ አማራጭ በፍላጎቷ ይወሰናል ይላል፡፡ ይሄ አውሮፓውያን ሌላ አፍሪካ ሀገር ላይ ያደርጉት የነበረ፣ አስፈርመው ይሄዱና "ያንን ሀገር የመጠበቅ የመንከባከብና እንደ ሞግዚት ሆኖ የማሳደግ መብት አለኝ" በሚል መንገድ ነው ወደ ቅኝ ግዛት የሚሄዱት፡፡

ጣልያኖች ይሄ ነበር ሀሳባቸው፣ እሱም አመት ሳይሞላ ተነቃ፡፡ በጊዜው በአስተርጓሚዎችም በኩል ትልቅ ችግር ነበር፡፡ ያን ያህል የታሰበበትና የተዘጋጀበት አልነበረም፡፡ ወደ አድዋ የመራው ጭቅጭቅ ልክ ከውጫሌ ስምምነት ጭቅጭቅ ይጀምራል፡፡ መቋጫው አንቀፅ "የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት፣ መንግስትም ይሁን የኢጣልያ መንግስት ከነዚህ ከተስማሙባቸው ሀያ አንቀፆች፣ አንደኛውን ማሻሻል ቢገባው ከአምስት ዓመት በፊት ማሳወቅ አለበት" ይላል፡፡ እየተጨቃጨቁ አምስት ዓመት ሊሞላ ሆነ፤ ስለዚህ ምኒልክ ውሉን ሲሰርዙት "ከዛሬ ጀምሮ ይሄን ውል አላውቀውም፣ ተሰርዟል በኢትዮጵያ በኩል" ሲባል ሁለቱም ሀገሮች ለጦር መሰናዳት ጀመሩ፡፡

**ግዮን፡-ጣልያኖች ውሉ በኢትዮጵያ በኩል ሲፈርስ በቀጥታ ወደ ጦርነት ከመግባት በዲፕሎማሲ መንገድ ለማግባባት ሙከራ አድርገዋል?**

ሬ/ፕ/ር አበባው፡- በተለያዩ መልዕክተኞቻቸው ተደጋጋሚ ሙከራ አድርገዋል፡፡ የውጫሌው ውል አምስት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳይኖር ማድረግ ነበር፡፡ እቅዳቸው በጣይቱ አማካይነት አልተሳካም፡፡ በዛ ጭቅጭቅ መሀል አንቶኖሊ የተባለው የጣልያን ተወካይ አንድ ቀን ግራዝማች ዮሴፍን ተሳደበ፤ "እርሱ ነው ይሄን ሁሉ ነገር የሚያመጣው፣ ምንም የማያውቅ መሀይም ነው" በሚል ተቆጣ፡፡ ጣይቱ እዛ ላይ አልቻለችም፤ እርሷ እንደ ምኒልክ ተለሳላሽ አይደለችም፡፡ "ቢያጠፋስ የፈለገውን ቢያደርግ አሽከራችንን እኛ ነን እንጂ የምንቀጣ፣ አንተን ገሳጭ ያደረገህ ማነው? እንድንትሳደብስ የፈቀልህ ማነው?" በሚል በጣም ተናገራቸው፡፡ እርሱም በዚህ ተናዶ እጅ ሳይነሳ እየደነፋ ሄደ፡፡ ጣይቱ ትያትር ላይ ብዙ ጊዜ የምትነሳው ይህቺ ነገር ነች፡፡ "ጦርነት የምትፈልግ ከሆነ ሳይመሽብህ ሂድ፣ እንደውም ሳምንት አድርገው፡፡ እኔ ሴት ነኝ፣ ግን ጦርነት አልፈራም" በሚል ምኒልክ እልፍኝ የተናገረችው፡፡

በሌላ በኩል ጣልያኖች ሰሜን ኢትዮጵያ ላይ ያሉትን መኳንንቶች ማባበልና ወደ ጣልያን እንዲገቡ ማድረግ ካልሆነም ለምኒልክ ተባባሪ እንዳይሆኑ ማድረግ ነበር፡፡ በዚህም አይናቸው ያረፈው ራስ መንገሻ ፣ ራስ ስብሐትና ደጃዝማች ሐጎስ ላይ ሆነ፡፡ ይሄ አካሄድ መጀመሪያ የተሳካ መስሎ ነበር፤ ምክንያቱም ራስ መንገሻ ትንሽ የፖለቲካ ቁርሾ ስለነበረባቸው፣ የመረብ ስምምነት የሚለውን ከጣልያን ጋር ተዋዋሉ፡፡ በዚህ ውል አፄ ምኒልክ ራስ መንገሻን ሊወጋ ከመጣ ጣልያኖች ሊረዱ፣ ምኒልክ ጣልያኖች ላይ ጦርነት ካወጀም ራስ መንገሻ ጣልያንን ሊያግዙ ተስማምተው ለሶስት ዓመት ያህል ቆዩ፡፡ በኋላ ግን ራስ መንገሻ ሁኔታውን አይተው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ታማኝነታቸውን ገለፁ፡፡ የትግራይ ግዛታቸውም ተሰጣቸው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ እነ ራስ ስብሐትና ደጃች ሀጎስ ደግሞ አኮረፉና ወደ ጣልያን ሄዱ፡፡ እነሱም የመቀሌው ከበባ ካለቀና ጣልያን ወደ አዲግራት ከሄደ በኋላ ከድተው ነው የገቡት፡፡ አድዋ ሲዋጉ ነው የዋሉት፣ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር፡፡ ስለዚህ ይሄኛውም ዕቅድ ለጣልያኖች አልተሳካም ማለት ነው፡፡

ሌላው ጣልያኖች የሰሩት ማጭበርበር በውጫሌ ውል መሰረት የጣልያን መንግስት ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ብዙ ሺህ ሊሬ ነበር፡፡ ያንን ለመፈፀም ራስ መኮንን በዓመቱ ወደ ጣልያን ሄደው እዛ ሲደርሱ ትልቅ አቀባበል ነው የተደረገላቸው፡፡ ያ ሁሉ ግርግር አስተርጓሚ በሌለበት ታዛቢ፣ በሌለበት አንድ ውል አስፈርሟቸው፡፡ ያ ምን ይላል? የውጫሌ ውልን አንቀፅ ሶስት የሚጥስና "የሁለቱ ሀገር ወሰን እግር በረገጠ ይሆናል" የሚል ነው፡፡ እግር በረገጠ ማለት መጥተው መቀሌ ከደረሱና ጣልያኖች ወታደራቸውና ሌሎች ነገራቸው እዛ ካለ ያ ሁሉ እነርሱ የረገጡት መሬት የጣልያን ግዛት ሊሆን ነው፡፡ ውሉ ከተፈረመም በኋላ አስመራን ለቀው ወደ ታች ወደ ደቀ መኃሪ ሰነአፌ ድረስ መጡ፡፡ ይሄ ሁሉ እንግዲህ ለአድዋ ጦርነት መቀስቀስ መንስኤ ሆኗል፡፡

**ግዮን፡- ወደ ጦርነት ሲገቡ የነበረው ዝግጅትስ ምን ዓይነት ነበር?**

ሬ/ፕ/ር አበባው፡- ሁለቱም ወደ ጦርነት ለመግባት መሰናዳት ሲጀምሩ በኢትዮጵያ በኩል የነበረው የጥይት ችግር ነው፡፡ እንደገና ደግሞ የስንቅ ችግር፡፡ ጣልያኖች እንደሚያሸንፉ ተማምነው ወደ ጦርነቱ የገቡ፤ ትልቁ ስትራቴጂያቸው ወደ መሀል ስንጥቆ በመግባት የንጉሰ ነገስቱን ሠራዊት መምታት፣ ከዛ በኋላ ጦሩ ስለሚበተን ኢትዮጵያ በእጃችን ትሆለች የሚል ነው፡፡ በመሳሪያቸው፣ በዘመናዊ ጦራቸው ተማምነዋል፤ ግን በብዙ ነገር ጥሩ ስትራቴጂ አልነበረም፡፡

በኢትዮጵያ በኩል ምኒልክ የክተት አዋጅ አወጁ፤ ከመስከረም እስከ ህዳር ዘመቻ ላይ ነበረ፡፡ ከጥቅምት አጋማሽ እስከ የካቲት የፈጀ ረዥም ዘመቻ ነው ያካሄደው፡፡ መጀመሪያ እስከ ህዳር አጋማሽ ባለው ጊዜ ጦሩ ሲጓዝ ነው የቆየው፡፡ ወረኢሉ የሚከተው ወረኢሉ ከተተ፣ ጨጨሆ የከተተውም ጨጨሆ ከተተ፣ ከጎጃምና ከበጌምድር የመጣው ሁለቱ "ወፍላ" ላይ (አሁን ከረም ከፍ ብሎ አሸንዳ የሚባለው አካባቢ) ተገናኙ፡፡ እዛ ላይ ምኒልክ የሰራዊታቸውን ሰልፍ ገመገሙ፤ ብዛቱን ዝግጅቱን በደንብ መገምገም ቻሉ፡፡

ከዛ በኋላ ለሁለት ተከፈለና እነ ራስ መኮንን፣ ፊታውራሪ ገበየሁ፣ ንጉስ ተ/ሐይማኖት፣ ራስ ሚካኤል ያሉበት ጦር ህዳር 29 አምባላጌ ላይ በሜዠር ቶዞሎሚ የሚመራውን የጣልያን ጦር ገጠመው፡፡ አምባላጌ ላይ ጣልያን ጥሩ ምሽግ ስለያዘ፣ ፊት ለፊት በሜዳው ይመጣሉ ብሎ ጠብቆ ነበር፣ ሠራዊቱ ግን ተከፍሎ ከጎንና ከጎን ነው ያጠቃው፡፡ ጥሩ ውጤትም ተገኝቶበታል፡፡ በዚህ የተነሳ ጣልያን ከአምባላጌ ሸሽቶ መቀሌ ገባ፤ መቀሌ የኢትዮጵያ ጦር እስኪመጣ እንዳየሱስ አካባቢ ትልቅ ምሽግ ሠርተው ነበር፡፡ አሁን ፎርቶ ዲጋሊያኖ ተብሎ የሚጠራውን ቦታ በሻለቃ ጋሊና አማካይነት ሠርተው ለሶስት ሳምንት መመሸግ ችለው ነበር፡፡

በመጨረሻ ውሃው ሲያዝባቸው ማለቃቸው ስለሆነ የግድ መደራደር ነበረባቸውና ተደራደሩ፤ ከመቀሌ ለቀው አዲግራት ገቡ፡፡ ምኒልክ ከመቀሌ ወደ አድዋ አቅጣጫ ሄዶ የሃ ሰፈረ፡፡ ምኒልክ እንደገና ከየሃ ወደ አድዋ መጣ፡፡ ምክንያቱም የቦታው አቀማመጥ በቀላሉ በመድፍ ሊመታ የማይቻል ስለሆነ፡፡ ጣልያኖች ደግሞ ከአዲግራት ወጥተው ኢንጢጮ በመምጣት ሰፈሩ፡፡ ይህ ቦታ ብዙም ተራራማ ስላልሆነ እዛ የምኒልክ ጦር መጥቶ እንዲገጥማቸው ነበር ፍላጎታቸው፡፡ አንድ ሶስት ጊዜ የሰራዊት ሰልፍ በማሳየት የጦርነት ሙከራ አድርገው ነበር፡፡ በኢትዮጵያ በኩል እነ ራስ አሉላን፣ ራስ መንገሻን የመሰሉ ብልህ ሰዎች ስለነበሩ ሜዳ ላይ የሚደረግ ጦርነት ኢትዮጵያን እንደሚጎዳትና ጣልያን መድፍና መትረየሱን እንደ ልብ ለመጠቀም ዕድል ስለሚፈጥርለት ትንኮሳው በዝምታ ታልፏል፡፡

ስለዚህ የነበረው አማራጭ ሌሊት ተጉዘው ጠዋት ላይ ድንገተኛ ተኩስ መክፍትና ማጥቃት ስንዝሮ የኢትዮጵያን ጦር መደምሰስ ነው፡፡ በዛ ጦራቸውን ለአምስት በመክፈል አንደኛውን ደጀን፣ አራቱን አጥቂ አድርገው በአራት ጄነራል ▶



የሚመራ ጦር ላኩ፡፡ ለነገሩ ከመጀመሪያው ጦርነቱን እንደሚሸነፉ ያውቁታል፤ አንደኛ በጦር ጄነራሎቹ መሀል መግባባት አልነበረም፡፡ እነ አሪሞንዲ "ተጨማሪ ሠራዊት ይኑረን ወይም ሌላ ስትራቴጂ እንጠቀም" ሲሉ እነ አልቤርቶና ባራቴሪ ደግሞ "ምንም አያቅተንም፣ አፈር ድሜ እናብላው" በሚል ከፍተኛ ጭቅጭቅ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ከሮም የተላከው መልዕክት "አዋረዳችሁን፣ ቶሎ ብላችሁ እንድታሸንፉ" የሚል ነው ያለውን ነባራዊ ሁኔታ እነሱ አልተገነዘቡትም፡፡

ጠዋት አንድ ላይ ያጠቃሉ የተባሉት በአቅጣጫ ስህተትና በተለያዩ ምክንያቶች ተበታትነው አልቤርቶኒ ቢደርስም ጦሩ ሸለቆ ውስጥ ተወቅቶ እሱም ተማረከ፡፡ ከዛ በኋላ አሪሞንዲ ረፈድ ሲል መጣ፤ እሱም በተመሳሳይ ሁኔታ ተመታ፡፡ የዳቦር ቢና ጦር ጭራሽ አቅጣጫ ስቶ ስለሄደ እርሱ ተመልሶ እስኪመጣ ያኛው ተደምስሷል፡፡ አድዋ የአንድ ቀን ጦርነት ነው አልን እንጂ ሰባት ውጊያ የተደረገበት ነው፡፡ ትልቅ ጦርነት የምንለውም ለእዛ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የካቲት 23 ቀን ሙሉ ለሙሉ በኢትዮጵያውያን ድል ተቋጨ፡፡

**ግዮን፡- የመጨረሻው የድል ብስራት የተሰማው በስንት ሰዓት ነበር?**

ሪ/ፕ/ር አበባው፡-ጦርነቱ እስከ ምሽት ተካሂዷል፡፡ የካቲት 23 ንጋት ላይ ነው የጀመረው፣ አድዋ ምቹ ነው፣ ጠላት በየት በኩል እንደሚመጣብህ በግልፅ ያሳያል፡፡ የተቋጨው ደግሞ ደጀን የነበረው ባራቴሪ ጦር አስግብቶ እንደገና ባራቴሪ መሸሸ ሲጀምር፣ እርሱም ተመትቶ የሸሸው ሸሽቶ፣ ንጉሰ ነገስቱ እስኪመለሱ ድረስ ወደ ምሽት አንድ ሰዓት ሁለት ሰዓት ሆኗል፡፡ ንጉሰ ነገስቱ ሲመለሱ ያው ድል ተደርጓል ማለት ነው፤ ያኔ ጣልያን እያጠቃ ሳይሆን ነፍሱን ለማዳን እየሸሸ ነበር፡፡የራስ አሉላ ጦር ባራቴሪን እይዛለሁ ብሎ የተወሰነ ሞክሯል፡፡ ግን ድካምም ጨለማም ይዘውት ያሰበው አልሆነም፡፡

**ግዮን፡- አድዋ ላይ የካቲት 23 ቀን ድል ከተመታ በኋላ ምኒልክ በአመቱ ያንን ታሪካዊ ቀን በምን መልክ አከበሩት?**

ሪ/ፕ/ር አበባው፡- ኢትዮጵያና ምኒልክ ቢያሸንፉም በጣም ያስደነገጠ ጦርነት ነው፡፡ አንደኛ በዚህ ውጊያ ለምኒልክ ቅርብ የነበሩ ታላላቅ ሰዎች ሞተውበታል፡፡ እነ ፊታውራሪ ገበየሁን የመሰሉ፡፡ የአምባላጌውን ጦርነት እኔ ሳልመጣ አስጀመርክ በሚል ትንሽ ቁርሾ ነበራቸው፣ በጥቂቱ እንደ እስረኛም አድርገው ይዘውት ነበረ፡፡ አድዋ ላይ ግን እየሸለለ ገብቶ ነው የሞተው፡፡ እነዚህ ታላላቅ ሰዎች መሞታቸው ትልቅ ሀዘን ነው፤ ሁለተኛ በኢትዮጵያ በኩል ከአስር ሺጎ በላይ ሰው ነው የሞተው፡፡ በዚህ የተነሳ ሳምንቱን ሙሉ ሀዘን ነው የተደረገው፡፡ አስከሬን በየጢሻው እየተፈለገ ሲቀበር ነበር፡፡ አፄ ምኒልክ ድል ቢያደርጉም አሸነፍን በሚል ያን ያህል ሆታ አልነበረም፡፡

ምኒልክ በድል አድራጊነት፣ በሆታና በእልልታ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው የተቀበለው ተመልሶ አዲስ አበባ ሲገባ ነው፡፡ ከሞተው ሰው፣ ከቆሰለው ሰው አንፃር ብዙ ደስታ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ጣልያን መትረየስ ለመተኮስ የተወሰነች ደቂቃ ካገኘ ረፍርፎ ነው የሚጥለው፡፡ ግን ደግነቱ ጦርነቱ የቅልቅል ነው፣ ጦሩ ቀደም ስለሚቀላቀል ኢትዮጵያዊያን ሰይፍና ጎራዴ ስላላቸው ከጣልያኖች የተሻለ ያጠቃሉ፡፡ በምኒልክ ጊዜ አድዋን በተመለከተ ትልቁ ክበረበዓል በሰባተኛው ዓመት የተካሄደው ነው፡፡

ያኔ ትልቅ የሰራዊት ግብዓት ተደርጎ፣ ዝግጅት ተካሂዶ፣ በጦርነቱ ለሞቱት ተስካር ወጥቷል፡፡ ከዛ ውጪ በየዓመቱ በፀሎት ይታሰብ ነበር፡፡

በዘውዲቱም ጊዜ በየዓመቱ ይከበር ነበር፡፡ በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጊዜ የአድዋ አከባበር እየተሻሻለ መጣ፤ በዘመናዊ መልክ የማርሽ ባንድ አለ፣ አሁን አራት ኪሎ ሀውልቱ ያለበት ቦታ የአድዋ መታሰቢያ ሐውልት ቆሞ ነበር፡፡ ከ1929 ዓ.ም በፊት፡፡ በ1929 ነው ያንን ሐውልት ጣልያኖቹ ያፈረሱት፡፡ ከጣልያን ነፃነት በኋላ የድል ሐውልት ተብሎ መሰየም ሲጀመር ነው የአድዋ ድል ጊዮርጊስ መከበር የተጀመረው፡፡ ከዛ በፊት ግን ጊዮርጊስ ፀሎት ነበር ብቻ የሚካሄደው፡፡

**ግዮን፡- በደርግ ጊዜስ የነበረው የአድዋ አከባበር ምን ይመስላል?**

ሪ/ፕ/ር አበባው፡- ደርግ እንግዲህ አድዋን ትልቅ ስፍራ ሰጥቶት ነበር ያከብር የነበረው፡፡ ምክንያቱም አንድነትን፣ ነፃነትን የሚያቀነቅን መንግስት ነበረ፣ ከሁሉም በላይ ማለት ነው፡፡ ደርግ ከጅምሩ የትኞቹ ብሔራዊ በአላት ይከበሩ? በሚል ጭቅጭቅ ሲይዝ እንኳን የአድዋን ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ አላስገባም፡፡ በምንም ተዐምር አድዋ ቅኝ ገዥን የመታንበት፣ የአፍሪካ ድል እየተባለ መሞካሸቱም የተጀመረው ያኔ ነው፡፡

እንደገና ለበአሉ የሚሰጠው ክብርም ትልቅ ነው፡፡ ታላላቅ የመንግስት ባለስልጣናት ናቸው በቦታው የሚገኙት፡፡ የአርበኞች ማህበርም ቢሆን ያን ያህል አልተዳከመም በደርግ ጊዜ፡፡ ያ በመሆኑ ሞቅ ደመቅ ያለ ግርማ ሞገስ ያለው በዓል ነበር፡፡ ህዝቡም አከባበሩና በአሉ የምር መሆኑን ስለሚያውቅ ይወጣል፡፡

**ግዮን፡- በኢህአዴግ ዘመን ከ1984 አንስቶ የነበረው አከባበርስ እንዴት ይገለፃል?**

/ፕ/ር፡- በኢሕአዴግ ጊዜ በጣም ብዙ ችግር አለ፡፡ የመጀመሪያው ነገርና በአሉን ያደበዘዘው ነገር ኢሕአዴግ ከታሪክ ጋር የተጣላ መንግስት ስለሆነ ነው፡፡ ከታሪክ ጋር መጣላት ብቻ አይደለም በሀገሪቷ በታሪክ ትልልቅ ቦታ ያላቸውን ሰዎች የውዝግብና የንትርክ መነሻ አደረጋቸው፡፡ ምኒልክ ሀገሪቷን የታደገ፣ አሁን ያለችውን ዘመናዊት ኢትዮጵያ የገነባ ሳይሆን፣ አንድ ጊዜ "ራሱ ቅኝ ገዥ ነው፣ አንድ ጊዜ በደቡብና በኦሮሞዎች ላይ ያደረሰው ግፍ" እያሉ ማውራት ጀመሩ፡፡ ሁለተኛ ከምኒልክ በፊት የነበረው ዮሐንስን እንኳን አያከብሩም እነዚህ ሰዎች፡፡ ትልቅ መሪ ነው፣ ከጣልያን ጋር የተዋጋ ነው፣ ከመሀዲስት (ሱዳን) ጋር ተዋግቶ የተሰዋ ትልቅ ብሔራዊ ሰማዕት ነው፡፡ እሱን እንኳን አንስተውት አያውቁም፡፡

ይሄን ውዝግብና ክርክር በምኒልክ ዙሪያ ሲያነሱ እንዲደበዝዝ ፈልገው ነበር፡፡ ሁለተኛ ለይስሙላ ማክበር፣ ዝምብሎ ምክንያቱም እንዳይተውት ትልቅ የፖለቲካ ኪሳራ ነው፣ እንዳያከብሩት ደግሞ አይፈልጉትም፡፡ የእነሱ (የወያኔዎች) የታሪክ ትርክት ምኒልክን ከፍ የሚያደርግ አይደለም፡፡ ሀገር ሀገር የሚል ሳይሆን ብሔር ብሔር የሚል ነውና ለአደዋ ደንታ አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ ያደረጉት ምንድን ነው ለይስሙላ አዲስ አበባ ላይ ማክበር፡፡ መቶኛ ዓመቱ ሲከበር ትልቅ ህዝባዊ ሰልፍ ሁሉ ተጠርቶ ነበር፤ መስቀል አደባባይ፡፡ አንድ አውሮፕላንም እንዲሁ ዥውዥው ብሎ ነበር መሰለኝ፤ ተማሪ ነበርኩ እኔ፡፡ በጊዜው ፕሬዝዳንቱ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ነበሩ እርሳቸው መጥተው ስለ አድዋ ታላቅነት ንግግር አደረጉ፡፡ መደምደሚያቸው ግን "ምኒልክ ነፃነት ቢያስጠብቁም በደቡብ ኢትዮጵያና በኦሮሞ ህዝቦች ላይ ያደረሱት ጭፍጨፋ ብዙ ነው" ብለው ሲናገሩ ጭራሽ ሰው ሁሉ ጮኸ፡፡ እንዴት በመቶ ዓመት ታሪካዊ ክብረ በዓል ላይ እንደዚህ ይባላል?

ሁለተኛ አከባበሩ ሲታይ አዲስ አበባ ለይስሙላ፣ አድዋ ላይ ደግሞ በደንብ ለማክበር ሞክረው ነበር፡፡ ሁሉ ነገር የሚጀምረው ከመቶኛ ዓመቱ ነው፤ አንደኛ ምኒልክ አይደለም ያሸነፈው ጦርነቱን፤ አድዋ ሲባል ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተባብሮ ያመጣው ድል ነው፡፡ ተዋጊው ብቻ አይደለም ስንቅ አቀባዩ፣ ሴቶቹ፣ በቅሎ ራሱ አስተዋፅኦ አድርጋለች ተ/ሐዋርያት እንደሚነግሩን፤ "የበቅሎና የሴቶቹ ውለታ መቼም የሚረሳ አይደለም" ይላል መጽሐፋቸው፡፡ ይሄ ሆኖ እያለ ሀቁ እነሱ ግን " አውአሎም የሚባለው ሰላይ ባይኖር ኖሮ የምኒልክ ጦር አልቆለት ነበር" በሚል "የጦርነቱ አሸናፊ ምኒልክ አይደለም" የሚል ትርክት አመጡ፡፡ በርግጥ አውአሎም አስተዋፅኦ አድርጓል ግን ያ የአስተዋፅኦ ብቻ ነው ወይ የምኒልክን ጦር ውጤታማ ያደረገው? ካልን ይሄ ትልቅ ስህተት ነው የሚሆነው፡፡

የአድዋ ድልና ጦርነት የአድዋ ዕለት ብቻ አይደለም፣ የሚጀምረው ከአምባላጌ ነው፡፡ ገና ከአዲስ አበባ ሲነሱ ነው ጦርነቱ የተጀመረው፤ ኢህአዴጎች ግን ይሄን ሁሉ መርሳት፣ ድሉ "የእኔ ነው፣ የእኔ ነው" ወደ ማለት ገቡ፡፡

ሶስተኛ እነዚህ ሰዎች ምን ትርክት አመጡ? "እንደ አድዋ ያለ ጦርነት እኮ እኛን ሲያደኸየን ነው የኖረው፤ የመሀል ሀገር ሠራዊት እየመጣ እዛ በመቀመጡ ነው፣ ለሰሜን ኢትዮጵያና ለትግራይ ድህነት ምክንያት የሆነው" የሚል አጨቃጫቂ ነገር ማንሳት ጀመሩ፡፡ ይሄን የሚቃወማቸውን ደግሞ "ሁለተኛ አድዋ ድርሽ እንዳይል" ብለው የአዘዙ ሰዎች ሆኑ፡፡ በአሉ የሀገር ክብረ በዓል መሆኑ ቀረና የተወሰኑ ካድሬዎች ሽር ጉድ የሚሉበት ሆኖ ለዘመናት አይተነዋል፣ እስከ አምና ድረስ ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- አሁን በሀገሪቱ የለውጥ ተስፋ ፈንጥቆ፣ ከ27 ዓመት በኋላ "ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ"**

**የሚባልበት ጊዜ ነውና የአሁኑ አከባበር ምን ዓይነት ይሆናል ብለህ ታስባለህ?**

ሬ/ፐ/ር አበባው፡- አሁን እንግዲህ ገና ከጅምሩ ስናይ ለውጥ ያለ ይመስላል፡፡ አንደኛ ይሄ ምኒልክ ላይ የሚነሳው አተካራ በረድ የማለት ሁኔታ ይታይበታል፡፡ ሁለተኛ ሚዲያዎቹ ለይስሙላ ሳይሆን አስቀድሞ በጉዳዩ ላይ ሲረባረቡ እናያለን፣ የእናንተን መጽሔት ጨምሮ ሁሉም ትኩረት ሰጥተውታል፡፡ የሚከበርበት አውድም በጣም ሰፍቷል፤ ዩንቨርስቲዎች በተለያየ ቦታ እየተዘጋጁ ነው፡፡ በወረኢሉ፣ ደብረብርሃን ትልቅ ዝግጅት እየተካሄደ ነው፣ በተቋማት ደረጃ አሁን የአድዋ በአል አከባበርን እየሰሩ ነው፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ በዓሉ የሚገባውን ትልቅ ክብር እያገኘ ይሄዳል፣ ከታሪክም ብዙ የምንማረው ነገር ይኖራል፡፡

አድዋን ስናከብር አንደኛ ያለፈው ትውልድ የከፈለውን መስዋዕትነት ለመዘከር ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ እኛም ያንን ፈለግ ተከትለን ያንን አኩሪ ታሪክ ነው የምናሳድገው፤ ኢትዮጵያዊነትን ስሜት እንዴት ነው የምናገሎለብተው? ለሚለው ወሳኝ ነጥብ መግሪያ ይሆናል፡፡ እነርሱ እኮ በአንድ የሀገር ስሜት ነው የዘመቱት፤ እኛስ እንዴት ነው በአንድ የሀገር ስሜት የምንጓዘው? የሚለውን ነገር የምንለከትበት ይሆናል፡፡

**ግዮን፡- አድዋ ብዙ ጊዜ በአዲስ አበባ ሲከበር ቆይቷል፣ አሁን ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ በአድዋ ይከበራል፡፡ ግን በትክክል ይህ ቀን የት ነው መከበር ያለበት?**

ሬ/ፐ/ር አበባው፡፡- በነገራችን ላይ አድዋ አዲስ አበባም፣ አድዋ ላይም ይከበራል፡፡ 1988 ዓ.ም ከመቶኛ ዓመት ክብረ በዓሉ በኋላ ነው፡ ፡ "ድሉ የእኛ ነው" የሚል ነገር መጣና መከበር የተጀመረው፡፡ አሁን አድዋ ላይ የሚከበረው ለሁለተኛ ጊዜ አይደለም፣ ከ1989 ጀምሮ እስከ አምና ድረስ ሲዘከር ነበር፡፡ እንዴት ነው የሚያከብሩት? ካልን፣ በእነ ስብሐት ነጋ ዙሪያ የተሰባሰቡ የተወሰኑ ካድሬዎች አሉ፣ አሽከር የሆኑ ምሁራን ነን ባዮች አሉ፣ እነዛ ሁሉ በአሉን ያከብራሉ፡፡

አምና ትንሽ ለየት ነበር አከባበሩ፡፡ "በአፍሪካ ደረጃም እናርገው፣ ይሄ ትልቅ በአል ነው" ተብሎ እንደው ትንሽ ጥሩ የሆነ ድባብ ተሰጥቶት ነበረ፡፡ ዘንድሮም ከዛ ያንሳል ብዬ አልጠብቅም፡ ፡ አድዋ ላይ ሁሌም ዝግጅት ቢኖር ጥሩ ነው፣ ታሪካዊ ቦታ ስለሆነ፡፡ ግን አድዋ ትልቅ ዝግጅት ተደርጎ መከበር ያለበት፣ ዋነኛ የሀገሪቱ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ነው፡፡ መተማ ሲዘከር እኮ መተማ ሄደን አይደለም የምንዘክረው፣ እዚህ ነው የምናከብረው፡፡ የሀገሪቱ መዲና ይከበር ስንል እኮ ርዕሰ ብሔሮቹን፣ የሃይማኖት መሪዎችን በሚመጥን መንገድ ማክበር ስለሚቻል ነው፤ ልክ እንደሌሎች በዓላት ሁሉ ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- ኢትዮጵያ ከአድዋ ምንድን ነው ያተረፈችው? ይህ ታሪካዊ ድል ለአፍሪካውያን የሚሰጠው ትርጉምስ ምንድን ነው?**

ሬ/ፐ/ር አበባው፡- ኢትዮጵያ ከአድዋ ያተረፈችው ነገር ሲባል፣ ከአድዋ በኋላ ምንድን ነው የሆነው? የሚለውን ማየት ተገቢ ነው፡፡ ከአድዋ በኋላ ኢትዮጵያውያን ትልቅ የሞራል ልዕልና ነው የነበራቸው፣ የወቅቱ ትውልድ ማለት ነው፡ ፡ ያንን የሞራል ልዕልና" ማንም የበላይ ነኝ ባይ ነጭ መጥቶ ሊሰብረን አይችልም፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፣ ፈጣሪ ይህቺን ሀገር ለማንም አሳልፎ አይሰጥም" በሚል ሐይማኖቱን፣ እምነቱን፣ ወጉን፣ ባህሉን ጠብቆ እንዲቆይ ያደረገው የአድዋ ድል ነው፡፡ ማንነቱን ያቆየው የአድዋ ድል ነው፤ ይሄ የኢትዮጵያውያን ትርፍ ነው፡፡

ለአፍሪካውያን ትርፉ ምንድን ነው? ብንል ወዲያውኑ ትንሽ አስደንግጦ ነበር፡፡ ምክንያቱም በአድዋ ጊዜ ያልተያዘና ነፃ የሆነ መሬት አፍሪካ ውስጥ ሁለት ቦታ ነው፡፡ አንደኛው የኢትዮጵያ ሀገር ሲሆን ሁለተኛው ሱዳን አካባቢ፡ ፡ መሀዲስቶች (ሱዳን) የግብፅና የእንግሊዝን ጦር ወግተው ነው ያባረሩት፤ ልክ "አድዋ ላይ ኢትዮጵያዊያን አሸንፉ" ሲባል እንግሊዞችን ያስደነገጣቸው "ይሄ ሁለቱ ኃያል ከተቀናጀ ለሌላውም የአፍሪካ ክፍል መጥፎ ምሳሌ ነው የሚሆነው" የሚል ነው፡፡ ኢትዮጵያን እንደማይወሩ ስለሚያውቁ ሱዳንን መትተው ሀገሪቱን ቅኝ ግዛት ለማስገባት ወዲያው ነው ዝግጅት የጀመሩት፡፡ በአመቱ አደረጉት፡ ፡ የአውሮፓ ሌሎች ቅኝ ገዢዎችም አፍሪካ ላይ ወታደራዊ እንቅስቃሴውን ጠበቅ ማድረግ አለብን የሚል አቋም እንዲይዙ አድርጓል፡፡

ውሎ አድሮ ግን ለአፍሪካውያን ብቻ ሳይሆን ለጥቁር ህዝብ ትልቅ የነፃነት ጮራ ፈንጣቂ ነው የሆነው፡፡ የነጭ የበላይነት በሰፈነበት ወቅት ጥቁሮች ባህል አላቸው፣ የራሳቸው ንጉስ አላቸው፣ የራሳቸው ስነ ፅሁፍ አላቸው፣ የራሳቸው ስልጣኔ አላቸው፣ በክርስትናውም እኮ የበለጠ ዕምነት አላቸው ተብሎ  እስከ ካሪቢያን ድረስ የአሜሪካውያን የኔግሮ ፍሪድመንትን (የጥቁሮች ነፃነትን) ያነቃቃ ነው፡፡

**ግዮን፡- በአድዋ ድል ላይ የአፄ ምኒልክና የእቴጌ ጣይቱ አስተዋፅኦ እንዴት ይገለፃል?**

ሬ/ፐ/ር አበባው፡-ሁለቱም የተለያየ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡አፄ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት ላይ የነበራቸው የመሪነት ሚና የሚናቅ አይደለም፤ ከክተት አዋጁ ጀምሮ በጥንቃቄ ነው የሄዱበት፡ ፤ አንዱ እንዳያኮርፍ ሌላው እንዳይደሰት በሁለት ነገሮች አስረው ነው የያዙት፡፡ ህዝቡ ሐይማኖተኛ ስለነበር "ማርያምን አልምርህም፣ ወስልተህ ከቀረህ!" ማለታቸው ወቅቱን ያገናዘበ ትልቅ ክተት ሲሆን፤ ሁለተኛ "የሀገሬ ህዝብ ሆይ እንደው በሚቻለው ሁሉ አስተዳድሬሀለሁ፣ የበደልኩህም አይመስለኝም፤ የበደልኩህ ነገር ካለም ይቅር በለኝ" ብለው ነው የተነሱት፡፡ ይሄ ከመጀመሪያው በጥንቃቄ እንደሰሩበት ያሳያል፡፡

እንደገና "ጉልበት ያለህ በጉልበትህ፣ ጉልበት የሌለህ በፀሎትህ እርዳኝ" ማለታቸው ሲታይ አዋጁ ትልቅና ግሩም አዋጅ እንደሆነ ትረዳለህ፡ ፡ ይሄን አስቦ ለህዝብ ጥሪ ማቅረብ ቀላል ነገር አይደለም፤ ከዛ በፊት የነበረውን የመሳፍንቱን አለመግባባት ፈትተው አስተማምተው መያዛቸው ሌላው ትልቁ ነገራቸው ነው፡፡ ሁሉም አስተዳዳሪ በየክልሉ ጠላቱን ነቅቶ እንዲጠብቅ፣ አንድ እንዲሆን ማድረግ መቻላቸው ብልህነታቸውንና ጦርነቱ ላይ የነበራቸውን አስተዋፅኦ ያሳያል፡፡

የጣይቱን አስተዋፅኦ ስናይ እርሷ ቀላል ሰው አይደለችም፤ ከትውልዷ ጀምሮ በጣም ዘመደ ብዙ ሰው ናት፡፡ ላስታና ዋግ ሀገሯ ነው፣ ሰሜን ሀገሯ ነው፣ ወሎና የለም ጎጃም ሀገሯ ነው፣ ደብረ ታቦር ሀገሯ ነው፡፡ ምኒልክ ይህቺን ሴት ሲያገባ ራሱ ትልቅ የፖለቲካ ጥቅም ነበረው፡፡ ምኒልክ ንጉስ ቢሆንም ትውልዱ ከዚች ከሸዋ አይወጣም፡፡ አድዋ ሲዘመት የስንቁን ጉዳይ የያዘችው እቴጌ ጣይቱ ናት፡፡ አንደኛ ስራ ቤቱን እንዳለ ነው ይዛቸው የሄደችው፤ የሚዘምተው የባላገር ጦር ነው፣ ስንቅ ከሌለው፣ ካልበላ ይበተናል፡፡ ዘመቻውና ጦርነቱ ከተራዘመም ይበተናል፡፡ ከዛ በፊት ሰሜን ኢትዮጵያ ርሃብና የከብት በሽታ ስለነበር ባለገሩን እየወሰድክ እዛ ቦታ ላይ ልትጥለው አትችልም፡፡

በዛ ምክንያት የስንቅ ሁኔታውን እቴጌ ጣይቱ ነች ያደራጀችው፡፡ ከየቦታው የሚመጣውን ስንቅ ወረኢሉ ላይ እንዲጠራቀም አደረገች፡፡ መሀል ላይ መቀሌ የተቀመጠውን ጦር ጣልያኖች ውጊያውን በማዘግየት ሠራዊቱ እንዲበተን ነበር የፈለጉት፡፡ ስንቅ ሲያልቅ ወዲያውኑ ወደ ደብረታቦርና ላስታ፣ ወደ ሰሜን በመላክ በቀላሉ ስንቅ እንዲያገኙ አድርጋለች ጣይቱ፡፡ የራስ ገብሬ ዘመድ መሆኗ ጠቅሟታል፡፡ በእርሷ ስር ወደ 16 ሺህ የሚሆን ሰው ታዝ ነበር፣ ከዛ ውስጥ ወደ ስድስት ሺህ የሚሆነው ተዋጊ ነው፡፡ ሌላው ስንቅ የማቀበልና የማብቃቃቱን ጉዳይ የሚሰራ ነበር፡፡ ስለዚህ ጣይቱም በአድዋ ላይ የነበራት ሚና እንዲህ በቀላል የሚገልፅ አይደለም፡፡

**ግዮን፡- ግን እነዚህ ሰዎች ለሰሩት ስራ ተገቢውን ክብር በዚህ ዘመን  እየተሰጣቸው ነው ማለት ይቻላል?**

ሬ/ፐ/ር አበባው፡-እስካሁን ያለውን እንውሰድ ሐውልት ቆመ፣ ምኒልክ መታሰቢ ቤት ተሰርቶ ነበረ ባዕታ ማለት ነው፤ አሁን ቤተክርስቲያን እንጂ የምኒልክ መታሰቢያ ቤት ብሎ የሚያስብ ማንም የለም፡፡ ከዛ በኋላ የመጣውም ትውልድ አንድ ሐውልት ቆመች ተብሎ፣ በዛ ላይ ይፍረስ አይፍረስ ተብሎ ጭቅጭቅ የሚያነሳ አሳፋሪ ትውልድ እኮ ነው፡፡ በሰሩት ደረጃ ሊያከብራቸውና ሊዘክራቸው ቀርቶ ያለውንም በቅጡ አልያዘም፡፡ ጣይቱ የአዲስ አበባ መስራች ነች፣ አዲስ አበባ ላይ ለጣይቱ ብጡል ምንድን ነው ያለው? አንዲት ቁስቋም ጋር ያለች አንዲት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ብቻ በቂ ናት? ለእነዚህ ሰዎች እኮ ትልልቅ ተቋማት መኖር ነበረባቸው በስማቸው፡፡ በተለይ ለጣይቱ ማለት ነው፡፡ከዛ አልፎ ተርፎ ለማራከስ እየተባለ የእነሱን ስም አወዛጋቢ ማድረግ  ጥሩ አይደለም፡፡

**ግዮን፡- ጥቂት የፖለቲካ ሰዎችና ምሁራን የምኒልክን ታሪክ ማሳነስ ይፈልጋሉ ይሄ ለምንድን ነው?**

ሬ/ፐ/ር አበባው፡- ትውልድ ተወራራሽ ነው፣ መጥፎም ተሰራ በጎ እየተወራረሰ ነው የሚሄደው፡፡ ከዘመን ጋር የሚያሻሽለውን እያሻሻለ ነው የሚሄደው፡፡ ታሪክን ስለምትወርሰው አይቀየርም፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ አንዱ ብሄር ሌላውን ሲያምሰው፣ ሲበዘብዘው የኖረ ነው ብሎ የተነሳ ኃይል ከዚህ የተለየ ሌላ ምንም ሊናገር አይችልም፡፡ ላለፉት 27 ዓመታት ያ ነው የሆነው፡፡ ከታሪክ ጋር የተጣላ ፖለቲከኛ ትውልድ ተፈጥሯል፣ከ1968ዓ.ም ጀምሮ፤ በተለይ ሕወሓት ከተፈጠረ ጀምሮ፡፡

አንደኛ ይህ ቡድን ከራሱ ጋር ተወዛግቦ ተጣልቶ የራሱንም ታሪክ፣ የአካባቢውንም ታሪክ እየረሳ፣ እያበላሸ ነው የኖረው፡፡ የሚያስተዳድራትን ሀገር እኮ እሱ አይደለም የፈጠራት፣ ድንበሯን ያስከበረላት፣ እሱ አይደለም ነፃነቷን ያስከበረው፡ ፡ የምኒልክና የቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ትውልድ ነው፣ የእነ መንግስቱ ኃ/ማሪያም ትውልድ ነው፡፡ ድንገት ከሰማይ የወረደች ኢትዮጵያን አይደለም ሕወሓት የተረከበው፡፡ ከታሪክ ጋር ጠጣልቶ የተነሳ የፖለቲካ ሀይል ሁልጊዜ በታሪክ ውስጥ ያሉ ታላላቅ ሰዎችን ማንቋሸሽ ስራው ነው፡፡

የአደዋ ድል የኢትዮጵያ ህዝብ ድል ነው፡፡ ህዝብ ደሙን አፍሷል፣ በፀሎት አግዟል፣ አጥንቱን ከስክሷል፡፡ አሁን "የትግራይ ድል ነው" "የአማራ ድልነው" "የኦሮሞ ድል ነው" የሚሉ ሰዎች መጀመሪያ በታሪክ ላይ ሁሉንም ባለድርሻ ማድረግ እንደማይቻል ማወቅ አለባቸው፡፡ መተማ ላይ የሞቱት አፄ ዩሐንስ ትግሬ ስለሆኑ ይሄ ትግራይ ታሪክ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ታሪኩ የኢትዮጵያ ታሪክ ነውና፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

# ‹‹ከስንት ዓመት በኋላ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እየሸተትን ነው!››



በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

እንኳን አደረሳችሁ፤ ዛሬ የዓድዋ በዓል ነው፡፡

‹‹ኧረ ጉዱ በዛ፤ ኧረ ጉዱ በዛ፤

በጀልባ ተሻግሮ ሃበሻን ሊገዛ፡፡››

…ብለው አዝማሪዎች ያንጎራጎሩለትን፤ የጣሊያንን ሠራዊት ኢትዮጵያዊያን ከዳር እስከ ዳር በኅብረት ንቅል ብለው፣ ዘምተው ድል የመቱበት፣ ታላቁ መኩሪያችን፤ ዓድዋ፡፡

‹‹ማጆር ጋሊያኖ ጄኔናር በራትሪ፤

እናንተን ማን ችሎ ያለ ፈጣሪ!››

ተብሎላቸውም ነበር በወቅቱ፣ አዋጊዎቹ እነጋሊያኖ እና እነጄኔራል ባራቴሪ፤ ወኔ፣ አንድነት እና ፍቅር ያጋመደው የኢትዮጵያ ሠራዊት ዓድዋ ላይ አንኮታኩቶ ሳያስቀራቸው በፊት፡፡

…ኤዲያ! ስለ ዓድዋ ድል ምኑ ይወጋል ጎበዝ!? የትኛው ተነስቶ፣ የትኛውስ ይተዋል!? (‹‹ጄኔናር በራትሪ›› በዘመኑ አዝማሪዎች፣ ‹‹ጄኔራል ባራቴሪ›ን› የሚጠሩበት ቃል ነው፡፡ ወትሮስ ጥሊያን ለአንደበታችንስ መች ይመችና!)

ቃና ቴሌቪዥን፣ ስርጭት የጀመረ ሰሞን፣ ግድያ፣ ስርቆት እና አፈና የበዛባቸው፤ የጣሊያን ተከታታይ የማፍያ ድራማዎችን ያሳይ ነበር፡፡

እኔ ኾዬ ታዲያ በአንዱ የዓድዋ ሰሞን ምሽት ላይ የቴሌቪዥን ጣቢያ እየቀያየርኩ ቀልብ የሚስብ ፕሮግራም ስፈልግ፣ ድንገት እጄ ላይ ያለው ‹ሪሞት› ወስዶ የቃናው የማፊያዎቹ ፊልም ላይ ጣለኝ፡፡ ልቀይር፣ ‹ሪሞቱን› ልጫን ስል፣ ‹‹ተወው!›› የሚል ድምፅ ከወደ ጀርባዬ መጣ፡፡ (ውይ! …ከገጠር የመጣው አጎቴ ነው፡፡)

‹‹ደህና ዋልክ አጎቴ!?››

‹‹ይመስገነው!

‹‹ድራማውን ማየት ፈልገኽ ነው?››

‹‹አዎ!››

…ተውኩለት፡፡

‹‹ዕድሜ ለዓድዋ፤ ዕድሜ ለአባቶቻችን!›› አለ በታላቅ ኩራት ጥቂት ካየ በኋላ፡፡

‹‹እንዴት?›› አልኩት፤ ዓድዋ እና የሚታየው ድራማ አልገናኝልህ ቢለኝ፡፡

‹‹እነዚህን ነጫጭባዎች ሳይወዱ በግድ አማረኛ አናገርናቸው!››

ሳቁ መጣ፡፡ አጎቴን ዘወር ብዬ አየሁት፡፡ ምናምን ቀማምሶ ሞቅታ ተጭኖታል፡፡ አጎቴ ሲቀማምስ ጨዋታ ይሆንለታል፡፡

ቤታችንም ሆነ ከቤታችን ውጪ እንዳጋጣሚ የቃና ቴሌቪዥን ተከፍቶ ስመለከት ይኽ የአጎቴ ንግግር ትውስ ይለኝና ብቻዬን እስቃለሁ፡፡

‹‹እነዚህን ነጫጭባዎች ሳይወዱ በግድ አማረኛ አናገርናቸው!››

የዛሬ ዓመት፤ በዛሬዋ ዕለት የአድዋ ድልን ለማክበር ጊዮርጊስ፣ ዐፄ ምኒልክ አደባባይ ተገኝቼ ነበር፡፡ በዓሉ፣ ከዚያ ቀደም ካሉት በዓላት በተለየ ሁኔታ ሞቅ ደመቅ ብሎ የተከበረና እጅግ በጣም ብዙ ሕዝብ የተገኘበት ነበር፡፡ በተለይ የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ እና የእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቴአትር ተማሪዎች ለበዓሉ መድመቅ የራሳቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንዲህ ላለው ታሪካዊ ክንውን ወጣቱ የሚሰጠው ቦታና የሚያሳየው ክብር በእጅጉ ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡ (ብሔር ለብሔር የምንፋለምበትን ሜዳ ማን እንደሚያበጃጅልን የምትታዘቡት እንዲህ ባለው አገራዊ ጉዳይ ላይ የሕዝቡን ተሳትፎ ስታዩ ነው፡፡)

ዓድዋ ድረስ የሚደረጉ የእግር ጉዞዎች፤ ከትግራይ ጀምሮ በተለያዩ ከተሞች የሚዘጋጁት፣ ዕለቱን መዘከሪያ ፕሮግራሞች እየበዙ መምጣታቸው እውነትም ይኽ ትውልድ ለሀገሩ ታሪክ የተለየ ተነሳሽነት እያሳየ እንደኾነ ምስክር ይሆናል፡፡

ልብ በሉልኝ፤ እንዲህ ስል ግን ይኽንኑ አጋጣሚ ለገንዘብ መሥሪያ ለማዋል የሚሯሯጠውን ቀጣፊ እያመሰገንኩ አይደለም፡፡ በጭራሽ! ‹‹ለበዓሉ ማካሄጃ በጀት ተይዟል›› ሲባል እሷኑ ለመቀርጠፍ፣ ‹‹ዋ ዓድዋ!›› እያለ እያቅራራ የየቢሮውን ደጃፍ የሚያንኳኳው አሞራ ብዙ ነው፡፡

(‹‹ጉዞ ዓድዋ››ም ቢሆን ዘንድሮ ሁለት እና ሦስት ቡድን መሆኑ፤ እንዲሁም ‹‹የባለጫማ እና የባለባዶ እግር›› ተጓዦች እሰጥ አገባ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊን በእጅጉ አሳዝኗል፡፡ የጉዞው ዓላማ ድንቅ ነው፤ ከጊዜ ወደ ጊዜም እየተሰጠው ያለው ትኩረት ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ግን በአንድነት እና በመስማማት ቢሆን ሸጋ ነበር፡፡ እሰጥ አገባው ለማንም አይጠቅምም፡፡ አንዱ ጸሐፊ እንዳለው፤ ያ ሁሉ ብዙ ሺህ የምኒልክ ሠራዊት፣ ‹‹ስንቅህን በጀርባህ፤ አመልኽን በጉያህ›› ተብሎ፣ ዓድዋ ተጉዞ ጣሊያንን ድል መታ፡፡ እናንተ በቅጡ መቶ የማትሞሉ ልጆች እንዴት አመላችሁን በጉያችሁ፤ ይዛችሁ ለአንድ ዓላማ፤ በአንድ መቆም አቃታችሁ!?)

ወደ አምናው ጨዋታ እንመለስ፡፡ የምኒልክ አደባባይ ከመቼውም በላይ በሰው ተሞልቷል፡፡ እንደ ቀድሞው የምኒልክ ሐውልት፣ በብሔር ብሔረሰብ ባንዲራ ታጥሮ፣ ‹‹ዓድዋ ላይ የተጎናፀፍነውን ድል ድኅነት ላይ እንደግማለን፤ ዓድዋ ላይ የተጎናፀፍነውን ድል፤ የትራንስፎርሜሽን እቅድን ተግባራዊ በማድረግ እንደግማለን!…›› ወዘተ አይነት ውሉ የጠፋበት የካድሬ መፈክር የሌለበት፤ እንደ ሀገር፣ ሕዝቡ በአንድ ቆሞ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ ያለበት በዓል ነበር፡፡

ወጣቶቹ ታዲያ በተንቀለቀለ አገራዊ ስሜት ውስጥ ሆነው ሲዘምሩ፣ ሲያቅራሩ፤ ሲፎክሩ እና ሆታ ሲያሰሙ እኔም ተገኝቼ፣ በመገረም ስመለከት አንድ አዛውንት ድንገት መጥተው አጠገቤ ቆሙ፡፡

‹‹ዘራፍ አካኪ ዘራፍ፤

ዘራፍ፤ አካኪ ዘራፍ፤

ሀገሩ ጦቢያ ከሰፊው ቦታ፤

በአፉ ተናግሮ በእጁ ሚመታ፤

ዘራፍ አካኪ ዘራፍ፤

ዘራፍ አካኪ ዘራፍ

…እያሉ ወጣቶቹ ሲፎክሩ አዛውንቱ ድንገት ወኔያቸው ተቀሰቀሰ፤ ‹‹ጎሽ መከታዎቼ፣ በሉት እስኪ እንዲያ እንዲያ!›› እያሉ ማበረታታት ጀመሩ፡፡

‹‹አባቱ ነበር ዳጉሳ ዘሪ፤

ልጁ ደረሰ ጥይት መንዛሪ!”

‹‹አዬ ልጆቼ እንዲያ ነውዬ! እስኪ አሙቁት እንደሱ!›› የአዛውንቱ ደስታ ልክ አጣ፤ ወጣቶቹ ጨዋታቸውን ቀጥለዋል፡፡

‹‹ጎራው ና! ጎራው ና!››

‹‹መለያየት ክፉ አንድ መሆን ደጉ፤

ሜረኛው ወደቀ በየጥጋጥጉ!”

‹‹ምናለ ወድቆ በቀረ… ምን እሳት ትውልድ ገጠመኝ ጎበዝ፤ አሰማምሩት እንደሱ!›› አዛውንቱ ተቅበጠበጡ፡፡ አሁን አልቻሉም፡፡ ከዘራቸውን ሽቅብ ወድረው ወደ መሃል ዘለው ገቡና መፎከር ጀመሩ፡፡

‹‹ዘራፍ አካኪ ዘራፍ፤

ዘራፍ፤ አካኪ ዘራፍ፤

ይምጡ ባይ፤ ይሰብሰቡ ባይ፤

ሲሰበሰቡ እንበላቸው ባይ፤

ይምጡ፤ ይምጡ ይምጡ ይከማቹ፤


ለአንድ ሰው እንዲመቹ…

አዛውንቱም ጥቂት ትንፋሽ ሲያጥራቸው፣ ‹‹በሉት እስኪ እንዲያ እንዲያ!›› ብለው ወደ ዳር ሲወጡ ክብ ሠርቶ ሲያጅባቸው የነበረው ወጣት በሙሉ ሞቅ ባለ ጭብጨባ ተቀበላቸው፡፡

በዚህ መሃል ተንቀሳቃሽ ስልካቸው ጠራ፤ አነሱት፡፡ በታላቅ ግለት ውስጥ ሆነው እንዲህ አሉ፤

‹‹ሃሎ!›› አሉ ጮኽ ብለው፤ ‹‹ሃሎ! እንዴት ነህ? ይኸውልኽ ከስንት ዓመት በኋላ ወንድ ወንድ እየሸተትን ነው፡፡ ና እባክህ ተቀላቀለን፤ ምንሊክ አደባባይ ነን!›› …ስልካቸውን ዘጉና ወደ መሃል ተወርውረው ገቡ፡፡

ንግግራቸው ልቤ ላይ ቀረ፤ ‹‹ከስንት ዓመት በኋላ ወንድ ወንድ እየሸተትን ነው፡፡›› እኔ ግን የሕዝቡን ብዛት፤ በአንድ ባንዲራ ጣራ ስር ለአንድ አላማ መሰባሰብን ልብ ብዬ ሳይ፣ የእኚህን አባት ንግግር እንዲህ ስል አረምኩት፤ ‹‹ከስንት ዓመት በኋላ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እየሸተትን ነው!››



ጌኖክ ገለታው

# የአጼ ምኒልክ ነገር

የዓድዋ ድል የተለመዱትን የዓለም የድል መዝገቦች ታሪክ ከታች ወደ ላይ ነቅንቆ በመገልበጥ ረገድ ተስተካካይ የለውም:: እንዲህ ያለ ሁነትን የቲያትር ጥበብ ሰዎች "ድንቃይ" ወይም "ሜሎ ድራማ" የሚል ሥም ይሰጡታል:: ድንቃይ ተውኔት በሁለት የወደረኛነት ችግር ባለባቸው አቀንቃኝ እና ተቀናቃኝ ገጸባሪያት መካከል በሚደረግ የጠነከረ ግጭት ሳቢያ በጥንካሬውና በብቃቱ የደከመ አቅምን የተላበሰው ገጸባህሪ ጉልበቱና ጡንቻው የፈረጠመው ኃያሉን ገጸባህሪ ድል በማድረግ የሚያጠናቅቅበት የተውኔት ዓይነት ነው (ሚዳቆ እንደምንም ተፍጨርጭራ ነብርን ዘርራ የመጣል ተደርጎ ሊታሰብም ይችላል):: ዓድዋ በአሸናፊነት ውስጥ ከፈረስ ጉልበት ይልቅ እውነት ፣ዕምነት ፣የጦር ሳይሆን የሥነልቦና ጥንካሬ ትልቅ ዋጋ እንዳለው ያስተማረን ፣ የክብርና የማያልቀው ኩራታችን ምንጭ የሆነ ትልቅ ድል ነው:: ክብር ኢትዮጵያን በደማቸው ዋጅተው ላቆዩ እመውና አበው!

የዛሬው መጣጥፍ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክን በሚመለከት በ1985 ዓ.ም ከታተመችው "ሙዳይ" መጽሔት የተመዘዘ አንድ የታሪክ ቅንጣት ላይ ያተኩራል:: ከዚያ በፊት ግን ጥቂት ነገር ስለ "ኡንተር መንሽ"…

## "ኡንተር መንሽን" በነጭ ቀለም!?

የአውሮጳውያን ከልክ በላይ የተለጠጠው ቅኝ የመቀራመት አባዜ ዓድዋ ላይ በተባበረው የኢትዮጵያውያን ክንድ መገታቱን ተከትሎ ወራሪዎቹ ኃይላት በኢትዮጵያ ላይ ይከተሉት የነበረውን ፖሊሲ ቆም ብለው ለማስተዋል ተገደዱ:: ኤሚለ ሉድዊንግ የተባለ ተመራማሪ "ዘ ናይል" በተባለው ጥናታዊ መጽሐፉ በግልጽ ያሰፈረው ሃሳብ የሚከተለውን ይመስል እንደነበር አንጋፋው ብዕረኛ ሙሉጌታ ሉሌ በአንድ መጣጥፉ አስፍሮልናል:: "በዓድዋ ድል ማግሥት የድሉ ባለቤት አጼ ምኒልክ አውሮፓውያን ፈጽሞ ያላሰቡትና ያልገመቱት በታሪካቸው ውስጥ ታላቁ የፖለቲካ ሰው ኦቶቫን ቢዝማርክ ብቻ ከሳዶዋ ድል በኂላ ያቀረበውን ጥያቄ አቀረቡ:: አውሮፓውያን ለኢትዮጵያ ነጻነት ዕውቅና እንዲሰጡና በዓለም ካርታ ላይ ነጻ መንግሥታት በሚወከሉበት ኅብረ ቀለም እንድትወከል::"

ይህንን የምኒልክ ጥያቄ አይደለም ኢጣሊያ መላው አውሮጳ የግዱን መቀበሉን ስናስብ በዘመናዊ ጦር መሳርያ ካልዘመነው የሃገራችን ሰራዊት (አርበኛ) ይልቅ ንጉሡ እንደ ግለሰብ የፈጠሩት ተጽዕኖ በሚገባ ተተንትኖ መገለጽ እንደሚገባው ጥያቄ ሳያጭርብን አያልፍም:: ዓድዋን ከምኒልክ ነጥሎ "መዘከር" የሚዳዳው አስገራሚ ትውልድ እዚህም እዚያም መብቀሉን ስንታዘብ ደግሞ መገለጥ ያለበት ብዙ እውነት ተሸፍኖ እንደቆየ ዓይናችንን ገልጠን እንድንጠረጥር ያደርገናል:: ወደ ነገራችን ስንመለስ … ለአውሮጳውያን በጥቁር ሕዝብ ክንድ ተደቁሶ መሸነፍ የሞት ሞት ነበርና ይህን እውነታ በመካድ "የነጭ ዘር በሁሉም ላይ የበላይ ነው" የሚለውን የዘረኝነት አመለካከታቸውን የሚያጸኑበት መላመቱ:: እናም ሀሮልድ ማርክስ "የምኒልክ ሕይወትና ዘመን ታሪክ" በተሰኘው መጽሐፉ "አውሮፓውያን መላው የአፍሪካ ሕዝብን 'ኡንተርመንሽ'(የነጭን ዘር ለማገልገል የተፈጠረ ዝቅተኛ) ብለው ነበር የመደቡት:: ከዓድዋ ድል በኂላ ግን ቢያንስ ቢያንስ አንድ የጥቁር ዘር (አበሻ) ከዚህ ምድብ ውጪ ማድረግ ግዴታ ሆኖባቸዋል:: ስለዚህም የኢትዮጵያን ሕዝብ ነጭ ቀለም መቀባት ጀመሩ:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ከአፍሪካዊው ወገኑ በተለየ የነጭ ዘር ያለው መሆኑን በግልጽ መስበክና መጻፍም ተያያዙት:: አዎን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደተቀረው የአፍሪቃ ሕዝብ 'ኡንተርመንሽ' ከሆነ የነጭ ዘር በጥቁር ዘር እጅ ሊሸነፍና ሊበለጥ እንደሚችል ማመን ስለነበር የግድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጭ ቀለም ተቀባ::" በማለት ገልጿል:: ምኒልክ ዓድዋ ላይ የነበራቸውን የማይተካ ሚናና ዋጋ የዛሬው ትውልድ ከገባው እጥፍ በላቀ ከመቶ ዓመታት በፊት ዓለም ተረድቶ የከበረ ቦታ ይሰጠው እንደነበር ከዚህ ቀደም በዚሁ በግዮን መጽሔት አጭር ክለሳ (Review) ባደረግሁበት "ታላቁ ጥቁር" መጽሐፍ በህልቆ መሳፍርት ማስረጃዎች በልጽጎ ተቀምጧል (አንባቢ ሆይ ወዴት አለህ!)::




አሁን ወደ ቀደመው ነገሬ ልመለስ:: ኅዳር 1985 ዓ.ም በሙዳይ መጽሔት የ"ቃለ ምልልስ" አምድ ቆይታ ያደረጉት የሦስት መንግሥታት የጋዜጠኝነት ሙያቸው ሰለባ የነበሩት ወ/ሮ ሙሉ ወንድማገኘሁ አስደናቂ ገጠመኞቻቸውን ለታሪክ ምስክር በሚሆን መንገድ ነግረውናል:: ጋዜጠኛ ሙሉ ወንድማገኘሁ በደርግ ዘመነ መንግሥት በሃገራችን በነበሩት ክፍለሃገራት በመዘዋወር የሕዝቦችን ማኅበራዊ አኗኗር ሥርዐት ፣ወግ ፣ ባህል ፣ ቋንቋ ልዩ ልዩ ዕሴቶች በቴሌቪዥን ካሜራ የተደገፈ ጥንቅር በመስራት ብዙዎች "ከምንጩ ይጎንጩ" ብለው የመሰከሩለትን ፕሮግራም በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን በማቅረብ ፈርቀዳጅ የቱሪዝም ጋዜጠኛ ነበሩ:: ጋዜጠኛዋ በአንድ ወቅት በደቡብ ኦሞ ወንዝ ዳርቻ እና ምዕራባዊው የኢትዮጵያ ጠረፍ ክፍል በሚኖሩት ሐመሮችና ሱርማዎች ዘንድ ያጋጠማቸውን ከአጼ ምኒልክ ጋር የተያያዘ አስደናቂ ሁነት እንደሚከተለው ተናግረዋል::

"… ከሦስት ክፍለ ሃገር በስተቀር ያልደረስኩበት ክልል የለም:: በተለይ ከአዲስ አበባ 800 ኪ.ሜ ርቀት በሚገኘው የጋሞ ጎፋ ክልል በገለብና በሐመር ብሔረሰብ የመኖርያ አካባቢ እንዲሁም የሱርማን የብሔረሰብን የባህል አኗኗር ስመለከት ያጋጠመኝ ትርዒት ኢትዮጵያዊነቴን ደጋግሜ እንድመረምር ያደረገኝ መልካም አጋጣሚ ነበር:: 'ኢትዮጵያዊ ነኝ' ከማለት በስተቀር ስለ ኢትዮጵያ የማውቀው ምንም ነገር እንደሌለ ያወቅሁት ያን ጊዜ ነው:: በጉዞው ላይ ፊልም አንሺው አቶ ኤሊያስ ብሩ ፣ የቱሪዝም ኮሚሽኑ አቶ ተስፋዬ ብርሃኑ ፣ የእማማኮው አቶ ተፈሪ መኮንንና አንድ አስተርጓሚው ተገኝተው ነበር:: መንገዱ አስቸጋሪ ነው:: እስከ መኪናችን ውኃ ሞልቶ ለአደጋ የተጋለጥንበት ወቅት ነበር:: ይህን ሁሉ ችግር ተቋቁመን ገለብን ፣ ኤርቦሬንና የሐመር ብሔረሰቦችን አገኘናቸው:: በዚያ አካባቢ የሰው ልጅ ያለልብስ ዕርቃነሥጋቸውን ይኖራል:: ሰው በመሆናቸው ብቻ ከአውሬ ይለዩ እንደሆነ እንጂ አኗኗራቸው ምንም ዓይነት ልዩነት የለውም:: ገላቸውን ጭቃ ይቀቡታል፤ አይታጠቡም:: ልብስ የለበሰ ሰው ሲያዩ 'ትገማለህ' ብለው በጥፊ ይማታሉ::… ብሔረሰቦቹ ውሸት አይናገሩም :: መምሸት መንጋቱን እንጂ ዕለቱን ቢጠየቁ አያውቁም:: ኢትዮጵያን ግን ያውቃሉ ፤ ኢትዮጵያዊነታቸውንም ጭምር:: የሚይዙት የጦር መሳሪያ በአጼ ምኒልክ ጊዜ ያገኙት ነው:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ምኒልክን እንጂ ሌላ መንግሥት አያውቁም ነበር:: በአካባቢያቸው አጼ ምኒልክ የተከሉት ዛፍ አለ:: ኬኒያ ጠረፍ ላይ ነው የሚገኘው:: ያንን ዛፍ አልፎ የውጪ ዜጋ እንዲገባ አይፈቅዱለትም:: ዳር ድንበር ይጠብቃሉ 'ምኒልክ የጦር መሣሪያ ይላክልን' ብለው መልዕክት እንድናደርስም ጠይቀውናል:: ሌሎች ጠረፍ አካባቢ ያገኘናቸው የሱርማ ብሔረሰብ ይባላሉ:: እንደ እንስሳ የዱር ፍሬ እየለቀሙ የሚበሉ ናቸው:: ከንፈራቸውን ይበሳሉ፤ይተለተላሉ:: የነርሱን ወንዝ ተሻግረህ ወደ ሱዳን መግባት አትችልም ፤ አይፈቅዱልህም:: ከምኒልክ ፈቃድ አምጣ ነው የሚሉህ :: ከአጼ ምኒልክ በስተቀር አጼ ኃይለሥላሴንና ደርግን እነኚህንም አያውቋቸውም ::… "

ይህ እውነት "ኢትዮጵያዊነት" ብለን ስለምንጮህለት ሰብሳቢውና መግነጢሳዊው ማንነት መልሰንና ቀልሰን እንድናስብ ገፊ ምክንያት ይሆነናል:: ይህ እውነት ዛሬ ለምንራኮትበት ሀገር መፈጠር እና ህልው ሆኖ እዚህ መድረስ ምኒልክ የተባሉት ንጉሥ እንደተዋጣለት የህንጻ ዲዛይን ምን ያህል እንደተጠበቡ እንድንረዳ ያግዘናል:: ምኒልክ "ምኒልክ" ብቻ እንዳልሆኑ በሥማቸው ፣ በግብራቸው ፣ በዳናቸው ፣ በድላቸው ፣ በሞታቸው፣…ለአደባባይ ያልበቃ ሺህ ታሪክ ሺህ ገድል ያላቸው ንጉሥ መሆናቸውን ለመረዳት እውነትን ከመግለጥ ውጪ አሁንም ትውልዳችን ምርጫ ያለው አይመስልም::

መልካም ዓድዋ!!!



ዘሪሁን ሙላቱ (ዶ/ር)

# የእምዬ ሚኒልክ

## የሃይማኖት ፖሊሲና የአድዋ ድል

**"ኹሉም በአባቶቹ እምነት ይኑር በሀገሩ ግን አይደራደር::"**

*ዳግማዊ አጼ ሚኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*

በሀገራችን ኢትዮጵያ የሀገር መሪዎች ሀገርን ለመምራት ታላቁን ሚና የሚጫወትላቸው የሃይማኖት ፖሊሲያቸው ነው ፤ ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ የሃይማኖት ግጭቶች ነበሩ፤ ነገሥታትም ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የሚከፋፍል የሃይማኖት ፖሊሲም ይከተሉ ነበር ። ከዚህ አንጻር የአድዋን በዓል ለማዘከርና የእምዬ ሚኒልክን የሃይማኖት ፖሊሲ ለመተንተን ከጥንቱ ታሪክ ከመጀመር ይልቅ ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ከቅርቡ ታሪክ መነሻ ልምዘዝና ከዚያም የእምዬ ሚኒልክ የሃይማኖት ፖሊሲና በአድዋ ድል ላይ የነበረውን የሃይማኖት ተዋጽኦ የሚተነትነው ሐሳብ ላስከትል።

የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ የሚጀምረው ከአጼ ቴዎድሮስ ዳግማዊ መኾኑ ከማንም ያልተሰወረ ሕዝባዊ ዕውቀት ነው ። አጼ ቴዎድሮስ በዘመነ መሳፍንት በሃይማኖት ውጥቅንጧ የወጣውን ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ከሄዱበት መንገድ አንዱ፤ አንዷት ሃይማኖትን በማወጅና በመከተል ነበር ። በዚህም ምክንያት ከጎንደር ጀምረው ሸዋ ድረስ ዘምተው የሸዋን ሊቃውንት በጸጋ ሃይማኖት ስም አጥቅተዋል ። በዚህና በተመሳሳይ ድርጊታቸው "አጼ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ የሸዋን መኳንንት እጅ ነሥተው ሄዱ" ተብሎ በባለ ቅኔዎች ተገጥሞላቸዋል ፤

የአጼ ቴዎድሮስ የአንዷት ሃይማኖት ፖለቲካዊ ሂደት እንዳሰቡት ሀገር አንድ የሚያደርግ ሳይኾን የበለጠ እምቢተኝነትን ያሰፈነባቸው ኾነ ። በርግጥ የአጼ ቴዎድሮስ የሃይማኖት ፖሊሲ የሸዋን ሃይማኖት ለመደምሰስ ኾን ተብሎ የተደረገ አልነበረም ወይም ከሃይማኖት አክራሪነት ጋር የሚገናኝ አይደለም ፤ ይሁን እንጂ አጼ ቴዎድሮስ በሸዋ ሕዝቦች የሚወደዱ ታላቅ ንጉሥ ናቸው ፤ በራእያቸው መሠረት ሀገርን አንድ ለማድረግ በማሰባቸው ያደረጉት እርምጃ እንጂ የመሀል ሀገር ሰውን ለማጥፋት የሄዱበት እንዳልሆነ ሸዋዎች ራሳቸው ያውቁታል፤፤

ይሄ ድርጊት የተከናወነው የዘር ፖለቲካ ጽንፍ በያዘበት በአሁኑ ዘመን ቢኾን ኖሮ አጼ ቴዎድሮስ የሸዋን ዘር ለማጽዳት የወሰዱት እርምጃ ነው የሚል አንድምታ ያሰጣቸው ነበር ፤ ወይም የአጼ ቴዎድሮስ ዘመን የዘር ጥላቻ የነገሠበት ቢኾን ኖሮ አጼ ቴዎድሮስ የሸዋዎቹን እጅ ሲቆርጡ የሚያሳይ ሐውልት አንኮበር ላይ ይተከልልን በተባለ ነበር ፤ ግን አልተባለም ፤ ጎንደርና ሸዋም አልተከፋፈለም ፤ የቋንቋና የዘር መንግሥት እድሜ ቢያገኝ ኖሮ አንኮበር ላይ አጼ ቴዎድሮስ እጅ ሲቆርጡ የሚያሳይ ሐውልት ዘረኞቹ ማቆማቸው አይቀሬ ነበር ።

ከአጼ ቴዎድሮስ ዳግማዊ ቀጥሎ መንግሥታቸው ከሃይማኖት ግጭት ጋር የሚነሳው የአጼ ዮሐንስ አራተኛ ስም ነው ፤ እንደ ተክለጻድቅ መኩርያ አገላለጽ አጼ ዮሐንስ ፍጹም የካራ ( ኦርቶዶክስ አክራሪ) ሃይማኖት ተከታይ እስኪባሉ ድረስ በሃይማኖት ሀገር ለመከለል የሄዱበት መንገድ እንደ ግራኝ አሕመድ ያስከተለው የሰው ሕይወት መጥፋትን እንጂ ትርፍን አላመጣላቸውም ፤ በአጼ ዮሐንስና በግራኝ መካከል ያለው ልዩነት እስላምና ክርስቲያን የመኾን እንጂ በሀገሪቱ ላይ ያደረሱት ጥፋት ተመሳሳይና አቻ ኾኖ የሚታይ ነው ሲሉ ተክለ ጻድቅ መኩርያ ጽፈዋል ።

የአፍሪካ ጥናቶች ተመራማሪ የኾነው ጆን አቢንክ ሲናገር የሰሜን ወሎ ሙስሊሞች የሚባሉት የዛሬውን የራያን ሕዝብ እንደሆነና አጼ ዮሐንስ 3000 ሰላማዊ የራያ ሙስሊሞችን ወይም የሰሜን ወሎዎችን ለግዛት ማስፋፋት ሲሉ ጨፍጭፈዋል ብሎ በመግለጽ የሰሜን ወሎን ሙስሊም ራያ ከአማራነት ጋር አያይዞ ጽፏል ። ፤

የሸዋው ታላቅ ሰው ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ስለአጼ ዮሐንስ አማካሪዎቻቸው ሲገልጹ አጼ ዮሐንስ በራያ ሙስሊሞች ላይ ዘመቻ እንዲያደርጉ ያልተማሩ መነኮሳት እንደመከሯቸው ተናግረዋል ። በዚያም ሆነ በዚህ ፤ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ አጼ ዮሐንስ የነበራቸው የሃይማኖት ፖሊሲ ኢትዮጵያን አንድ ሊያደርግላቸው አልቻለም ።

ከአጼ ቴዎድሮስ ዳግማዊ የሃይማኖት መመርያ ፤ ከአጼ ዮሐንስም አራተኛ የካራ አዋጅ ይልቅ በሃይማኖት ፖሊሲያቸው የምናደንቃቸው ዛሬ የአድዋን በዓል ስናከብር የምንዘክራቸው ዳግማዊ አጼ ሚኒልክ ናቸው ። ለአድዋ በዓል ትልቁ መሠረት የኾነው ሰዎችን በሃይማኖት ሳይለያዩ ባላቸው ሰውነትና ኢትዮጵያዊነት ላይ የተመሠረተ የሃማኖት ፖሊሲ አጼ ሚኒልክ ነበራቸው ።

የሚኒልክ የሃይማኖት መመርያ የኢትዮጵያ ታሪክ መሠረቶች የኾኑ ኢትዮጵያውያን ኹሉ ነባር ሃይማኖታቸውን የሚተገብሩበትን መንገድ የሚያሳይ ነበር ፤ አጼ ሚኒልክ ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርት በመውሰድ ከእርሳቸው በፊት የነበሩት ነገሥታትን ስሕተት ላለመድገም በኢትዮጵያ የመንግሥት ምሥረታ ታሪክ ውስጥ ሃይማኖትም ኾነ እምነት ምን ያህል ሚና እንዳለው ስለተረዱ

"ኹሉም በአባቶቹ እምነት ይኑር በሀገሩ ግን አይደራደር::" በማለት የሃይማኖት መመርያ አወጥተዋል ። ከዚህ መመርያቸው የተነሣ ህዳር 2 ከወረ ኢሉ ጉዞ ጀምረው ታሕሳስ 4 ቀን አጼ ሚኒልክ አላማጣ ተራራ ግርጌ እንደደረሱ በዚያን ወቅት በሃይማኖቱ ሙስሊም በመኾኑ በአጼ ዮሐንስ ጥቃት የደረሰበት የራያ ሕዝብ በአባቶቹ ሃይማኖት እንዲኖር ስለፈቀዱለት በዕልልታና በአጀብ አጼ ሚኒልክን ተቀብሏቸዋል፤ ።

አጼ ሚኒልክ በግላቸው የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ ናቸው ፤ ነገር ግን ተዋሕዶዎች ብቻ ናቸው የሀገር ተቆርቋሪ የሚል አመለካከት ሚኒልክ የላቸውም ፤ በግላቸው ባላቸው እምነት በዋልድባ መነኮሳት መካከል የዘጠኝ መለኮት ትምህርት የሚያስተምሩ መናፍቃን እንዲወገዙ በመነኮሳቱ መካከል ጉባኤ አድርገው ራሳቸው መነኮሳቱ ጉዳያቸውን እንዲፈቱ አድርገዋል ።

አጼ ሚኒልክ ሃይማኖተኛም ከመኾናቸው የተነሣ ሩሀሩህ ነበሩ ፤ ለዚህም ማሳያ የሚኾነን የአድዋው ድል ከመታወጁ በፊት በመቀሌው ጦርነት በሊቀ መኳስ አባተና በደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ መሪነት የመቀሌውን የጠላት ምሽግ እያፈረሱ ሲታኮሱ እምዬ ሚኒልክ ትእዛዝ ይሰጡ እንደነበር ተጽፏል፤ እቴጌ ጣይቱ በበኩላቸው ከምሽጉ የሚወጣው ጠላት ወኃ እንዳያገኝ በውኃ ጥም እንዲሞት አዛዥ ዘአማኑኤልን አስጠርተው መክረዋል፤ በዚህ ምክር መሠረት የበውኃ ጥም እየተጠቃ የሚሞተው ጠላት ስለበዛ ኢጣልያዎች በማዦር ጋልያኖ በኩል በውኃ ጥም ማለቃችን ነው ብለው ቴሌግራም ወደ ሀገራቸው አስተላለፉ ።

በቴሌግራሙ ውይይት መሠረት በሐረር ይኖር የነበረ ካቫሊዬሬ የተባለ ኢጣልያዊ የቡና ነጋዴ አማላጅነት የኢጣልያ ወታደሮች በሕይወት ሳሉ የኢትዮጵያን ግዛት እንደሚለቁ ለአጼ ሚኒልክ ቃል ስለገባላቸው "በውኃ ጥም እንዲሞቱ ባይደረግ በሚል የድርድር ሐሳብ ስላቀረበ ሀገሬን በሰላም ለቃችሁ ውጡ በውኃ ጥም እንዳትሞቱ ተስማምቼአለሁ ነገር ግን ይህን ማድረጌ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልኩ የተዋሕዶ ልጅ በመኾኔ እንጂ ሌላ ምክንያት ኖሮ አይደለም" በማለት አጼ ሚኒልክ መልስ በመስጠታቸው ጠላት የኢትዮጵያን ግዛት እየለቀቀ ሸሽቷል ። አጼ ሚኒልክ በዚህ አነጋገራቸው በእግዚአብሔር የሚያምኑ የኦርቶዶክስ አማኝና ሰብዐዊነት የሚሰማቸው ሩሑሩሕ መኾናቸውን አሳይተዋል::

በሌላ በኩልም ከእርሳቸው ኦርቶዶክሰዊ ተዋሕዶ ሃይማኖተኝነት የተነሣም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በአድዋ ድል የነበራት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ▶

ነበር፤ ሁሉም የጦር ልዑላን የቃል ኪዳን ታቦታቸውን ይዘው ወደ አድዋ ተምመዋል ፤ ራስ መኮንን የቁልቢ ገብርኤልን ታቦት ይዘው ወደ አድዋ ተጉዘዋል ፤ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ወንጨ ውስጥ ያለችውን አዘር ማርያምን ፤ አዲስ አበባ ያለውን አራዳ መናገሻ ጊዮርጊስን ይዘው ወረ ኢሉ ደርሰው ወደ አድዋ ተጉዘዋል ። ለአብነት ያህል እነዚህን ጠቀስን እንጂ ክርስቲያኖቹ ልዑላንና የጦር መሪዎች ሁሉ ታቦት ይዘው ዘምተዋል ።

በየአድባራቱ የነበሩ ካህናት እጃቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው ይህን የቃል ኪዳን ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ ፈቃድ እንዲሆን የሚኒልክ መታሰብያ እንዲኾን ፈጣሪን ተማጽነዋል ።

በዘመኑ የነበሩ የአራዳ ጊዮርጊስ ማለትም የገነተ ጽጌ ጊዮርጊስ ሊቅ አዲስ አበባ ላይ ኾነው በመንፈስ አድዋ ድረስ ተጉዘው የጦርነቱ ድል ስለተገለጠላቸው መወድስ ቅኔ ተቀኝተዋል ፤ ከቅኔው መጨረሻ ቤት በግእዝ "በጽባሕ እስመ አቅረበ ሙስና ሮምያ መስዋዕተ ሠርክ ፡ " በአማርኛ "በጠዋት የሮምያ ኢጣልያን ጥፋት የኾነውን የሠርክ መስዋዕትን አቅርቧልና ።" ሲሉ የተገለጠላቸውን ምሥጢር ተናግረዋል ።

አጼ ሚኒልክ በሃይማኖት ፖሊሲያቸው ኹሉም በአባቶቹ እምነት ይደር ማለታቸው አንዱን ሃይማኖት ከሌላው ሃይማኖት አላስበለጡም፤ ይህም የኢትዮጵያን ሕዝቦች ያስተሳሰረ ፖሊሲ ነበር ፤ በእርሳቸው የሃይማኖት መመርያ ፈላሻ እየተባለ የሚገፋ አልነበረም ፤ ጋፋት እየተባለ የሚያንስ የለም ፤ ኹሉም ኢትዮጵያዊ በሚል ማእቀፍ ሃይማኖቱ ተጠብቆለት የኢትዮጵያዊነት ስሜቱ የሚያኮራው ነበር ፤ ኢትዮጵያዊ ኾኖ ፕሮቴስታንት መኾን እንደሚቻል የአጼ ሚኒልክ የሃይማኖት ፖሊሲ ያሳያል ። መሠረቱ ኢትዮጵያ ይሁን እንጂ የትኛውንም ሃይማኖት ቢከተል አማራጭ የሰጡ የነጻነት መሪ አጼ ሚኒልክ ነበሩ፤ ኢትዮጵያዊ መሠረት ያለው ሙስሊም ፤ ፕሮቴስታንት ፤ ካቶሊክ፤ ዋቄንፈታ ወዘተ የመሳሰሉት ሀገራዊ ስሜት እንዲኖራቸው ያወጁ ንጉሠ ነገሥት እምዬ ሚኒልክ ናቸው ። ለዚህም ማስረጃነት የእምዬ ምኒሊክን ጀግንነት ሰምተው ቤተ ክርስቲያናቸውን የአቢሲኒያ ቤተ ክርስቲያን ብለው የመሰረቱ የውጭ ዜጎችና ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ወንጌላውያን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን እንደመሠረቱ ዶናልድ ሊቨን ጽፈዋል ።

በአጼ ሚኒልክ የሃይማኖት መመርያ ኢትዮጵያዊ ኾኖ ሙስሊም መኾን እንደሚቻል በአባ ጂፋር ሹመትና ስልጣን ማወቅ ተችሏል ። አባ ጅፋርና ጦራቸው በተለያየ የውስጥ ጉዳይ ከአጼ ሚኒልክ ጋር ክርክር ቢኖርባቸውም በአድዋው ጦርነት ጊዜ ሀገረ መንግሥት አዲስ አበባን እንዲጠብቁ ዋስትና የተሰጠው ለጅማ አባ ጅፋርና ሠራዊታቸው ነበር ፤

አጼ ሚኒልክ ሙስሊሞችን የሀገር ታማኝና ጠባቂ በማድረጋቸው ማለትም ኹሉም በአባቶቹ ሃይማኖት ይኑር በሀገሩ ግን አይደራደር የሚለው ሥርዓታቸው በሕዝቡ ዘንድ መስረጹን አመላካች ነበር ።

ከዚህም ሌላ የሚኒልክን የሃይማኖት መመርያ ለየት የሚያደርገው "ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም" በሚል በሚታወቀው የአድዋ ጦርነት የክተት ዐዋጅ ላይ የሸዋን ጦር ክተት ያሉበት ታሪካዊ ቦታ ወረኢሉ መኾኑ ነው ። አጼ ሚኒልክ የጥንት አባቶቼ ርስት ናት ብለው ወረኢሉን ታሪካዊ ስፍራ ላይ ያስቀምጧታል።

ወረኢሉ ብዙ የስም መፈራረቅ ደርሶባታል ፤ በአጼ ዘርዐ ያእቆብ ዘመን እስከ ንብለ ድንግል ድረስ ስሟ ባዶቄ አንዳንዴ ደግሞ ዋሲል ይባል ነበር ፤ በዚህ ቦታ ላይ ቀድሞ የግራኝ አሕመድ ወረራን ለመቋቋም አጼ ንብለ ድንግልም ከሸዋ ልዑላንና ከትግራይ መሳፍንት ጋር የተማማሉባት ቦታ ናት ። በዚሁ መሃላ መሠረት በባዶቄ/ወረኢሉ ጦርነት ላይ የግራኝን ወታደሮች ለማጥፋት ተጋድለው ካለቁት መካከል የትግሬ ጦረኞችም ይካተቱበታል ። ለዚህም ይመስላል ፤ግራኝ አሕመድ ያሳደደውን የሸዋን ሰው ንጉሠ ነገሥት ንብለ ድንግልን ያስጠጋ የትግራይ ደብረ ዳሞ ገዳም ለሸዋ ሰውና ነገሥታት ባለውለታ መኾኑን ሸዋዎች በተለይም አጼ ሚኒልክ አልዘነጉትም ።

ተመሳሳይ የታሪክ ድግግሞሽ መምጣቱ ተፈጥሯዊ ክስተት በመኾኑ በአድዋ ጦርነት ዋዜማ አጼ ሚኒልክ ለትግሬዎች ያላቸው ፍቅር የተለየ ነበር ለዚህም ነው ለመጀመርያ ጊዜ የጠላት ጦር መሪ ባራቶሪ ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ የትግራይን ግዛት ወረረ የሚል ቃል በግእዝ "ተሞዐ መንገሻ ወተፈትሐ አንቀጸ አበሻ" በአማርኛ "መንገሻም ተሸነፈ የኢትዮጵያም በር ተከፈተ" የሚል መርዶ ነጋሪ ለአጼ ሚኒልክ ቢነግራቸው "ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም" በሚል የሚታወቀውን ዓዋጃቸውን በማወጅ የሸዋ ሰው ጦርነቴ በጥቅምት ነውና እስከ ጥቅምት እኩሌታ ወረኢሉ ከተመህ ጠብቀኝ አሉት ።

ወረኢሉ ታሪካዊ የአንድነት ተምሳሊት ናት የአዋጁ ማጠንጠኛ ማርያም የሚለው ስም መኾኑ ደግሞ ሌላ ኃይል አለው ። ይህ ስም እንደ ወንጌላውያኑ የኢየሱስ እናት በማለት የሚያውቋት እንደስሊሞቹ ደግሞ አልመሲሁ ኢሳ እናት መጠርያ ነው ፤ በቁርዓን አልመሪማ የሚል ምዕራፍ የተሰጣት ፤ በካቶሊክ ዘወትር የማትረሳ በተዋሕዶ ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ የምትመሰገን አማላጅ፤ ባጠቃላይ የስሙ ባለቤት በታሪከ ነገሥት ኢትዮጵያ የድንግል ማርያም የዐሥራት ሀገር ናት የሚል መዝገብ ያላት ናት ፤ ስለዚህ በኢትዮጵያ ጉዳይ የድንግል ማርያም ስም መጠራቱ በወቅቱ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የማሳሳብ መንፈሳዊ ኃይል ስላለው ነው ። የአጼ ሚኒልክ የመጨረሻ ቃል ማርያም የሚለው ደግሞ ሸዋዎች በወቅቱ የአምልኮ ማጠንጠኛቸው ማርያም ናት የሚል "ምስለ ወልዳ" የሚል አስተምህሮን የሚከተሉ ስለነበር በተለይ ለነሱ አጽንዖት ለመስጠት ነበር ።



በማርያም ስም በወረኢሉ የተሰባሰቡት ኢትዮጵያውያን ኹሉ ኦሮሞው ፤ ጉራጌው አማራው ደቡቡ የተባበረበት ፤ ሰባት ቤት ወሎ የተማማለበት የቃልኪዳን ምድር ወረኢሉ ናት ። የኦሮሞው፤ የጉራጌው የአማራው ባጠቃላይ የሙሉ ሸዋ የጦር የተመመበት የሸዋ ልዑላን ምክር የጸደቀበት ፤፤ የትግራይ ገዢዎች መንገሻ ዮሐንስና አሉላ አባ ነጋ የእምዬ ሚኒልክ ወዳጆች ከመኾናቸው ባሻገር የኢትዮጵያዊነት መሠረት ለመጣል አስቀድመው የተማማሉበት ቦታ ወረኢሉ ነው ፤ የጎንደርና የጎጃም ጦር ተሸግሮ ታሕሳስ 15 ቀን መሐን ዘንባ የተባለ ቦታ ላይ እንዲገናኙ ቀጠሮ ያስተላለፉበት ቦታ ወረኢሉ ነው ።

የድል ሁሉ ድል የኾነው የካቲት 23 ቀን ታላቁ የአድዋ ድል የተፈጸመው አስቀድሞ በዚህ ቦታ በተፈጠረው አንድነት ነው፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ድል በኃላፊነት የምትዘክረው ነው ። ይልቁንም ፈቃደ ሥላሴ የተባለ የጎጃም ሊቅ ለሌሎች ቅዱሳን ኹሉ እንደሚደረሰው ከስም አጠራራቸው ጀምሮ እስከ ሰውነት ክፍሎቻቸው እያነሳ የአጼ ሚኒልክን መልክእ ደርሷል ለመልክኡም መልክአ ዘሚኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሚል ርእስ ሰጥቶታል ። የአድዋን ድል አስመልክቶ በመልክአቸው ውስጥ ጀግንነታቸውን አመስግኗል ። ከመልክኡ መካከል በ4ኛ ተራ ያለውን "ሰላም ለገጽከ ከመ አንበሳ ዘገዳም" የሚለውን በግእዝ ቢኾንም በአማርኛ ተርጉሜ ሙሉውን ለምሳሌ ያህል ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

(4) ልክ እንደ ዱር አንበሳ ለኾነው ለፊትህ ሰላምታ ይገባል፤

በሰም እንደተወለወለ ጌጥ እይታው የሚያብረቀርቅ ነው

ዙፋንህ የሚያስገርመው የነገሥታት ንጉሥ ሚኒልክ ሆይ!

ከሮም ሀገር የመጣውን ወራሪ ገደልከው ።

ይህ የአጼ ሚኒልክ ሙሉ መልክአ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ከጻፉት የአጼ ሚኒልክ ዜና መዋዕል ጋር እንዲነበብ ሥርዐት እንዳለው የመልክኡ ድርሰት ይዘት ይናገራል ። በዚህ ጉዳይ ክርክር የሚያነሱ ሰዎች እንደሚኖሩ ቢታወቅም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጼ ሚኒልክንና የአድዋን ድል ነጥላ የማትመለከት በመኾኑ መልክእ እንኪደረስላቸው ድረስ የምታከብራቸው መኾኑን ማሳያ ነው ። አጼ ሚኒልክ ከእርሳቸው በፊት ከነበሩ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ነገሥታት ይልቅ ለኹሉም ሃይማኖቶች ነጻነት የሰጡ በመኾናቸው ኹሉም ኢትዮጵያዊ ያመሰግናቸዋል፤

ይሁንና ደግሞ ለሃይማኖቱች ኹሉ እኩልነትና የሃይማኖት ነጻነት የሰጡ ታላቅ ንጉሥ ቢኾኑም በአንጻሩ እንደ አማኝነታቸውና እንደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የበላይ ጠባቂነታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታከብራቸው ከሁሉም ይልቅ በከፍተኛ ደረጃ መኾኑን በእርሳቸው መሪነት የተከናወነው የአድዋ ድልና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተዋጽኦ ያስረዳናል ። ይቆየን …

"ኵሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንዑ"

ገለቶማ !!!

ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

የጥንታዊ ቋንቋዎችና ጽሑፎች ተመራማሪ

# አድዋ <<የአፍሪካውያን የድል ቀን>> አፄ ምኒልክ <<የአፍሪካ የነፃነት አባት>>



ሁሴን ከድር

....ዋ!

ዓድዋ የዘር ዐፅመ ርስትዋ

የደም ትቢያ መቀነትዋ

በሞት ከባርነት ሥርየት

በደም ለነፃነት ሥለት

አበው የተሰውብሽ ዕለት

ዓድዋ

የኩሩ ትውልድ ቅርስዋ

የኢትዮጵያነት ምስክርዋ.....

ጸጋዬ ገ/መድኅን እሳት ወይ አበባ 1966

ዛሬ የአፍሪካውያን የድል ቀን ነው፡፡ ከ123 ዓመታት በፊት አንገታችንን ቀና ያደረግንበት፣የውርደትን ማቅ ገፍፈን የጣልንበት የነፃነት ቀን፡፡ ንፉግነት ካልሆነ ድላችንን የግላችን ማድረጋችን ተገቢ አይመስለኝም፡፡ የሰው ልጆች መገኛ አድርገን ለዓለም የተዋወቅን ሕዝቦች፣ በቋንቋ አጥኚዎች ዘንድ የሴሜቲክ ቋንቋ መገኛ እንደሆንን የሚነገርልን ሕዝቦች፣በዓለም የቀደምት ሥልጣኔ ባለቤቶች፣የራሳችን ፊደል ያለን ሕዝቦች ....ምነው አድዋ ላይ ድሉን የራሳችን ብቻ በማድረግ አፍሪካን ዘነጋን?

የአድዋ ድል የኢትዮጵያውያን በሙሉ ድል መሆኑ እሙን ነው፡፡ አጼ ምኒልክ በየወሰናቸው ተብቃቅተው ይኖሩ የነበሩ ጠወቃቅን ንጉሶችን በግድም ይሁን በውድ ካሰባሰቡ በኋላ የመጣ መዓት በመሆኑ፤ መዓቱን በጋራ ክንድ ተባብረን እናስወግደው የሚል ጥሪ አድርገው በሚኒልክ ግዛት ሥር ያደሩ በሙሉ ሥንቃቸውን ቋጥረው መሳርያቸውን ተሸክመው ጋዛቸውን በአጋሰስ ጭነው በሕብረት መከራቸውን ለመገዳደር የተመሙበት ጦርነት ነበር፡፡ የጎጥ፣የዘውጌ ፖለቲካ አራማጆች የሚያፍሩበት አንድነት ቢኖር አድዋ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከሰሞኑ በአድዋ ላይ ያተኮሩ በርካታ መጽሐፍትን አነበብኩ፡፡ ሃበሾቹም ፈረንጆቹም በአንድ ቃል የኢትዮጵያውያንን ሕብረት፣ያለ ጦር ስልት እውቀት በብዛት በመሆን የጠላትን ምሽግ በሆታ በወኔ ጥሰው በመግባት ዘመናዊ የጦር መሣርያ የታጠቀውንና የሰለጠነውን የፈረንጅ ጦር አርበደበዱት፡፡ ከምሽጉ አስወጥተው ከፊል ማርከው፣ ከፊል ገድለው፣ ከፊሉን አባረሩት፡፡ በአምባላጌም በአድዋም ሀገር ነቅሎ ወጥቶ ሹምባሹን፣ነጫጭባውን፣ባንዳውን እንዲፈረጥጥ አደረጉት እያሉ ነው አፋቸውን አንድ ያደረጉት፡፡

‹‹...የኢትዮጵያ ወታደር ረኸሙን የወራት መንገድ በእግሩ ተጉዞ፣የራሱን ጥራጥሬ እህል በልቶ ንጹሕ ውሃ ተጎንጭቶ ከባሕር ማዶ በባቡርና በመርከብ ተሳፍሮ የመጣውን ድርጅቱ የተሟላውን ፣በጦር ትምህርት ቤት የሰለጠነውን በማናቸውም ምቾት ያልተለየውን የፈረንጅ ወራሪ ተዋግቶ በማሸነፍ አገሪቱን ከባርነት ውርደት በማዳን ለሚመጣው ትውልድ አኩሪና አስመኪ ታሪክ አወረስ፡፡›› ይላሉ ተክለጻድቅ መኩሪያ ‹‹በአጼ ምኒሊክና የኢትዮጵያ አንድነት›› መጽሐፋቸው በገጽ 229

ሌሎች የታሪክ ጸሐፊያንም ወደረኛ ሓሳባቸውን ያስነብቡናል፡፡ ‹‹አድዋ›› ታሪክ፣ሥነጽሑፍ፣ፖለቲካ፣ ጦር ያሰናሰሉት ክስተት ነው፡፡ ይህንን ታላቅ ዋጋ የከፈልንበትን ታሪክ ባለፉት 123 ዓመታት አፍነን ቁጭ ብለናል፡፡ የአፍሪካውያን ኩራት፣የጀግንነት ተምሳሌት ሳናደርግ ጨምቀን ጉያችን ወሽቀነዋል፡፡ ሌሎች አገራት ጥቃቅን የድል ታሪኮቻቸውን አግዝፈው ለመተረክ በርካታ ጥራዞችን፣በርካታ ብሩሾችን በሸራዎች ላይ ይጨርሳሉ፡፡ በሲኒማ፣በቪዲዮ ታሪክ ያኖራሉ፡፡ በሙዚየሞች ያሳለፏቸው የታሪክ ቁሶች ተሰቅለው ትውልድ እንዲጎበኘው ያደርጋሉ፡፡ አልባሳቶች ፣መጫሚያዎች፣መመገቢያ ቁሶቻቸው በሙሉ ትውልድ እንዲያየው ለኤግዚቢት ያቀርባሉ፡፡ እኛ ዛሬም መንቃት አልቻልንም፡፡

ባለፈው ዓመት ‹‹አድዋ ዩንቨርሲቲ›› ትግራይ ላይ የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ተብሎ እንደሚከፈት ሰምተን ነበር፡፡ ምናልባት በአፍሪካ ደረጃ ከሰራነው ሥራ አንዱ ይሕ ቢሆን ነው፡፡ ሌላ ካለ ለመታረም ዝግጁ ነኝ፡፡ እስካሁን ባለኝ መረጃ ግን ምንም ነገር አላየሁም፡፡ ዛሬም ‹‹አድዋ ሙዚየም›› የለንም፡፡ በሙዝየሙ ልናኖራቸው የሚገቡ፡- አያት ቅድመ አያቶቻችን የተዋጉበት የጦር መሣርያ፣ጋሻ፣ጦር፣የዘመኑ መድፍ፤ የዘመኑ አልባሳት አላሰባሰብንም፡፡ በወቅቱ በጦርነቱ ከመላው ኢትዮጵያ የተሰባሰቡ ከ120ሺህ በላይ ወታደሮች (ቁጥሩ ላይ ሁሉም ጻሐፊዎች ከግምት የዘለለ ያስቀመጡት ትክክለኛ መረጃ የለም) የተመገቡበት ሳህን፣የጠጡበት ጣሳ.... ተሰባስቦ አልተቀመጠም፡፡ በየአያቶቻችን ቤት የተቀመጡ የጦር ልብሶች ወደፊት ለምንመሠርተው ‹‹የአድዋ ሙዝየም›› ብለን የማሰባሰብ ሥራ እየሠራን አይደለም፡፡ የባሕል ሚኒስትር፣አርበኞች ማኅበር ሌላም ጉዳዩ የሚመለከተው በዚህ ረገድ ሊያስብበት ይገባል፡፡

ቱርክ ከ1400ዓመታት በፊት ነብዩ ሙሐመድ(የአላህ ሰላምና እዝነት ይስፈንባቸው) ይገለገሉባቸው ነበር ተብለው የሚታመኑባቸው አልባሳት፣መጫሚያ ከየአገሩ በመሰብሰብ በሙዚየሞቿ በማኖር የገቢ ማግኛ መንገድ አድርገዋለች፡፡ ግብጽ ነብዩ ሙሐመድ ከሐበሻው ንጉሥ ነጃሺ ጋ የተጻጻፏቸውን ደብዳቤዎች በመያዝ የታሪክ ሽሚያ አድርጋላች፡፡ እኛ ዓለምን ያስገረመ ጀግንነት ያተረፍንበትን የአድዋ ድል የመዘከርያ ሙዝየም አልገነባንም፡፡ በሀገራችን ምን ያህል ‹‹አድዋ›› ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ? ልጆቻችን ስለ አድዋ ታሪክ የሚማሩበት ጥራዝ በምን ያህል መጠን አዘጋጅተናል?..... በርካታ ሥራዎች ይጠብቀናል፡፡

ከሁሉም በላይ አድዋን የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ፣ አጼ ምኒሊክን የአፍሪካ የነጻነት አባት አድርገን በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ ይህን እውነታ ገፍተን እስከሰራንበት ድረስ የአፍሪካ አገራት ከመቀበል ወደኋላ የሚሉ አይመስለኝም፡፡ አብዛኞቹ የአፍሪካ አገራት ባንዲራ ከአድዋ ድል በኋላ ወደ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሕብር መለወጣቸው የታሪክ እውነታ ነው፡፡ የአፍሪካ አገራት ከአድዋ ድል በኋላ በነጭ ወራሪዎቻቸው ላይ አምጸው የነጻነት ንቅናቄያቸውን ከዳር ለማድረስ ወኔ እንደሰነቀላቸው እሙን ነው፡፡ ታዲያ አጼ ምኒልክን ‹‹የአፍሪካ የነጻነት አባት›› የአድዋ ድልን ‹‹የአፍሪካውያን የነጻነት ቀን›› ብለን በአፍሪካ ሕብረት እውቅና ለማስጥጠት ምን ያግደናል?

ሁሉም ነገር በአንድ ጀንበር አይሆንምና የአድዋ ድልን የዩኒቨሪስቲዎቻችን የታሪክ ምሁሮች በአፍሪካ አገራት በሚታተሙ ታላላቅ ጋዜጦች ላይ ቢጽፉ፣በአፍሪካ በሚታተሙ የጥናትና የምርምር መጋዚኖች ደረጃቸውን የጠበቁ ተጠቃሽ ሊሆኑ የሚችሉ ጥናታዊ ጽሑፎችን ቢያሳትሙ፣ በአፍሪካ አገራት ያሉ ኤንባሲዎቻችን በየሀገራቱ ያሉ ተጽእኖ ፈጣሪ ምሁራንና ተደማጭ ሰዎችን በመሰብሰብ መድረኮች አዘጋጅተው አድዋን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራና ጥናታዊ ጽሑፎች የሚቀርቡበትን ሁኔታ ቢፈጥሩ፣ ብሎም እነዚህ ሥራዎች በየሃገራቱ ብሔራዊ ጣቢያዎች እንዲቀርቡ ቢያመቻቹ፣ ሰዓሊያን በአፍሪካ በሚኖሩ የሥዕል ማቅረቢያ ጋለሪዎች የአድዋን ጀግንነት የአፍሪካውያን ኩራት መሆኑን ሊያሳዩ የሚችሉ ሥራዎች ሥለው እንዲታዩ ቢያደርጉ፣ የሙዚቃ ባለሙያዎች አድዋ የአፍሪካውያን ድል እንደሆነ ሊያሳዩ የሚችሉ ሥራዎችን ሠርተው በአፍሪካ ዓመታዊ ውድድሮች ላይ ቢያስደምጡ፣ በአፍሪካ ታዋቂ የሆኑ የሙዚቃ ባለሙያዎች ስለ አድዋ እንዲዘፍኑ ግጥሞች ተሰርተው ቢሰጣቸው..... ሌላም ሌላም


በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ አህጉራዊ ታሪክ መለወጥ የሚከብደን አይሆንም፡፡ ይህ ሁሉ ቅንነት፣ ሕብረትና የአገር ፍቅር ወኔ እስካዳበርን ድረስ የሚሳካ ይሆናል፡፡ በአፍሪካ ሕብረት አደራሽ የአጼ ምኒሊክን ሃውልት ማቆምም ይከብዳል ብዬ አላስብም፡፡

እያንዳንዱ አገር የየራሱን ጀግና ይፈጥራል፡፡ አሰባሳቢ አባትም ጭምር፡፡ አጼ ምኒሊክ ከቀደምት ነገስታት በተሻለ የአባትነትና የአሰባሳቢነት ሚናን ተጫውተዋል፡፡ እንንቀስ ካልን ስህተት የምንነቅስበት መሪ አንድም አናገኝም፡፡ ከአጼዎቹም፣ከጓዶቹም፣ከአቶዎቹም፣ከዶክተሮቹም አስተዳደራዊ በደል ደርሷል በሚል መዘርዘር እንችላለን፡፡ አጼዎቹ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ስላደረሱት በደል ብናወጋ ወራት አይመልሱንም፡፡ ትናንት ታሪክ ሆኖ አልፏል ዛሬ እውነት ሆኖ እየኖርን ነው፡፡ ነጋችን ያማረ፣ልጆቻችን የሚደሱበት አገር የምንፈጥረው ትናንትን በማንኳሰስ ሳይሆን ዛሬን ከትናንት ስህት ተምረን በመሥራት ነው፡፡ ለልጆቻችን ታላቅዋን ኢትዮጵያ ለመገንባት እንነሳ፡፡ ጀግናችንን እንፍጠር፡፡ በአድዋ መነሻነት አጼ ምኒልክን የጋራ አባታችን አድርገን ለአፍሪካ ብሎም ለዓለም እናስተዋውቅ፡፡ የጥላቻ ወሬን ካልገደልን እያገነገነ ራሳችንን ጠልፎ ይጥለናል፡፡

በሕዝቦቿ መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተችው ኢትዮጵያ አድጋ፣ በልጽጋ፣ እንድናያት ፈጣሪ ይርዳን፡፡ መልካም የአድዋ በዓል፡፡

እንኳን ለግዮን አንደኛ ዓመት አብሮ አድረሰን!!!

# የአፄ ምንሊክና የእቴጌ ጣይቱ
## የማዘዣ ሰፈር በወሳኟ ዕለት


ብሩክ መኮንን



የውጫሌ ውልን በተመለከተ በጊዜው አለቃ አፅሜ የተባሉ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚያውቁ ኢትዮጵያዊ፣ ለአፄ ምንሊክ በአማርኛ እና በኢጣልያንኛ የተፃፈው የውሉ ሰነድ የአንቀፅ 17 ልዩነትን ለምንሊክ በሚገባ አስረዷቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ምንሊክ በጊዜው በኢትዮጵያ የኢጣልያ ወኪል የነበረውን ሶንቶ አንቶሊን፡- "የተዋዋልነው ውል የማታለልና የማጭበርበር ነገር አለበት ይሉኛል፣ እኔ ግን አንተን አምኜህ ነበር፣ ምነው እንዲህ አደረግህ?" ብለው ሲጠይቁት፡፡ ጉዳዩን ከማስተባበል አልፎ ይህንን መረጃ የሰጡት አለቃ አፅመ ጊዮርጊስን "የሁለቱ ሀገራት ወዳጅነት ላይ እያሴሩ ናቸው" በሚል በመወንጀል አፄ ምንሊክ በእስራት እንዲቀጧቸው ለማድረግ ችሎ ነበር፡፡

ከአመታት በኋላ አለቃ አፅሜ እንደተናገሩት የውጫሌ ውል በኢጣልያኖች በተቀነባበረ መልኩ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የሚያሳጣ መሆኑ ሲረጋገጥ አፄ ምንሊክ አለቃ አፅሜ ጊዮርጊስን ከታሰሩበት ድረስ በመሔድ "ስለ ሀገርህና ለእኔ ስትል የነገርኸኝን ምክር አልሰማ ብዬ በሐሰት እንድትታሰር አድርጌሀለሁ፣ ስለ በደልኩህ ማረኝ" ብለው ይቅርታ ጠይቀዋቸዋል፡፡

በቦታው የነበሩት እቴጌ ጣይቱም "አፅመ ጊዮርጊስ ቢታሰርም፣ ቢፈታም ለሀገሩ የሚገባውን ሠርቶ ነው፡፡ ለመሆኑ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው ዮሴፍ ጣልያኖች በተንኮል ገብተው በማታለል፣ ይኼንን ሁሉ ሲፈፅሙ አስተርጓሚ ሆኖ እንዴት ሳያስጠነቅቅ ቀረ?" ብለው በመግለፅ ዮሴፍና ሌሎች አስተርጓሚዎች ከኢጣልያኖች ጋር የውጭ ኃይሎች ተልዕኮ አስፈፃሚ እንደነበሩ አጋልጠዋል፡፡

ከአድዋ ጦርነት በፊት በአምባላጌ ላይ ከኢጣልያን ጦር ጋር በተካሄደው ጦርነት በድንገት ማጥቃት የጀመሩት ፊታውራሪ ገበየሁን ራስ መኮንን ሳያማክሯቸውና ሳያስፈቅዱ መዋጋታቸውን በመቃወም ከድሉ በኋላ ምንሊክ አስረዋቸው ነበር፡፡ሁኔታውን የሰሙት እቴጌ ጣይቱ በጉዳዩ ላይ ከራስ መኮንን ጋራ ባደረጉት ውይይት "ገበየሁ ለጌታዬ የጦር ድግስ አላቆይም" ብሎ ጠላቱን ተዋግቶ ድል ባደረገ ያሰርከው፣ ድል ቢሆን ኖሮ ትገድለው ነበር?" ብለው በመጠየቃቸው "ራስ መኮንንን ስንማከር፣ ሳያስፈቅድ ስለ ተዋጋ በደንብ መተላለፍ ነው የታሰረው" ሲሉ መለሱላቸው፡፡እቴጌ ጣይቱም "እርሱ ሲዋጋ አንተ ጠላት ሲሠራው በነበረው አጥር ጭቃ ታቀብል ኗራል" ሲሉ መናገራቸውን በጊዜው የነበሩ የአይን ምስክሮች ተናግረዋል፡፡

የአድዋ ድል ለመገኘቱ ዋነኛው ምክንያትም እቴጌ ጣይቱ ብጡል ለጠላት ወገን የተሳሳተ መረጃ እንዲደርሰው ለማድረግ ባሻ አውአሎም ሐረጎት የተባሉ ሰውን በመጠቀም ለኢጣልያን ጦር አዛገቶች "በዕለተ ጊዮርጊስ ወታደሩ ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም፣ ስንቅ ለመፈለግ በየአቅጣጫው ተበታትኗል" በማለት የጣልያን ጦር ከምሽግ ወጥቶ ወደ ንጉሱ ወደሠፈሩበት ጉብታ ቢያመራ ንጉሰ ነገስቱንና እቴጌይቱን በቀላሉ ሊማርክ ይችላል የሚል የተሳሳተ መረጃ እንዲደርሰው በማድረግ የተገኘ ድል እንደሆነ ታሪክ ፀሐፊዎች ይናገራሉ፡፡

የአፄ ሚኒልክና የእቴጌ ጣይቱ የማዘዣ ሰፈር በወሳኟ ዕለት በውጋገን የተሞላው የአድዋ ሰማይ ላይ በደመና የተጀቦነችው ፀሐይ በምስራቅ አድማስ በኩል ገና እየወጣች፣ ጎህ እየቀደደ ቢሆንም ወፎች እንኳ መንጫጫት አልጀመሩም፡፡

በዚህን ድንግዝግዝ ያለ ብርሃን እየተረዱ ወደ ኢትዮጵያውያኑ ጦር ሰፈር የሚገሰግሱ በሜጀር ትሪቶሪ የሚመሩ ወታደሮች ሳያውቁት ወደ ኢትዮጵያውኑ የጥበቃ ቀጠና ውስጥ ደርሰው ነበር፡፡ በጥበቃ ላይ ያሉ የምንሊክ ወታደሮች እነዚያን ያልተጠበቁ የኢጣልያ ወታደሮችን በድንገት የጥበቃ ክልላቸውን አልፈው ሲገቡ በማየታቸው ተኩስ ከፈቱባቸው፣ በዚህ ጊዜ ሰዓቱ ልክ ከንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ከሆነ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነበር ያለፉት፡፡ በዚህች ቅፅበት ነበር የአድዋ ጦርነት የተጀመረው፡፡

በወቅቱ ኢትዮጵያውያን ጣልያውያኑ ወረራ ለመፈፀም ከሰፈሩበት አድዋ ድረስ ይመጣሉ ብለው እየጠበቁ እንደነበሩ የሚገልፅ ምንም አይነት ማስረጃዎች አልተገኙም፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያውያኑ ስለ ኢጣልያ ጦር እንቅስቃሴ ምንም ዓይነት መረጃ አልነበራቸውም፡፡ በ1930 ሩይልፎ ማዙንኩኒ ስለ አድዋ ጦርነት በፃፈው መፅሐፍ ላይ ምንሊክና ጣይቱ የኢጣልያ ጦር እየገሰገሰ ወደ አድዋ መምጣትና ተኩስ መክፈት የሰሙት በቤተ ክርስቲያን በፀሎት ላይ እያሉ መልዕክተኛ ተልኮባቸው እንደሆነ በእርግጠኝነት አስፍሯል፡፡

አንድ ስሙ ያልተጠቀሰ ኢትዮጵያዊ የአይን ምስክር በበኩሉ ምንሊክና ጣይቱ ከሌሊቱ አስር ሰዓት ጀምሮ በቤተክርስቲያን ፀሎት ላይ እያሉ ነው የኢጣልያን ጦር ወደ አድዋ መድረሱን የሚገልፀው መልዕክት የያዘ መልዕክተኛ ያገኛቸው ብሏል፡፡መልዕክተኛው ለምንሊክ ወደ ጆራቸው ተጠግቶ መልዕክቱን ነገራቸው፡፡ በሚገርም መልኩ ምንሊክ መልዕክቱን ከሰሙ በኋላ ሙሉ ትኩረታቸውን ወደ ቅዳሴና ፀሎታቸው በመመለስ ትኩረታቸውን ሰጥተው ከቆዩ በኋላ ፣ የቅዳሴው ስነ ስርዓት እንደተጠናቀቀ በቤተ ክርስቲያን አብረዋቸው ለነበሩ የጦር አዛገቻቸው የደረሳቸውን መልዕክት በመንገር ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ራሳቸውም ለውጊያው መዘጋጀት ጀመሩ፡፡ ይህ የሆነው ከንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት ከሰላሳ ላይ ነበር፡፡

በሁለቱም በኩል ይህ ስሙ ያልታወቀ የአይን ምስክር የተናገረው ምስክርነት ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ምክንያቱም ምኒልክና ጣይቱ ወደ ቤተክርስቲያን በማምራት በፀሎትና የቅዳሴ ስነ ስርዓት ላይ እንዲገኙ ያደረጋቸው፣ ኢጣልያውያን ደግሞ በግብታዊነትና በስሜት ተነድተው በአድዋ በሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር ልዩ ማጥቃት እንዲጀምሩ ያደረጋቸው የመረጃ ምንጮቻቸው በነበሩት ሰላዮቻቸው የተሳሳተ መረጃ ስለደረሳቸውና በዚህ መረጃ ተመስርተው ባደረጉት ምክንያት ለሽንፈት መዳረጋቸውን በቀላሉ መገመት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያውያኑ የተከፈተባቸውን የማጥቃት ዘመቻ ለመመከት የሚያስችል በቂ ጊዜ ስለነበራቸውና በቂ ዝግጅት ▶

በማድረጋቸው ሽንፈቱ በኢጣልያ ላይ ሊደርስ ቻለ ይላሉ፡፡ ማንነታቸው ያልተገለፀ ምስክሮች ቢሆኑም የሚገርመው ደግሞ በምንሊክ የስልጣን ዘመን ፀሐፊ ትዕዛዛቸው የነበሩ ሰውም ያንን የጦርነት አጀማመር ቅፅበትን የሚያሳይ ምንም መረጃ አልተውልንም፡፡ በተወሰነ ደረጃ ስለወቅቱ መረጃ የሚሰጡን ዮሴፍ ንጉስ የተባሉ ምንሊክን በአስተርጓሚነትና በፀሐፊነት የሚያገለግሉት ሰው፣ ለአልፍሬው ኢልግ ስለ አጠቃላይ ጦርነቱ አጀማመር ሂደቱን በተመለከተ በዝርዝር በፃፉለት ደብዳቤ ላይ "ጦርነቱ የተጀመረው ከትሪቶሪ የሚታዘዙ ወታደሮች ተኩስ በመክፈታቸው የኢትዮጵያ ጦር የአፀፋ ተኩስ ምላሽ ሰጠ፡፡ በዚህ ወቅት ምንሊክ ልክ የታሰረበትን የብረት ሰንሰለት በጥሶ የወጣ አንበሳ በሚመስል ግርማ የተላበሰው ሠራዊታቸው በጀግንነት ሊፋለም ከየአለበት ተንቃሰቀሰ" ብለዋል፡፡

ወደ አድዋ ጦሩን ይዞ የገሰገሰው ሜጀር ትሪቶሪ ከነሠራዊቱ በአድዋ ከፍተኛ ኮረብታዎች አንዱ ላይ ቢደርስም የሚገኝበት አጠቃላይ ሁኔታ አደጋ ውስጥ መሆኑን የሚያሳይ አንዳችም ምልክት የለውም፡፡ በትሪቶ የሚታዘዘው ጦር ከዋናው የጄነራል አልቤርቶኒ ጦር ከሌላ ድጋፍ ሰጪ ኃይል በአንድ ማይል ከግማሽ ርቀት ቀድሞ ነው የሚገኘው፡፡በድንገት የተጀመረው የተኩስ ልውውጥ እየተበራከተ ከሁለቱም ወገን የሚተኮሰው ጥይት አለት እየመታ በየአቅጣጫው ሲፈነጣጠር የተኩሱን ድምፅ የአድዋ ተራሮች እየተቀባበሉ ሲያስተጋቡ በኢትዮጵያውያኑ ጦር ሰፈር ያለ ሠራዊት ሰምቶ ትጥቁን እየያዘ ትዕዛዝ ለመቀበል ወደ የአዝማቹ ድንኳን ይጣደፍ ጀመር፡፡

የሜጀር ትሪቶ ጦር ግስጋሴን የገታው ተኩስ የከፈተው የራስ መንገሻ ጦር ከጠላት ጋራ ተኩስ ልውውጥ ያደረገ መሆኑን የተረዳው በባልቻ አባነፍሶ የሚታዘዘው የእቴጌ ጣይቱ አምስት ሺ ጦር የያዘ ነበር፡፡ ከነርሱ ጥቂት ርቆ ሰፈራ ያደረገው በጎጃሙ ንጉስ ተክለሃይማኖት የሚታዘዝ ከአራት እስከ አምስት ሺ ተዋጊን የያዘ ጦር፣ ከሰፈረበት ብዙም ሳይርቅ ደግሞ የእቴጌ ጣይቱ ወንድም ራስ ወሌ ብጡል አስር ሺ ተዋጊ የያዘ ጦር ሰፈር ይገኛል፡፡ ከነዚህ ሰፈሮች ብዙም ሳይርቅ በራሳቸው በምንሊክ የሚታዘዘው ሰላሳ አምስት ሺ የሚጠጋ ተዋጊ ደግሞ በአድዋ ከተማ መግቢያ ላይ የሚገኘው ሸለቆን ይዞ በአባ ገሪማ እና ሶሎዳ ተራራ በስተሰሜን ካለ ቦታ ላይ ነው ሰፍሮ የነበረው፡፡

የሜጀር ቶሮቲ የሚመራው ቀዳሚ ጦር አደጋ ውስጥ ወድቋል ማለት ነው፡፡ በወቅቱ በነበረው ሁኔታ አልቤርቶኒ ለጠላት ጦር ባለው ንቀት ለራሱ ከሰጠው ትልቅ ግምት አንፃር በቶሪቶ የተመራው ጦር እጅግ ርቆ እንዲጓዝ በማድረጉ ከቀረው ጦር ጋር ግንኙነት ለማድረግ እንኳን በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ እንዲወድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክንያት ቶሪቶ የሚመራቸው 950 ወታደሮች ከማይወጡት አረንቋ ውስጥ መዘፈቃቸውን ሁለቱም ታውቋቸዋል፡፡

ጄነራል አልቤርቶኒ በሩቁ ሊነጋጋ ሲል ጀምሮ ይሰማው የነበረው የተኩስ ልውውጥ ድምፅ በሜጀር ቶሪቶሪ የተመራው ጦር የገጠመው አስቸጋሪ ሁኔታን ያመላከተ ነበር፡፡ ይህንን በሚገባ የተገነዘበው ጄነራል አልቤርቶኒ ጦሩን በአፋጣኝ ወደ ሜጀር ቶሪቶሪ ለሚመራው ጦር እንዲደርስለት ወደፊት እንዲጓዝ አላደረገም፡፡ ምክንያቱም በሜጀር ቶሪቶሪ የሚመራው ጦር እጅግ ርቆ በመጓዙ ሊደረስበት እንደማይችል፣ እንዲሁም በጉዞው ላይ በኢትዮጵያ ወታደሮች ጥቃት ሊሰነዘርበት እንደሚችል በመጠራጠሩ ነበር፡፡

ማለዳ ላይ የምንሊክ ጦር ከፊት ለፊቱ በአልቤርቶኒ የሚመራውን የኢጣልያ ጦርን እንቅስቃሴ መመልከት የሚችሉበት ወሳኝ ገዥ መሬት ላይ ነበር፣ ምንሊክ ጦራቸው ከጠላት ጦር ጋር በግልፅ አውደ ውጊያ ማካሄጃያ ጦር ግንባር ላይ እንዲፋለሙና እንዲለይለት ነው የሚፈልጉት፡፡ በእርግጥ የኢጣልያ ጦር በውትድርና ስነ ምግባር ደንብ የታነፀ፣ በቂ ወታደራዊ ስልጠና የወሰደ፣ የተሟላ ትጥቅ ያለው መሆኑን በዚህ ብልጫ እንዳለው ቢያውቁም በእሳቸው ከሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ጋር በፍፁም የማይመጣጠን አነስተኛ ቁጥር እንዳለው ያውቃሉ፡፡በዚያን ጊዜ አንድም ሰው እየተካሄደ ያለው ጦርነት ኢትዮጵያውያን የሚፈለሙበት ብቻ ሳይሆን ከዚያ በበለጠ መልኩ የወደፊቷ አፍሪካ የሚካሄድ ጦርነት እንደሆነ አይታወቅም ነበር፡፡

በጄነራል ሜትዬ አልቤርቶኒ የሚመራው የኢጣልያ ጦር ውስጥ ወደ አንድ መቶ የሚደርሱ ወታደራዊ መኮንኖች እንዲሁም መድፈኞች አውሮፓውያን ሲሆኑ፣ የተቀረው ጦር ውስጥ አራት መቶ ያህሉ ኤርትራውያን፣ አራት ሺ ሰባ ስድስት አካባቢዎቹ ተዋጊ ወታደሮች የሀገር ተወላጆች በመሆናቸው በመቶዎቹ አውሮፓውያን እየታዘዙ የምንሊክ ሠራዊት የሚዋጉት ወታደሮች የአፍሪካ ምድር ያፈራቻቸው አፍሪካውያን መሆናቸው አስደናቂው እውነት ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ነበር ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ወደ ሸለቆው መገስገስ የጀመሩት፡፡ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ጦር የተንቀሳቀሰበትን መሐል ለመሐል አቅጣጫን በመከተል ማጥቃት ሰነዘረ፡ በዚህ ማጥቃት ላይ የምንሊክ የግል ጠባቂዎች የሚገኙበት የንጉሰ ነገስቱ ጦር የማለዳዋ ፀሀይ ጨረር አይናቸውን እያጥበረበራቸው በመጀመሪያ በአነስተኛ መጠን በመቀጠል እጅግ በጣም ብዙ ወታደር በማሳለፍ ወደ ኢጣልያኖቹ ይዞታ መገስገስ ጀመሩ፡፡ ይህ እንቀስቃሴያቸው ለኢጣልያ ወታደሮች የጥይት ኢላማ እንዲሆኑ በቀላሉ አጋለጣቸው፡፡ ከፍተኛ ጉዳትም አደረሱባቸው፡፡

በዚህ የኢጣልያ ወታደሮች ጥቃት ወደኋላ ያፈገፍጋል ተብሎ የታሰበው የኢትዮጵያውያኑ ግስጋሴ ግን ሊገታ አልቻለም፡ ፡ የኢትዮጵያ ወታደሮች መጀመሪያ የማጥቃት እንቅስቃሴያቸው በኢጣልያ ወታደሮች ተመክቶ ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ ቢያስገድዳቸውም ኢትዮጵያውያኑ ወደፊት ለመገስገስ ባላቸው ቁርጠኝነት እንቅስቃሴያቸውን እንደገና እንደ አዲስ ሲጀምሩ ይታያሉ፡፡ በዚያ ጥይት በላያቸው ላይ እያፏጨ በሚያልፍበት የቀለጠ ውጊያ ውስጥ እቴጌ ጣይቱ እንደ ወታደሮቻቸው ሁሉ በእግራቸው ሆነው ፊታቸውን የሸፈኑበትን አይነ እርግብ ገልጠው በወኔ ወታደሮቻቸውን ያበረታቱ ነበር፡፡

የኢትዮጵያውያኑ አዳዲስ የሆቺክስ መድፎች እጅግ በፈጣን መልኩ የተኩስ ናዳ ማውረድ ጀመሩ፡፡ እነዚህ አዳዲስ ዘመናዊ መድፎች በመቀሌው ውጊያ ወቅት ውጤታማነታቸው ተረጋግጧል፡፡ መድፎቹ በተራራዎቹ ግርጌ ላይ ሆነው የአልቤርቶኒን ጦር ይዞታ ደጋግመው መደብደብ እንደጀመሩ ምንሊክ ራሳቸው ወደ መድፈኞቹ ቀርበው አተኳኮሳቸውን እያዩ ያበረታቷቸው ጀመር፡፡

እቴጌ ጣይቱ በአምስት መድፎች የሚተኩሱ መድፈኞች አጠገብ ሆነው መድፎቹ የሚደበድቡትን የጠላት ወረዳን ይመለከቱ ነበር፡፡ ኢትዮጵያውያኑ መድፈኞች ልክ እንደ መቀሌው ሁሉ መድፎቻቸውን ሲተኩሱ ኢላማቸውን እንዲመቱ አድርገው ስለነበር እጅግ ውጤታማ ነበሩ፡፡

ራስ መኮንን እና ራስ ሚካኤል አስራ አምስት ሺ የሚጠጋ ጦራቸውን በአልቤቶኒ ጦር በሰፈረበት የአዲፋቂ ኮረብታ በስተቀኝ በኩል ላኩበት፡፡ በተመሳሳይ ሰዓት የጎጃሙ ንጉስ ተክለሃይማኖት፣ የላስታው ገዥ ዋግሹም ጓንጉል፣ በእቴጌ ጣይቱ የሚታዘዘው ጦር በአልቤቶኒ ጦር ከሚገኝበት በስተግራ አቅጣጫ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮችን ላኩበት፡፡ ይህ እጅግ ረቂቅ ወታደራዊ ስልትን መሰረት ያደረገው የኢትዮጵያውያን የውጊያ ስልት እንደ ደጋን ትልቅ ግማሽ ክብ ቅርፅ ይዞ የነበረውን የኢጣልያ ጦር የጥቃት አድማስ እንዲሰበሰብና ወደ መሐል እንዲሳብ በማድረግ እያደረሰው ያለውን ጉዳት እየቀነሰ፣ ኢትዮጵያውኑ ተዋጊዎች ፋታ እንዲያገኙና ወደ መካከለኛው የጦሩ ይዞታ እንዲያመሩ አስቻላቸው፡፡

የማለዳው ፀሐይ እየበረታ ሲሄድ የኢትዮጵያውያኑ ተዋጊዎች በቁጣ በወኔ ተሞልተው ወደ ኢጣልያኖቹ ይዞታ ይወረወሩ ጀመር፡፡ እግረኞቹ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ፈረሶቻቸው እያስካኩ በተኩሱ መሀል ሽምጥ እየጋለቡ ከኢጣልያ ወታደሮች ጋራ እየተናነቁ የሚዋደቁት ኢትዮጵያውያንን አልበገር ባይነት በማየት ወደ ኋላ ከማፈግፈግ በስተቀር ሌላ አማራጭ እንደሌለ የተረዱት ጄነራል ደቦ ሜዳን ዋናው ሥር አዛዥ አርኔስቶ ባራቴሪ ከኢትዮጵያውያኑ ጋራ በፅናት እየተፋለሙ የሚወድቁ ወታደሮቻቸውን ቢያበረታቱም ሰዓቱ እየገፋ በሄደ ቁጥር በአድዋ ተራሮች ላይ ሽንፈታቸውን ማረጋገጫ ምልክቶች ይታዩ ጀመር፡፡

በዚያ ደብልቅልቅ ያለ ውጊያ ላይ ከጦሩ ጋር የሚጓዙት አዝማሪዎች፣ የሽለላና ቀረርቶ ፉከራ የሚያወርዱ ቀስቃሾች በኩራትና በወኔ እየተንቀጠቀጡ ስንኝ በመደርደር ኢትዮጵያውያኑ ተዋጊዎች የጠላትን ጦር እያርበደበዱ እያሰደዱ እንዲመቱ እንዲማርኩ ይቀሰቅሱ ነበር፡፡ ጀንበር በማዘቅዘቅ ላይ እያለች የእቴጌይቱ የንጉሰ ነገስቱ የማዘገር ጣቢያ በብዙዎች መስዋዕትነት ጀግንነት የተገኘውን ድል መቀዳጀቱን ያረጋገጡ ተዋጊዎች ቁስለኛ ጓዶቻቸውን ተሸክመው፣ የማረኩትን የጦር መሳሪያ እና ምርኮኛ ይዘው ጀብዱአቸውን ለማሳየት ወደ ንጉሱ ድንኳን አቅራቢያ መገስገስ ጀመሩ፣ ከዛሬ 123 ዓመት በፊት በዚች ቀን፡፡



# የዳግማዊ ምኒልክ

## ታሪካዊ ንግግሮች እና የምስክርነት ቃል

- ሰው ሁሉ እኩል ስለሆነ፤ ማንም ሰው ሰውን ባሪያ አይበል ::
- ሁሉም ሰው በየኃይማኖቱ ይደር ::
- ያሳደጋችሁኝ ልጃችሁ፣ አብረን ያደግን ባልንጀራችሁ ነኝ :: በአባቴ አልጋ ካስቀመጣችሁኝ፤ በፍቅር ተዳደሩልኝ :: (ለሸዋ ኦሮሞዎች የተናገሩት)
- ደኻ እወደደበት ቦታ ይቀመጥ :: በዘር፣ በወገን ልዩነት አይከልከል :: ( ለሱልጣን አባጅፋር የተነገረ)
- ሰው አታስፈጅ ! አገርህንም አታስጠፋ! ገብርህን ይዘህ ግባ! ( ለንጉሥ ጦና የተነገረ )
- የመሬት ጥያቄ ላቀረቡ የውጭ አገር ሰዎች ንጉሡ የሰጡት መልስ፡-
- በጣም ወደኋላ የቀረን ሕዝቦች ነን :: ገና የሚሠራ ብዙ ሥራ ስላለ ወጣቶቻችን መማር አለባቸው ::
- አባት ያለህ የአባትህን እሰጥሀለሁ፤ አባትህን መርቅ :: አባት የሌለህ አባትህ እኔ ነኝና ደጅ ጥናኝ ::
- እኔ ቤት እንጀራ የለም :: እንጀራ ያለው ትምህርት ቤት ስለሆነ፤ እሠራሁት ትምህርት ቤት ልጆቻችሁም እያስገባችሁ አስተምሩ ::
- የኔ ርስት ኢትዮጵያ ናት፤ የግል እርስት አልፈልግም :: ደግሞስ የተሾምነው እርስት ከተካፈልን ለሕዝቡ ማን ያካፍለዋል?
- ሀገራችን አንድትለማ የሚቀርቡንን ሁሉ በታላቅ ደስታና በአክብሮት እንቀባላቸዋልን :: በሌላ ለሚመጡብን ግን፤ ሁላችን ሳናልቅ ሀገራችንን ለባዕድ አሳልፈን እንሰጥም ::
- ‹‹ በንጉሠ ነገሥቱና በሕዝቡ መካከል መራራቅ የለም ›› ( ሮድ እንግሊዛዊ ባለስልጣን )
- ‹‹ በምኒልክ ዘመነ-መንግሥት የአገሪቱ ክብር አደገ :: የዘመናዊ አስተዳደር መሠረት ተጣለ :: ንጉሠ ነገሥቱ በዘመናዊ አስተደደር ይመራሉ›› ( ኢላንዶርፍ )
- ‹‹ ምኒልክ በጥበብ ሕዝቡን ሲያስተዳድሩ፤ ሕዝቡ በፍቅር እንዲከተላቸው እንጂ በፍርኃት እንዲገዛላቸው አይፈልጉም ›› ( ግሊክን )
- ‹‹ ዓለም ምኒልክን ያህል ታላቅ ኢንጂኒየር አጣች›› (ዶክተር መረብ)

/ ምንጭ፡- የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ መጽሔት ቁጥር1. ነሐሴ 1992 ዓ.ም ከገጽ 16 እስከ 17. /

### አዋጅ

እግዚአብሐር በቸርነቱ እስከ አሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ እኔም እስከአሁን በእግዚአብሐር ቸርነት ገዛሁ። እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ስለ እኔ ሞት አላዝንም ደግሞም እግዚአብሐር አሳፍሮኝ አያውቅም ከእንግዲህም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም አሁን ግን በእግዚአብሐር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጥም። የአገሬ ሰው ከአሁን ቀደም የበደልኩህ አይመስለኝም አንተም እስከአሁን አላስቀየምከኝም።

ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ ለሚስትህ ለሃይማኖህ ስትል በሐዘን እርዳኝ ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ አልተውም ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም ዘመቻውም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረኢሉ ከተህ ላግኝህ

## ዳግማዊ ምኒልክ ያከናወኗቸው ብሔራዊ ተግባራት

- የሕትመት መሣሪያመስመጣት፣
- የጥይት ፈብሪካ ማቋቋም፣
- የማዕድን ፍለጋ ፕሮጄክት ፣
- ትራስፖርትና የመገናኛ አውታሮች ( የባቡር መስመር ዝርጋታ ከጂቡቲ አዲስ አበባ )፣
- ዘመናዊ ገንዘቦችን አስቀርጸ ማውጣትና ባንኮችን መክፈት፣
- ገንዘብ መቅረጫ አስመጥተው ሥራ ላይ ማዋል፣
- የቴሌፎን ቴሌግራምና የፖስታ አገልግሎትን በሥራ ላይ ማዋል፣
- የክትባት መድኃኒት፣
- የኤሌትክሪክ መብራት፣
- የመንገድ፣ የድልድይና የሕንፃ ሥራዎች ግንባታ፣
- የሸክላ ፋብሪካ ማቋቋም፣
- ቶሎ የሚደርስ ልዩ የዛፍ ዘር አስመጥቶ መትከል፣
- ዘመናዊ የከብት ማዳቀልና እርባታ ሥራብ ማስጀመር፣
- በሕክምና ተቋም ዘመናዊውንና ባህላዊውን መድኃኒት አቀነባብሮ መጠቀም፣
- የመጠጥ ውኃ ቧንቧ ዝርጋታንና የጉድጓድ ውኃዎችን ማደራጀት፣
- የመጀመሪያውን ጋዜጣ መውጣት፣
- ዘመናዊ ሆቴል ማቋቋም፣
- የዲፕሎማቲክ ግንኙነትን በአቻነት ደረጃ አጠናክሮ መቀጠል፣
- የንግድ ግንኙነት ( ከውጭ አገሮች ጋር )፣
- የወሰን ክልል ስምምነት መፈረም፣
- በቂ ሕክምና ባልተገኘበት አጋጣሚ ማንም ሰው ታሞ ስዳከም፤ 48 ሰዓት ሳይሆነው ሞተ ተብሎ በችኮላ እንዳይገነዝ የሚደርግ ደንብ አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋል፣
- ባርነትን ማውገዝና በሕግ መከልከል፤
- በኢየሩሳሌም ገዳም የኢትዮጵያ ይዞታ የነበረውን አርመን፣ ፅርዓውያንና ግብፃውያን ስለአጣበቡት ፤ ከቱርክ ንጉሥ ከሡልጣን አብዱል ሂሚድሃን ጋር ተላልከው የአባቶችን ይዞታ ማስከበርና ማስፈፋት፣
- ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪውን የሰፈራ ማስተር ፕላንና የቦታ አስተዳደር ደንብ ማውጣት፤
- የድንጋይ ከሰል ማዕድንን ማግኘትና ወዘተ. ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው ::

/ ምንጭ፡- የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ መጽሔት ቁጥር1. ነሐሴ 1992 ዓ.ም ገጽ 18. /

# “ባይ ባይ ኢህአዴግ?!”

**መላክ ቢ.**

“ከጥቂት ወራት በኋላ የአፋር፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የሶማሌ፣ የኦሮሞ፣ የአማራ … ፓርቲ እያልን አንሄድም። እንደኢህአዴግ ከጫፍ ጫፍ ያሉ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በነጻነት የሚሳተፉበት አንድ ሃገራዊ ፓርቲ እንመሰርታለን!!”

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ እሁድ የካቲት 17 ቀን 2011 ዓ.ም ከ3 ሺህ ከሚልቁ ከሃረሪ፣ ከጋምቤላ፣ ከአፋር እና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ እንዲሁም ከሶማሌ ክልሎች ከተውጣጡ ተወካዮች ጋር በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አዳራሽ ባካሄዱት ውይይት የተናገሩት ሃሳብ ነው። ይህ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ዋና የመወያያ አጀንዳ ሆኖ የወጣው ሃሳብ በታዋቂ አክቲቪስቶች እና የፖለቲካ ሰዎች ዘንድ የተለያየ ትርጓሜ እየተሰጠው አሁን ድረስ ከመጥበሻው ያልወረደ እንቁላል ሆኗል። ጉዳዩን የጊዜው የመገናኛ ብዙሃን መነጋገሪያ እንዲሆን ያደረገውም የኢህአዴግ “አንድ ሃገራዊ ፓርቲ” እቅድ እንዲህ በቅርቡ ለጥብስ ይደርሳል ብሎ ያሰበ ባለመኖሩ ነው። የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ሃላፊው አቶ ብናልፍ አንዱዓለም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ፍንጭ ሲያሰፉት “ አጋር ድርጅቶች በሙሉ የሚካተቱበት፣ አማራ ኦሮሞ የማይባልበት፣ አንድ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ይመሰረታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም እንደቀድሞው በብሄር ውክልና ሳይሆን በአባላት በብቃት ይመረጣል። ለዚህም የጥናት ሰነድ ዝግጅቱ እየተካሄደ ነው። በያዝነው 2011 አመት መጨረሻ ላይ ይጠናቀቅና ለውይይት ይቀርባል” ነበር ያሉት። ሰነዱ ተጠናቅቆ ውይይቱ ተካሂዶ ሲያበቃ ወደተግባር ይገባ ሲባል ኢህአዴግ የሚባለው ፓርቲ ይፈርስና አንድ ብሄራዊ ፓርቲ ይቋቋማል። ይህ እንዲህ ከሆነ ዘንዳ ከጨቅላ እድሜው ጀምሮ እስከወጣትነቱ መባቻ ድረስ ኢትዮጵያን ለ28 ዓመታት “አንቀጥቅጦ” የገዛው ኢህአዴግ ከግዛት መንበሩ “ባይ ባይ” ተብሎ ይሰናበት ይሆን? የሚለውን ጥያቄም እኛ ዛሬ ልናነሳ ነው።

## አሮጌው ፓርቲ በአዲስ ቆዳ

በብዙ ወረዳ እና ክፍለከተማ ቢሮዎች ግድግዳ ላይ ከደቂቃ መቁጠሪያቸው ስር “መጪው ጊዜ ከኢህአዴግ ጋር ብሩህ ነው” የሚል ጽሁፍ የተለጠፈባቸው ሰዓቶች ዛሬም ተሰቅለው



ይታያሉ። የዛሬው እውነት የሚመሰክረው ግን ይህ መፈክር እንኳን መጪውን ዘመን ብሩህ አድርጎ ሊኖር ኢህአዴግ ኖሮ የሰዓቱን እድሜ ያክል ርዝማኔ እንኳን የህዝቡን ፍላጎት አሳክቶ ማለፍ እንዳዳገተው ነው። ኢህአዴግ አርጅቷል። ከተመሰረተበት ወቅት አንስቶ አውራ ፓርቲ ሆኖ ሃገር ለ40 ዓመት እንዲገዛ በስትራቴጂስቱ አቶ መለስ ዜናዊ ረጅም ርዕይ የተቀረጸለት ኢህአዴግ አሁን ገና በጎልማሳነት ዘመኑ አርጅቷል። ይህንን ያረጀ ፓርቲ በአዲስ ስም እና መለያ ብቅ አድርጎ ዳግም አገዛዙን ሃ ብሎ እንዲጀምር ማስቻል ደግሞ ብዙ ማሰብን ይጠይቃል። ኢህአዴግ ወደ መሬት የወረደ ለውጥ ማምጣት ቢሳናቸውም አየር ላይ የሚንሳፈፍ አሳብ ያላቸው አሰላሳዮችን አላጣም። ኢህአዴግ አንዳንድ ምሁራን እንዳሉት በጥልቅ እቅድ በህብረተሰቡ ውስጥ ሰፊ አስተሳሰብ ዘርግቶ በቀላሉ ላለመውደቅ አማራጭ ድጋፎችን አመቻችቶ ቆቅ ሆኖ የተቀመጠ ድርጅት ነው። ይህ ድርጅት ወድቆ እየተነሳና አባሎቹ እንደሚሉት በእሳት ውስጥ እያለፈም ፈታኝ ዘመናትን ተሻግሯል። ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ነኝ ቢልም ሳያስበው ወይም አስቦበት አምባገነን ባህሪ ስለሰፈነበት ከውጭ የሚመጣውን ተግዳሮት በሃይል እና በአሳሪ ህጎች እየፈታ ቆይቷል።ኢህአዴግ ከባድ ፈተና የገጠመው ከውስጥ የሚነሳበት ተቃውሞ እና የመለያየት ሃሳብ ላይ ነው። በተለይም የቀድሞ ሊቀመንበሩ ከሞቱ በኋላ በነበረው ሂደት ኢህአዴግ ውጪውን ያለ ቢመስልም በውስጠ ፓርቲ ትግል ሲታመስ ኖሮ ነው የውጭውን ግፊት መቋቋም ካልቻለበት ደረጃ ላይ የደረሰው።

አቶ መለስ ዜናዊ በኢህአዴግ (ህወሃት ቢባል ይቀላል) ውስጥ የተነሱትን የተለዩ ድምጾች እያፈኑ እርሳቸውን የሚተካ የፓርቲ አባል ሳያፈሩ መኖራቸው ሳያንስ ስጋት የሚሏቸውን ሁሉ እየቀነጠሱ ፓርቲያቸውንም ራሳቸውንም ከስልጣን አካባቢ የማይርቅ ባለርስት አድርገው ቆይተዋል። ወደ መጨረሻው አካባቢ በታሪኩ ከባድ የሚባል ተቃውሞ ተቀጣጥሎበት በተለይ በኦሮሚያ ሙሉውን እና በአማራ ጎንደር አካባቢ ተይዞ ሲታመስ ቢቆይም ድንገት እነዶክተር አብይ ከመሃል ወጥተው የፓርቲውን ህልውና ከመውደቅ አትርፈው ሞትን አስመልጠውታል። የቲም ለማ መፈጠር ኢህአዴግ የሚባለውን ድርጅት ግብዓተ መሬት አዘግይቶታል። ልዩነቱ ዛሬ ከሞት ማምለጡ ሳይሆን በራሳቸው በዚህ ቲም አባላት ነገ የማይቀረው ሞቱ ክብር ሞት እንዲሆን መደረጉ ብቻ ነው። ለዚህም ▶

እነሆ ኢህአዴግ እንደበረዶ ቀልጦ ሌላ ፓርቲ የሚወልድበትንና ራሱ ግን ከገጽ የሚጠፋበትን መስመር ይዟል። ይህ አሮጌ ፓርቲ አዲስ ቆዳ ከመቀየሩ በፊት ግን አሟሟቱን ለማሳመር እየተጣጣረ ይገኛል። ምናልባትም ኢህአዴግ ወደቀ ሳይሆን ከሰመ እንዲባል አዲስ ስትራተጂ የተነደፈለት መስሏል።

## ሽግግር "ከብሄር ፓርቲ ወደ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ"

ኢህአዴግ ከመነሻው የተጠነሰሰው በህወሃት ነው። ህወሃት ከትግራይ ሪፐብሊክ አጀንዳው ለጊዜው ተላቅቆ ያዋጣኛል ብሎ ባመነውና የራሱንም ህልውና በሚያስቀጥልለት፣ የሚታገልለትን ህዝብ ጥቅምም በሚያስጠብቅበት የኢትዮጵያ ጠቅላይነት ሃሳብ ሲመጣ ኦህዴድ እና ብአዴንን እንደትሮይ ፈረስ ሊጋልባቸውና በፈለገው አቅጣጫ ሊነዳቸው አስቦ ከምርኮኛ እና ከኢህአፓ ትራፊ ሰዎች አሰባስቦ መሰረታቸው። ከዚያም በህዝብ ላይ ጫናቸውና ስራውን እሱ መስራት ጀመረ። ላለፉት 27 ዓመታት የኢትዮጵያ ፖለቲካ በህወሃት የበላይነት የተመራው እህት ድርጅቶችም ይባሉ አጋር ሁላቸውም የህወሃት ቡችሎች ስለነበሩ ነው። ይህ ግን ካሰበበት 40 አመት የመግዛት ህልም ሳይደርስ በሁለት ሶስተኛው እድሜ ላይ ተቋረጠ። አዳዲስ አሳቦች እና አዳዲስ ጥያቄዎች ከውስጥ ሲመጡ ዶክተር አብይ እንዳሉት አንቁላሉ ከውስጥ ተሰበረ። እናም ህይወት ያለው ነገር ወጣ። ህወሃት አክትሞለት ወደመቀሌ ሲያፈገፍግ እነሆ አማራ እና ኦሮሞ አዳዲስ ስያሜ በያዙ ፓርቲዎቻቸው መመራት ጀመሩ።
ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ላይ ፌዴራሊዝምን ሲጭን እና የብሄር መብት ብቻ የሚከበርበት ስርዓት ሲዘረጋ ግለሰባዊ መብት በቡድን መብት ተጥሶ ዜግነት ትርጉም አልባ ሆኖ ነበር። በዚህ ሳቢያም ማንነት ሲባል የብሄር ማንነት ብቻ እየተዘመረለት ብሄራዊ ማንነት ወይም ኢትዮጵያዊ ማንነት የሚባለው ጉዳይ የቡና ቁርስ ላይ ብቻ የሚቀርብ መቆያ ሆኖ አረፈ። በዚህ ሳቢያ ሃገሪቱ ከላይ ታች ድረስ ብሄር ላይ ብቻ የተንጠለጠሉ ሃሳቦች ሲራመዱባት እና ኢትዮጵያዊነት የማይነሳ ውጉዝ ሲሆን አመታት አለፉ። ለምን ይህ ሆነ ብሎ ለመጠየቅ እንኳን በማይቻልበት ደረጃ ስርዓቱ አፋኝ ሆኖ ከጅምሩ የኢትየጵያዊነትን ሃሳብ ሲያጥላላ እና ሃሳቡንም ሲያናንቅ ኖረ።

ኢህአዴግ እንዲህ ብሄራዊ ፓርቲ ሆኖ ኖሮ ብቻ ሳይሆን ሃገሩን ሁሉ በብሄር ሃሳብ አጥምቆ ቆይቶ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወደ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ለመለወጥ የሚያስችለውን ቁልቁለት ይዞ ሲንደረደር ጉዞው ጥቂትም ቢሆን ግር ማሰኘቱ አልቀረም። ብሄር ቆጥ ላይ በተሰቀለበት በዚህ ጊዜ ላይ ኢትዮጵያዊነት ሊያውም በአንድ ሃገራዊ ፓርቲ ደረጃ ኢትዮጵያዊነት ይቀንቀን ሲባል አሃዳዊ አስተዳደር ሊመጣ ይሆን ወይ የሚል ጥያቄም መነሳቱ አልቀረም።

ከሁሉ በላይ ደግሞ ብሄር አሳቡም ይሁን ተግባሩ ነግሶ አንድ ሃገራዊ ማንነት ደግሞ በተራው ቆርቁዞ ኖሯል። ዶክተር አብይ እና ለማ መገርሳ በኢትዮጵያዊነት ሃሳብ የተዳከመውን አንድነት ካነቃቁት በኋላ ኢትዮጵያዊነት ወደቀድሞ ቦታው ለመመለስ ዳር ዳር ባለበት ጊዜ በአማራው በኩል አማራዊ ብሄርተኝነት በኦሮሞውም በኩል ኦሮሞአዊ እንደ አዲስ አጎንቁለው ወጥተዋል። ሁሉም አጥሬንና ብሄሬን እያለ መጣለዝና በጋጨት አብዝቷል። በዚህ ሳቢያ ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን ባልታየ መልኩ ብዙ ህዝብ ተጎድቷል። ከቤት ንብረቱም ተፈናቅሏል። በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ የቀለጠ የብሄር ጡዘት ላይ ናት። ይህ ጊዜ ለኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነት የሚተርፍ ስፍራ ይኖረው ይሆን ወይ የሚለው ደግሞ የብዙዎች ጥያቄ ነው።

## "በፌዴራሊዝም አንደራደርም"

ፌዴራሊዝም በኢትዮጵያ ውስጥ የህልውና መሰረት ነው ተብሎ በታመነበት በዘመነ ኢህአዴግ ከአሃዳዊ አገዛዝ በተቃርኖ እንዲቆም ተደርጎ የተቋቋመ የአስተዳደር ስርዓት ነው። የፌዴራል ክልሎች ቀድሞ የነበረችውን ኢትዮጵያ የምትባለውን ሃገር በፈቃደኝነት አቋቋሚት ተብሎ ነው በኢህአዴግ የተነገረው ። ኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ተመሰርታለች ነው የተባለው። ኢትዮጵያ ከፌዴራሊዝም ለዚያውም ከብሄር ፌዴራሊዝም በላይ መድሃኒት የላትም እየተባለም ነው። በተለይም በቅርቡ የዶክተር አብይ ፓርቲ የሆነው የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኦዴፓ) በሰጠው መግለጫ "በፌዴራሊዝም አንደራደርም" ማለቱ አሁን ዶክተር አብይ ካመጡት ኢህአዴግን አሃዳዊ ፓርቲ የማድረግ ሃሳብ ጋር የሚጋጭ ነው የሚሉ አስተያየቶች እየተበራከቱ ነው። የፌዴራል ሰርዓቱ አሁን ባለበት ሁኔታ ሳይሻሻል ወይም ህገመንግስት ሳይከለስ ወይም ክልሎች ያላቸው ራሳቸውን የማስተዳደር መብት ላይ ከአሃዳዊ ፓርቲ መርህ ጋር የሚጋጭ መሆን አለመሆኑ ሳይመዘን ከጥቂት ወራት በኋላ ሃገሪቱን የሚመራት ፓርቲ አሃዳዊው አዲስ ፓርቲ ነው መባሉም የርዕዮተ አለም መጠላለፍ ያመጣል የሚል ስጋታቸውን ያስቀመጡም አልታጡም ። የሆነው ሆኖ ፌዴራሊዝም እንደ አስተዳደር ስርዓት በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዞ በተቀመጠበት ሁኔታ ሃገሪቱ ከብሄር ፓርቲ ወደአንድ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ልትሸጋገር ስለመሆኑ ማሰብ በርግጥም ይፈጸማል ወይ የሚል ጥርጣሬን ያጭራል። ያም ሆኖ ዶክተር አብይ ካቀረቧቸው ሃገርን አንድ አድርጎ የመምራት እና የብሄር ጉዳይን ከኢትዮጵያዊነት የሚቀጥል ሁለተኛ ጉዳይ የማድረግ ሃሳቦች ውስጥ ይህ እርምጃቸው ቀዳሚ ሰፍራ የሚሰጠው ሆኗል።

## ቀን የወጣው "ለአጋር" ወይስ "ለአውራ"

በኢህአዴግ መዋቅር ውስጥ ግንባሩን ያቋቋሙት አራት ብሄራዊ ፓርቲዎች ናቸው። ከእነዚህ አራት ፓርቲዎች ሶስቱ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በህወሃት ፈብራኪነት የተቋቋሙ ናቸው። ዓላማው ግንባሩን የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ድምጽ የተወከለበት አስመስሎ ኢትዮጵያን በፈለጉት መንገድ መምራት ነበር። ለዚህም ነው ሶስቱን ዋና ዋና ብሄሮች (አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ ) እንዲሁም ከሰባ በላይ ብሄር ብሄረሰቦችን የያዘውን ደቡብ በሚል አንድ ደርጅት በመጨፍለቅ አራት ውክልና ለመፍጠር የተነሱት። ቀሪ አናሳ በሚል የሚጠሯቸውን ብሄሮች ደግሞ በየራሳቸው ፓርቲ በማደራጀት አጋር ፓርቲ ብለው ይዘዋቸዋል። ይህ ላለፉት 27 ዓመታት ሲሰራበት የኖረ አካሄድ ነው።

እነዚህ አጋር ፓርቲ የሚባሉት የሶማሌ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ሶህዴፓ) ፣ የጋምቤላ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጋህዴን) ፣ የአፋር ብሄር ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አብዴፓ) ፣የቤኒሻንጉል ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ቤህዴፓ) እና በመጨረሻም የሃረሪ ብሄር ዴሞክራሲያዊ ንቅናቂ (ሃብሊን) ናቸው። እነዚህ አምስት ፓርቲዎች የወከሏቸውን ህዝቦች ይዘው በኢህአዴግ አጋርነት ላለፉት 27 ዓመታት ቆይተዋል። በዚህ ጊዜ ለህዝባቸው ምን ረብ ያለው ትግል አደረጉ፣ ከኢህአዴግ አድርግ አታድርግ ትዕዛዝ ባፈነገጠ ሂደት ምን ያህል ተጉዘው የህዝብ ጥያቄ መለሱ የሚለው በራሱ ሌላ ጥያቄ ነው። በተለይም ኢህአዴግ ሲፈልግ እየሾመ ሲፈልግም እያወረደ አሻንጉሊት ያደረጋቸው እነዚህ ፓርቲዎች አንዳንዴም እንደጋምቤላ ፓርቲ አመራሮች እያመጹና እየተቃወሙ ኢህአዴግን ለመገዳደር ሲሞክሩ ለብዙ መከራ እና እስር የተዳረጉበት ጊዜም ነበር። ለኢህአዴግ ሪሞት ኮንትሮል ሆነው ከማገልገል ያለፈ ተግባር ያልነበራቸው እነዚህ ፓርቲዎች በብዙ መንገድ ውስጥ ለማለፍ ቢሞክሩም እርምጃቸው ግን አንድ ቦታ ላይ ተቀምጦ የክልሉን ሃብት እና ንብረት የሚቦጠቡጥ ሙሰኛ ባለስልጣን ከማፍራት እና ለኢህአዴግ አመራር እጅ ሰጥቶ በተፈለገው መንገድ ከመነዳት ያለፈ ተግባር የሌለው አመራር ብቻ ነው ያተረፉት።

በዚህ ስሌት ዛሬ ኢህአዴግ የሚባለው ድርጅት ፈርሶ የነዚህ አናሳ ብሄሮች ፓርቲዎች በእኩል ለመወሰን የሚካተቱበት ፓርቲ መፈጠሩ ከአውራ ፓርቲዎች በላይ የሚያስደስታቸው እንደሚሆን ይጠበቃል። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በነበራቸው ቆይታም ሃሳባቸውን ሲገልጹ የተስተዋለው ይኸው ነው።

አጋር ፓርቲዎች ቀን ወጣላቸው ማለት በሚያስችል መልኩ ነው የአሁኑ የዶክተር አብይ መግለጫ የሚያስደስታቸው። ምክንያቱ ደግሞ ከእነዚህ ፓርቲዎች ብዙ ጠንካራ ሰዎች ቢኖሩም ለፌዴራል ስልጣን ያላቸው ስፍራ ውስን ስለሆነ የመሰማት ሃይላቸው ደካማ ሆኖ ኖሯል። የመጨረሻ ወሳኝ የፓርቲውን ስልጣን የሚይዙት ሰዎች ከአራቱ አውራ ፓርቲዎች ብቻ የሚውጣጡ መሆናቸው በራሱ የተሳትፎ እድልን ከመከለሉ ባሻገር አግላይ የሆነ አካሄድ እንዲሰፍንም አድርጓል የሚል አምነት አለ።

ከዚህ አንጻር የአሁኑ አንድ ብሄራዊ ፓርቲ ምስረታ እቅድ ለአጋር ፓርቲዎች መልካም አጋጣሚ ተደርጎ መወሰድ ይችላል።እስከመቼ ድረስ አጋር ተብለን እንኖራለን የሚለው ጥያቄያቸውም በዚህ አዲስ ፓርቲ ምስረታ ምላሽ እንደሚያገኝ ይታመናል።

## ከ "ተዋሃዱ" ወደ "ተቀላቀሉ"

ጠቅላይ ሚኒስተር አብይ አህመድ ወደስልጣን ሲመጡ ቀዳሚ መልዕክታቸው ኢትዮጵያ ይህ ሁሉ ፓርቲ አያስፈልጋትም፣ ሁላችንም በየምንታገልበት መስመር አንድ ከሆነን ተዋህደን እና ተባብረን አንምጣና እንፎካከር የሚል ነበር። በገዢው ፓርቲ እህት ድርጅቶችም ይሁን በተፎካካሪ ፓርቲዎች በኩል "ተዋሃዱ" የሚለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቃል የተከበረ መስሏል። ቀዳሚውን እርምጃ የወሰደው ራሱ ኦዴፓ ሲሆን ከኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ጋር ተዋህዷል። ይህ እርምጃ በአማራው

ክልልም ከአንድ ለትግል ኤርትራ ከነበረ ግንባር ጋር የመዋሃድ መስመር አስከትሏል። ከዚያም በኂላ በኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ ሰብሳቢነት ስምንት ፓርቲዎች ተዋህደዋል። እንዲህ እያለ በብዙ ፓርቲዎች መካከል የሚደረገው ውህደት የዜግነት ፖለቲካ ወደሚያራምዱት ሃይሎች ቤትም ጎራ ብሎ ሰማያዊ ፓርቲ ራሱን እስኪያፈርስ እና አዲስ የዜግነት ፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረት ውሳኔ ላይ ደርሶ እስኪንቀሳቀስ አድርሶታል።

በተለየም ኦዴፓ እና አዴፓ አዳዲስ ስም ይዘው እንዲመጡ ያደረጋቸው አቃፊ ፖለቲካ ባህሪ እንዲላበሱ በሚል መሆኑ ተነግሯል። ይህ የሆነው በቅርብ ጊዜያት ውስጥ ነው። አሁን ደግሞ እነዚህ ሁሉ ድርጅቶች እንደማይኖሩና በምትኩ አንድ ኢትዮጵያዊ ድርጅት እንደሚመሰረት ነው የተነገረው። አዳዲሶቹ የኢህአዴግ ታዳሽ ፓርቲዎችስ ምን ሊሆኑ ነው የሚል ጥያቄ እዚህ ላይ ይነሳል። ኢህአዴግ በአንድ በኩል ፓርቲዎቹን በአዳዲስ መልክ እያዋቀረ አቃፊ ባህሪ እንዲኖራቸው እየሰራሁ ነው ባለ ማግስት እንደገና አፍርሼ የብሄር ስም የማይጠራበት አዲስ ፖለቲካ ፓርቲ ልመሰርት ነው ማለቱ ምን ያህል ተቀባይነት ያገኛል የሚለው ጥያቄ አንዳለ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ላለፉት አመታት በላያችን ላይ ተዘርቶ የኖረው የብሄር ፖለቲካ ብዙዎችን በየራሳቸው ብሄር እንዲቧደኑ እና የየራሳቸውን ብሄር እንዲመሰርቱ ያደረጋቸው በመሆኑ ነው። በዚህም ሆነ በዚያ ነጻ አውጪዬ ወኪሌ ብለው የተቀበሉት እና የሚደግፉት የብሄር ፓርቲ ያላቸው ዜጎች ያለብሄር ውክልና በሁሉን አቀፍ ጥላ ስር ተሰባሰቡ ቢባሉ አስቀድሞ የፖለቲካ ስራ ካልተሰራ በቀር የፍላጎት ማጣት እና የመጠራጠር ከዚያም አልፎ መከታ የመፈለግ ሂደት ሊፈጠር እንደሚችል ከወዲሁ ማሰብ ሞኝነት አይደለም። ተቃውሞ ገጥሞት አፈጻጸሙ የሚዘገይበት፣ በየብሄራችን የሚያቧድነን አንጂ በምንቃወመው አሃዳዊነት ውስጥ የሚከተን አሰራር እንዴት ይፈጠራል ብሎ በሚያስብም ህዝብም በጥርጣሬ የሚታይበት እድል አይጠፋም። ነገር ግን ከመሰረቱ ላየው ይህ አዲስ አይነት ብሄር አልባ ኢትዮጵያዊ አወቃቀር ሁሉንም በእኩል የሚያገለግል ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ለመመስረት እና ሁሉም ዜጎች ያለምንም የፓርቲ ጣልቃ ገብነትና ፍቃድ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተሳትፈው የየራሳቸውን አስተዋጽዖ የሚያሳርፉበት እድልም ይፈጥራል የሚል እምነት አለ። በዚህ በኩል በሂደት ኢትዮጵያውያን ክልሌ ሳይሆን ሃገሬ ብለው የሚሰሩበት መድረክ አንደሚፈጠርላቸው ጥርጥር የለውም። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሃሳብ ተዋሃዱ ባሉ ማግስት ተቀላቀሉ ማለት እንደጀመሩ ማሳያም ጭምር ነው። ኢትዮጵያዊነትን ሲሰሙ የሚያንገፈግፋቸው እና ብሄራቸውን ብቻ በማላቅ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ሳለን ተጨቁነን ነበር የሚሉ ዜጎች በአዲሱ ፓርቲ እንዴት እንደሚታቀፉ እና ሃገር አቀፍ ተሳትፎ ላይ እንዴት እንደሚካፈሉ የተነገረ ነገር ባይኖርም በዚያው ልክ ብሄር ታክቷቸው ሃገር የናፈቃቸው ደግሞ ከነበሩበት የአስተሳሰብ አጥር ወጥተው ሁሉን አቀፍ የሆነውን ኢትዮጵያዊ ትርክታቸውን የሚያሚሙቁበት ዘመን እንደሚመጣም ይታሰባል።

## ጉዞ -ከጠቅላይ ሚኒስትር ወደጠቅላይ ባለስልጣን

ይህ የኢህአዴግ "አንድ ፓርቲነት" ሃሳብ የጠቅላይ ሚኒስተር አብይ ሳይሆን የአቶ መለስ ዜናዊ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ። ኢህአዴግ ከአጋር ድርጅቶች የሚመጣበትን ተግዳሮት ለማስቀረት፣ ሁሉንም ጸጥ አድርጎ ለመግዛት እና የፌዴራል መንግስቱን ስልጣን በማስፋት የክልል ፓርቲዎችን ተገዳዳሪነት ለማስቀረት አማራጭ አድርጎ በመቀየስ በባህርዳሩ 9ኛው የኢህአዴግ ጉባኤ ላይ እንደሃሳብ ጠንስሶ በ11ኛው የኢህአዴግ ጉባዔ ላይ ያበሰለውና ተጠንቶ እንዲቀርብ መመሪያ የሰጠው ለዚሁ ነው። ስልጣንን ማስፋት እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቅላይ ገዢ በመሆን ወሰን አልባ ወሳኝ እንዲሆን ማድረግ የዚህ አንድ ብሄራዊ ፓርቲ ዓላማ ነው ብለው የሚሟገቱ ወገኖች አሉ።ነገር ግን ይህ አባባል ከጠቅላይ ሚኒስተር አብይ ሃሳብ ይቃረናል።

ዶክተር አብይ አህመድ ይህንን እቅድ ወደዚህ ሲያመጡ በተደጋጋሚ ጊዜ ስልጣን ላይ ለመቆየት ፍላጎት እንደሌላቸው በመግለጽ እና ለዚሀም የጠቅላይ ሚኒስተሩን የስልጣን ዘመን በህገመንግስቱ መሰረት መገደብን እንደአንድ ሃሳብ ባቀነቀኑበት ጊዜ መሆኑ እርሳቸው ጠቅላይ ገዢ ለመሆን ፈልገው እቅዱን አመጡ የሚለውን ሃሳብ ዋጋ ቢስ ያደርገዋል። በርግጥም በዚህ ፓርቲ መመስረት ማን ረጅም የስልጣን ዘመን ያገኛል የሚለውን መጠየቅ እዚህ ላይ ምላሽ አያስገኝም። ምክንያቱም ፓርቲው ላይ ማንኛውም ብቃት ያለው ኢትዮጵያዊ ከፓርቲ ውክልናም ውጪ ሆኖ የብሄራዊ ፓርቲው አባል ከሆነ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት የመወዳደር እና የማሸነፍ አንዲሁም ሃገር የመምራት እድል አንዳለው በመነገሩ ነው።

## ህወሃት ይገፋ ይሆን?

ብዙዎች የሚያነሱት ይህንኑ ነው። ህወሃት በአሁኑ ወቅት በዶክተር አብይ ቋንቋ ውስጥ ገና አልገባም። በሌላ አነጋገር አልተደመረም። ነገር ግን አሁን ድረስ የኢህአዴግ አባልነቱን ስለመሰረዙ የተናገረው ነገር የለም። በዚህ ስሌት ህወሃት ድምጽ ሳይኖረው በጥቂት ወራት ውስጥ ኢህአዴግ ከፈረሰ አዲስ በሚቋቋመው የብሄር አልባ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ውስጥ ራሱን ያቅፋል ወይስ ባለበት ብሄራዊ ፓርቲነቱ ይቀጥላል የሚል ጥያቄ ይነሳል። ከህወሃት ባህሪ አንጻር በደም በአጥንት የገነባሁት የሚለውን እና ኢህአዴግን ራሱን የፈጠረውን የ44 ዓመት ፓርቲውን አፍርሶ በአዲሱ ብሄራዊ ፓርቲ ውስጥ አባላቱን የሚያሳትፍበት ሂደት ውስጥ ይገባል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። ህወሃት ሁለት ምርጫዎች ውስጥ ይሆናል። አንድም አንደጀመረው የክልሉ ብቸኛ አስተዳዳሪ እኔ ብቻ ነኝ ብሎ አውጆ ሌሎች አጠገቡ እንዳይደርሱ ማድረግ ሌላም ትግራይን ለመገንጠል መንቀሳቀስ። ሁለተኛው አማራጭ የማይሰራ ብቻ ሳይሆን የማይጠቅምም ጭምር ነው። ይህ የፖለቲካ ትርፍና ኪሳራ ተሰልቶ የሚገባበት ውሳኔ ህወሃትን አጣብቂኝ ውስጥ ሊከተው ስለሚችል ይሞክረዋል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። በዚህ ፈንታ በብሄር ፓርቲነቱ ይቀጥልና የአዲሱ ፓርቲ አባል ግን አይሆንም። በሌላ ቋንቋ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ፓርቲ ማዕቀፍ ውስጥ ህወሃትም ይሁን አባላቶቹ የሚሳተፉበት እድል አይኖርም ማለት ነው። ስለዚህ ህወሃት ይገፋል። ይህ ታክቲካል የሆነ ማግለል ነው ብለው የሚያስቡ ፖለቲከኞች ዶክተር አብይ ይህንን አዲስ ፓርቲ ለማሳካት ከተመቻቸው የህወሃትን መኖር ስለማይፈልጉት ለርሳቸው መልካም አጋጣሚ ይፈጥርና ህወሃትን ከሁሉም ዘርፍ በማግለል የማይጠቅም ከዘራ ያደርጉታል የሚሉ አስተያየቶችም ይደመጣሉ።

## የተሰቀለውን ብሄር ማን ያወረድልናል

አሁን ከብሄር ወደግለሰብ የሚያንደረድር መንገድ መጥቷል። ማንም ኢትዮጵያዊ በፓርቲው ውስጥ ከገባ ሁሉም ከፓርቲ ሳጥን ወጥቶ የሚፈልገውን ሰው ለመምረጥ አድል ይኖረዋል። ነገር ግን አስከዛሬ የተሰቀለውን ብሄር ማን ያወርደውና አስተሳሰባችንን ከብሄር ወደ ብሄራዊነት ያደርስልናል የሚል ጥያቄ አለ። በብሄር በታጠረ ሂደት አልፈናልና በቀላሉ ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ትርፍና ኪሳራ ሳናሰላ አንገባም። ይህ ባህሪ ነው። የተሰራው ላለፉት ዘመናት ኢህአዴግ የለፋው ብሄርን ለማግነን እና ለመስቀል አንጂ ኢትዮጵያዊነትን ለማጉላት ባለመሆኑ የራሱ ሲሚንቶ ራሱን መልሶ መፈተኑ አይቀሬ ነው። ብሄር የገነባውን አስተሳሰብ ለማፍረስ ኢህአዴግ ገና ብዙ ርቀት ይጓዛል። ያም ከተሳካለትና በትክክል መተግባር ከቻለ ብቻ ነው። እንደነአብን እና ኦነግ ያሉ አክራሪ ብሄርተኛ አስተሳሰብ ያላቸው የፖለቲካ ቡድኖች በዚህ በኩል የሚኖራቸው አስተያየት ገና አልታወቀም። በአብዛኛው ግን ይቀበሉታል የሚል እምነት የለም።

## ባይ ባይ ኢህአዴግ

ቀድሞም እነዶክተር አብይ ኢህአዴግን ተፋትተውት ነበር። በቃላት አጠቃቀም እንኳን የኢህአዴግ ሽታ የላቸውም። ሰውም የወደዳቸው ኢህአዴግ ኢህአዴግ የሚል ሽታ ስለሌላቸው ነው። እናም ቢመሩ የሚያዋጣቸው አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ ብሄራዊ ፓርቲ ነው። ይህ ግን ከአራቱ ፓርቲዎች ፍላጎት ውጪ መተግባር የችላል ወይ የሚለው የሁሉም ጥያቄ ነው።

ብሄራዊ ፓርቲ ለኢህአዴግ አዳዲስ አባላትና ደጋፊ ያስገኝለታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብይና ቡድናቸው ከኢህአዴግ መራቁ ብዙዎቸን ባለሃብቶች እና ምሁራን ይስብላቸዋል። ፖለቲካን በሩቁ የሚሉ በፖለቲካ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ኖሯቸው ለሃገራቸው ይሰራሉ። በሌላ ወገን የሽግግር መንግስት ይመስረት እየተባለ የሚጮኸው ጩኸት እዚህ ላይ ሲደርስ ፍሬን የይዛል። ቲም ለማ የለውጥ አባላት ሁሉንም ተቃውሞ ጥያቄ አጉነው ይጠልዙትና ያለተፎካካሪ ብቻቸውን ሃገር ይመራሉ። ኢህአዴግን ማፍረስ እና ባይ ባይ ማለት ለኢህአዴግ ሰዎች ከማንም በላይ የተሻለ ሃገር እና ህዝብን በቅንነት የመምራት ዕድል ይፈጥርላቸዋል። ከተጠቀሙበት ኢትዮጵያም የምታድገው በዚህ አይነት የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ስትገባ ብቻ ነው።



"እኔም፣ እኔን መሰሎችም፣ ራሱ ኢሳትም ቢሆን፣ ሌላውም ነባው ፕሬስ የሚቃወመው ስልጣን ላይ ያለው መንግስት፣ ኢትዮጵያዊ መንግስስት አይደለም በሚል ነው። የአፈና፣ የጭቆናና የዘረኛ መንግስት ነው። ጥያቄያችንና ተቃውሟችን ዘረኛ ካልሆኑ፣ አፈና ካላካሄዱ ኢ-ዲሞክራሲያዊ ካልሆኑ ለምንድን ነው የምቃወማቸው? አሰራራቸው ትክክል ካልሆነ፣ ይሄ አካሄድ ትክክል አይደለም በሚል እንፅፋለን፣ አስተያየት እንሰጣለን። ከዛ ውጭ ግን እኔ ለ27 ዓመት ስጮህለት የነበረውን፣ የማምንበትን እንዲሆን የምመኘውን፣ የአገር መሪው ሲተረጉመው፣ እውን ሲሆን እያየው እንዴት አቃወማለሁ፡ ፡"

***ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና***
***አዲስ አድማስ ጋዜጣ የካቲት 16 ቀን 2011 ዓ.ም***



"እኛ ለአማራ፣ ለኦሮሞ፣ ትግራይ፣ ሱማሌ፣ አፋር፣ ሐረሬ፣ ጋምቤላ ወዘተ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ነው የቆምነው። ይህ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖሩ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በባህል ወዘተ ለማይገናኝ ሁሉ ቆመናል ማለት ነው። ምክንያቱም ማዕቀፏ ኢትዮጵያ ስለሆነች። በዚህ ምክንያት የምንለይበትና የምናለያይበት ምንም ምክንያትና ውሳኔ የለንም። ለኢትዮጵያ ሲባል አንዳንዱ ብሔሩን ወይም ጎሳውን ካልጠራሁ አይስማማውም ምክንያትና ሰበዝ ፈልጎ ለእክሌ ነው የቆምኩት ወይም ‹‹የምቆመው›› እንድትል ይፈልጋል።"

***ጋዜጠኛ አበበ ገላው***
***አዲስ ጊዜ መጽሔት የካቲት 2011 ዓ.ም***



"ወመዘክራቸው እጅግ ትልቅ የኢትዮጵያን ታሪክ የያዙ መፅሐፎች አሉ። ነገስታት የተፃፃፏቸው ደብዳቤዎች መዓት አሉ የወመዘክሩን ኃላፊ አነጋግሬያት እነዚህን መፅሐፎች ኢትዮጵያ ውስጥ ቦታ ጠበበን ብለው ያስወግዷቸው ነበር። አንዳንዶቹ በኪሎ ይሸጡ ሁሉ ነበር እነዚህን ውድ መፅሐፎች ልናገኝ ስለማንችል እንግሊዝ አገር ያለ አንድ አጋራችን ገዝቶ እንዲያመጣልን አድርገን ከአዲስ አበባ ወመዘክር ያመጣናቸው ናቸው ነበር ያለችኝ።"

***ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን***
***ሸገር ታይምስ መጽሔት የካቲት 2011 ዓ.ም***



"የዛሬ ዓመት ይህን በዓል አዲስ አበባ እናከብረዋለን" አልኩኝ። ምን ታይቶህ ነው ሳልሺኝ፣ ተስፋ ብቻ ነበር። ያኔ ሁሉም ነገር ጨለማ ነበር፤ የሚታይ ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር እኮ በምድረበዳም ያዘንባል። እናም የዛሬ ዓመት በድምቀት አዲስ አበባ እናከብራለን ስል በኢሳት ተላልፎ ስለነበር፣ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ እኔም መቃወም ቋሚ ስራቸው የሆነ ልጆች ነበሩ፤ እነዚህ የህወሐት ልጆች "አንተ ቅዠታም ስትቃዥ ትቀራለህ" ብለው ፃፉብኝ። "እንዴት አስበኸው ነው እዚህ የምታከብረው?" ብለው የስድብ ናዳ አወረዱብኝ። ነገሩ ዓመት ሳይሞላው፣ አገራችንን ረገጥን፣ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።"

***ጋዜጠኛ ደረጀ ሀብተወልድ***
***አዲስ አድማስ ጋዜጣ***
***የካቲት 16 ቀን 2011 ዓ.ም***



"ላለፉት 27 ዓመታት የታሪክ ትምህርት ክፍሎች አልተፈለጉም ነበር። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ትምህርት ክፍል እንኳን ብዙ ጫና ነበረበት። ታሪክን የሚቀነቅንና ለኢትዮጵያ ታሪክ የጎላ ቦታ የሚሰጠው የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም እንዲዳከም ተደርጓል:: በዚህ ተቋም ይሰሩ የነበሩትም ታላላቅ ምሁራን ተገፍተዋል።"

***ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው***
***አዲስ ዘመን ጋዜጣ***
***የካቲት 15 ቀን 2011 ዓ.ም***

# ምስጢረ ዘራፍ

*ዘራፍ!*
*እፍ................እኮ ነው እሳት ሲነደድ!*
*እፍ................እፍ እኮ ነው እሳት ሲነደድ!*
*እፍ እፍ አይደል፣ እሳት ሲነደድ.................*
*ዘራፍ እያለ ነው፣ ጀግናዬ ሲራመድ።*
*የሀገሬ ጀግና፣ ለካስ ያገሬ ሰው፣*
*ያን ሁሉ ጠላቱን፣ ምሱን ያቀመሰው፣*
*በመሳሪያው ሳይሆን፣ ዘራፍ በማለት ነው።*
*የዘራፍ ሚስጢሩ፣*
*ሲመረመር ስሩ፣*
*ይበልጣል ከጦሩ፣*
*የሀገሬ ጀግና፣ ዘራፍ በሚለው ቃል፣*
*ጦርነቱን ውስጡ፣ ቀድሞ ድል ያውጃል።*
*ዘራፍ በል እንጂ ጃል!*
*ዘራፍ ዘራፍ ማለት ለሁሉም ይበጃል።*

***የቀንድ አውጣ ኑሮ በይስማዕከ ወርቁ***

# ጠቅላላ እውቀት

- *ድራገን ፍላይ የተባሉት በራሪ ነፍሳት በሰዓት 60 ኪ.ሜ ይበራሉ፡ ፡ እነዚህ ነፍሳት 6 እግር ቢኖራቸውም በጭራሽ መራመድ አይችሉም፡ ፡ እድሜያቸው አንድ ቀን ብቻ ነው። በአይናቸው ውስጥ ያለው የሌንሶች ብዛት 30ሺህ ነው። በርግጥ አንድ ቀን ብቻ ለሚኖሩት ይህ ሁሉ ሌንስ ምን ያደርግላቸዋል? ያስብላል።*
- *የባህር ማዕበል ጥቃቅን እንቁራሪቶችን ከባህር ውስጥ ጠራርጎ በማውጣት ረጅም ርቀት ተሸክሟቸው ከተጓዘ በኋላ አንድ ሥፍራ ላይ እንደ ዝናብ ያዘንባቸዋል። ለዚህም ነው አንዳንድ ጊዜ "እንቁራሪት ዘነበ" ተብሎ እንደ ተአምር የሚነገረው።*
- *ከሰውነት ክብደት አንፃር እጅግ በጣም ጠንካራ የሚባለው ፍጥረት ሪኖሰረስ ቢትልስ የተባለ የጢንዛዛ ዝርያ ሲሆን የሰውነቱን ክብደት በ850 እጥፍ የሚበልጥ ሸክም በጀርባው ላይ ተሸክሞ መጓዝ ይችላል።*
- *አዞ ምግቡን ፍለጋ ሲሻ እና በወንዝ ውስጥ እስከ ወለሉ ድረስ ለመስመጥ ሲያስፈልገው ተለቅ ተለቅ ያሉ ድንጋዮችን ይውጣል።*
- *ጃርት በሰውነቷ ላይ 25000 በጥቁር እና ነጭ ቀለማት የተዥጎረጎረ ጦር መሰል እሾሆች አሏት።*
- *በደቡብ አሜሪካ አንዳንድ ስፍራዎች ውስጥ ምስጥ ልክ እንደ ፈንዲሻ ተቆልቶ ይበላል።*
- *ማንኛውም ሥጋ በል አውሬ በመብረቅ ተመቶ የወደቀን እንስሳ ለመመገብ አይችልም።*
- *•በደቡብ አሜሪካ አንዳንድ ስፍራዎች ውስጥ ምስጥ ልክ እንደ ፈንዲሻ ተቆልቶ ይበላል።*
- *•ማንኛውም ሥጋ በል አውሬ በመብረቅ ተመቶ የወደቀን እንስሳ ለመመገብ አይችልም።*

# ግዮን ፩

- ግዮን በአንድ ዓመት ውስጥ የ45 ዕትሞቹ እንግዶቹ ምን ብለው ነበር
- የአንድ ዓመት የግዮን መጽሔት ቃለ ምልልስ የተሰሩ ሰዎች ስም ዝርዝር
- ለግዮን መጽሔት በአምደኛነት በተሳታፊነት በተጋባዥ ፀሐፊነት እነማን ተሳታፉ







በ1ኛ ዓመት



# የግዮን ልዩ ዕትሞች

ግዮን መጽሔት ለህትመት ከበቃች እነሆ አንድ አመት ሞላት : : ባለፉት አርባ አምስት እትሞቻችን በኢትዮጵያ ጉዳይ ትልቅ ተሳትፎ የነበራቸውን ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች፣ የሃይማኖት አባቶችና በተለያዩ የሙያ ዘርፍ ትልቅ አበርክቶ የነበራቸውን ታዋቂ ሰዎች የመጽሔታችን እንግዶች ነበሩ : : ለማስታወስ ያህል በ45 እትም ውስጥ ቃለ ምልልስ ካደረግንላቸው ሰዎች መካከል ከተናገሩት የተቀነጨበውን ለአንባቢያን ትውስታ ይሆን ዘንድ ከሁሉም ዕትሞች እንዲህ ባለ መልኩ አቅርበንላችኋል : :
















## እስክንድር ነጋ

እኔ የዚያ ሰው ድርጊት ምን እንደሆነ በገባኝ በዚያ ቅጽበት በየሥርቻው የጦር መሳሪያ ይዘው የተደበቁት ወታደሮች አካባቢውን ተቆጣጠሩት:: ያኔ ልጄ ሁኔታውን ተመልክቶ ይደነግጥብኛል በሚል የተረበሸ መንፈስ ውስጥ ሆኜ ለባለቤቱ ሠርካለም ልጃችንን መጥታ እንድትወስደው ስልክ ደወልኩላት:: እሷ ወዳለንበት እስክትመጣም ወታደሮቹ እኔና ልጄ የነበርንባትን መኪና ዙሪያዋን ከበቧት:: አንድ ሲቪል የለበሰ ፖሊስም ወደ እኔ ቀረብ ብሎ ከመኪናዬ እንድወርድ ጠየቀኝ:: ‹‹ልጄ እያለ እንዴት እወርዳለሁ? እናቱ ትወስደዋለችና እሷ እስክትመጣ አንድ አፍታ ታገሰኝ›› አልኩት:: ለደግነቱ ብዙም ሳትቆይ ሠርካለም መጣች:: እንደመጣች ልጃችንን ሰጧት:: ከመኪናዬ ወርጄ ፖሊሶቹ ወዳዘጋጁልኝ ሚኒባስ ውስጥ ገባሁ::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## አንዱአለም አራጌ

ሞትን የተመኘሁት በሰላማዊ ትግል በሀገሬ ለውጥ ለማምጣት ከነበረኝ ህልም፣ ዓላማና ዕምነት አንፃር ነው:: ከመነሻው ወንድሙን ከማፍቀር በቀር ከቶውንም ለመግደል ባለማሰብ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ወደ ፖለቲካ የሚገባ ሰው፣ ተስፋ የቆረጠ ሳይሆን ተስፋ ያለው ነው:: የዚህች ሀገር ችግር የሚቀረፈው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነባራዊና ወቅታዊ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሚያገኘው በሰላማዊ ትግል ነው ብዬ ስል፤ ትግሉ የሚያስከፍለውን የሕይወት መስዋዕትነት ዋጋ ራሴው ለመክፈል ዝግጁ ነኝ ማለቴ ነው:: ስለዚህ እነሱ የተለያየ ባጅ ቢለጥፉልኝም ሰላማዊ ትግልን የኃይማኖት ያህል አምንበታለሁ:: እኔ ስታሠር ሰላማዊው ትግል ሊቋረጥ እንደማይችል ተስፋ አድርጌአለሁ:: ብሞትም እንደዛው::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## ንግስት ይርጋ

የማዕከላዊ ቆይታዬ በምድር ሲዖል ውስጥ የመኖር ያህል ነው:: በእኔ አስተያየት ያ ሥፍራ ፖሊስ ትክክለኛውን ሙያዊ ምርመራ የሚያካሄድበት ቦታ አይደለም:: በቃ ሲዖል ነው! ለአራት ወራት የቆየሁበትን ያን የሰቀቀንና የጭንቅ ቦታ ከዚህ በተሻለ ቃላት ልገልፀው አልችልም:: በማዕከላዊ ወንዶች ሌሊት እየተወሰዱ መመርመራቸው የሚታወቅ ነው:: ሴቶችን በተመለከተ ግን ምናልባት የሌሊቱ ምርመራ የሚጀመረው በእኔ ሳይሆን አይቀርም:: በእኔ ላይ ከባድ ምርመራ በሌሊት ሲካሄድብኝ በዚያ የነበሩት ሴት እሥረኞች ተረብሸዋል:: ታመዋል:: ራሳቸውን መቆጣጠር ባለመቻላቸው፤ የሚያስቀምጣቸው፣ የሚያስመልሳቸው ነበሩ:: እና የማያልፍ ነገር የለምና እነዛ ከባድ ጊዜያቶች አለፉ::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## በቀለ ገርባ

ይሄን ባልናገር ይሻል ነበር:: ምክንያቱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን ስልጣን ነበራቸው? በግላቸው ቅን እና መልካም ሰው ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን በእውነቱ ስልጣን ነበራቸው? የመወሰንና የመሻር ስልጣን ነበራቸው? አንደ አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊሰራ የሚገባውን ነገሮች ይሰሩ ነበር ለማለት ያስቸግረኛል:: ስለዚህ ስልጣን ኖሯቸው ስልጣን ለቀቁ ቢባል ራስን ማሞኘት ይሆናል:: ከኢሕአዴግ አንድ እጅ ወደ ሌላው እጅ፣ ቢተላለፍም ብዙ የሚያመጣው ለውጥ ያለ አይመስለኝም:: ስልጣን መልቀቅ ማለት የግለሰቦች ሳይሆን የሥርዓት ነው:: እንዳለ ቡድኑ ወይም ፓርቲው ሲለቅ ነው ስልጣን ለቀቀ የሚባለው እንጂ በመካከላቸው ከአንዱ ወደ አንዱ ቢያዘዋውሩት የአሁኑ ጠ/ሚኒስትር፣ የቀድሞው ጠ/ ሚኒስትር ከመባል ውጪ የሚፈይደው ነገር የለም:: በዚህ ሥርዓት ወደፊት የሚነሳውም በራሱ መንገድ የወሳኝነት ሚና ይቀጥላል ብዬ መናገር ያስቸግረኛል::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## አህመዲን ጀበል

እስከ ነሐሴ ሦስት ቀን 2004 ነገሮች በጥሩ ሁኔታ እየሄዱ ነበር:: ነሐሴ 3 ጨለማ ክፍል አስገቡኝ:: 13 ቀን እዚያ አቆዩኝ:: እጄን ወደላይ አስረው ለ12 እና 13 ሰዓታት ግርፊያና ማንገላታት ፈጸሙብን:: እንግዲህ ጊዜው ረመዳን የመጨረሻዎቹ 10 ቀናት በይበልጥ ወደ ፈጣሪህ የምትቃረብበት ጊዜ ነው:: እኛ በመከራና ሥቃይ ነበር ያሳለፍነው:: ቤተሰብ እንኳ ማግኘት አልቻልንም ነበር:: እኔ ጨለማ ቤት ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በወንድሞቼ (በእነ አቡበክር) ላይ ይደርስ የነበረው ግፍና መከራ የሚያሳቅቅ ነበር:: የአቡበክር መታመም ሕክምና እንዲያገኝ ሌሊት በር እየደበደብን ስንጮህ ሰሚ ማጣጣችን፣ እስልምናን በማንቋሸሽ መርማሪዎች ያደርሱብን የነበረው የሥነልቦና ቀውስ፣ እኛን በማንቋሸሽ ይደርስ የነበረው ስቃይ መቼም የማይረሳ ነው::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## ናትናኤል መኮንን

የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የምታውቀው ነው:: በማስረጃና ተጨባጭ እውነት ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ የፍርድ ውሳኔ የለም:: ይልቁኑ የገዥዎችን ፍላጎትና ትዕዛዝ ለማስፈፀም ነው የቆመው:: ስለዚህ መጀመሪያውኑ የፈጠራ ክስ ነበር:: እውነት ለመናገር ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ወንጀል ይጻፋል ወይም እንደማንኛውም ድርሰት ይደረሳል እንጂ ይፈፀማል ይሰራል ብዬ አላምንም:: የፈጠራ ክሱ ፍርድ ቤት ቀረበ:: ፍርድ ቤት ደግሞ ያን የፈጠራ ክስ ተቀብሎ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ በሌለበት ተፈረደብን ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ የቀረበብን በአደባባይ የተናገርናቸው ጥያቄዎች በፖለቲካ ድርጅታችን ውስጥ ያደረግናቸው ትግሎ፣ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው እንጂ በፍፁም ከሽብር ወንጀል ጋር በተያያዘ የቀረበብን ተጨባጭ ማስረጃ የለም:: ስለዚህ እንድንታሰርና እንዲፈረድብን ስለተፈለገ ሽብርተኛ የሚል ተቀፅላ ተለጥፎብን ተፈረደብን:: የተፈረደብን ስለተከሰስን ብቻ ነው እንጂ ማስረጃ ስለቀረበ አይደለም::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## ተስፋሚካኤል አበበ (አበበ ቀስቶ)

ህክምና ማጣት የእስር ቤት ታላቁ ፈተናና ስቃይ ነበር:: እውነት እንደ ዜጋ ሕዝብን አስተዳድራለሁ ከሚል መንግስት የማይጠበቅ በእኔ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ላይ እየተከሰተ ያየነው አንድን በፖለቲካ አቋሙ ምክንያት የተያዘን ሰው ለማንበርከክ ህክምና መሰረዝ የህክምና ቀጠሮ ማስተላለፍ፤ ዓመታት ቆይቶ እንደገና ማስጀመር የመሳሰሉት ግፎች ማረሚያ ቤት ውስጥ ይፈፀማሉ:: እነኚህ ነገሮች በጣም ያማሉ:: ይህ በእኔ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ላይ ይፈፀማል:: በወቅቱ ብታከም በቀላሉ ይድን የነበረው ነገር አሁን ግን ህክምና ሳላገኝ ሶስትና አራት አመት በመቆየቱ ምክንያት የማይድንበት ደረጃ ላይ ደርሶ ዛሬ ቀኝ ጆሮዬ የማይሰማ ሆኗል::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## ማሙሸት አማረ

ማዕከላዊ እንደሚታወቀው ለአራተኛ ጊዜ የገባሁበት ነው:: በዚህ ስርዓት ምንም የተለወጠ ነገር የለውም:: ሁልጊዜም ቢሆን ምድራዊ ሲኦል የመከራ ምንጭ ነው:: ማዕከላዊ ማለት ምድራዊ ሲኦል ነው:: እጅግ ብዙ መከራ የሚታይበት:: የሰው ልጅ እንደ ሰው የማይታይበት:: ሰው የሆኑ ሰዎች ወንድሞቻቸውን እህቶቻቸውን አባት እናቶቻቸውን ወገኖቻቸውን እንደ ሰው ሳይቆጥሩ እንደ አውሬ የሚበላበት:: የሰው ልጅ ስጋ የሚበላበት የሚቆረጥበት ማለት ነው ማዕከላዊ:: እኔም ሌሎች ጓደኞቼም ወገኖቼም እዚያ ውስጥ ብዙ መከራ ታልፎ ነው እዚህ የደረስነው::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## አሕመድ ሙስጠፌ

ማንኛውም ማኅበረሰብ የሚያልፍበት የዕድገት ደረጃ አለ:: በታሪክ አንድ ሕዝብ ከፍ የሚልበት ሆነ መውረዱ የሚለካበት መስመሮች አሉት:: አንድ ማኅበረሰብ መውደቁ የሚታይበት የሕንፃ አለመኖር ወይም የመንገዱ መበላሸት ጉዳይ አይደለም:: የአንድ ማኅበረሰብ ውድቀት መገለጫው ሥነ-ልቦናው ነው:: በፍርሃት ማቅ ውስጥ የገባ፣ የበታችነት የመሸነፍ ስሜት የተሰማው ተቃራኒውን አካል አግዝፎ የማየት ስሜት የተሰማው፣ በደልን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ፣ መሰል ማኅበረሰብ በቁስ ምን ቢራቀቅ፣ የሚያምሩ ሕንፃዎችን ቢሰራ ከሙት አይሻልም:: እኛን ለእሥር የዳረገን ይህንን ጉዳይ ለመስበር መንቀሳቀሳችን ነው:: የዚያን ጊዜው ማኅበረሰብ እምቢ ለጥቃት ባይ ሆነ:: የእኛም እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ታሪክ አንድ መስመር ተደርጎ፣ እርከን ወይም ኬላ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## እማዋይሽ ዓለሙ

በቅርቡ በሆነ ሚዲያ ላይ ስለዚህ መንግሥት ሰብዓዊ መብት አያያዝ ሲናገሩ ሰምቻለሁ:: እና በጣም አዝኛለሁ:: ማስተካከል ነው እንጂ የሚሻለው መካድ በጣም ያሳፍራል:: እኔ ማዕከላዊ በከፍተኛ ደረጃ ነው የተደበደብኩት:: ማታ ማታ ዓይኔ ተሸፍኖ በሰንሰለት ታስሬ ለሴት ልጅ የማይገባ ዘግናኝ ጭካኔ ተፈፅሞብኛል:: በጣም የሚገርመው የደረሰብኝ ስቃይ ምርመራ ላይ እያለሁ ነበር በአሜሪካ ሬድዮ ጣቢያ የተጋለጠው:: የተፈፀመብኝ ግፍ ብዙ ነው:: በደብደባ ብዛት ብዙ ጊዜ ደም በደም ሆኛለሁ:: አሰቃቂና ዘግናኝ ነበር:: እስካሁን በሰውነቴ ላይ ያሉት የድብደባው ምልክቶች አልጠፉም::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## ዶ/ር ታየ ንጉሴ

ይህ ነው ትልቁ የዚህ ስርዓት ችግር:: ስርአቱ በዳይና ተበዳይ ብሎ የከፈላቸው ህዝቦች አሉ:: ማን ነበር በዳዩ ህዝብ? ለጊዜው በዳይነትን በአንድ ህዝብ ላይ ጭኗል:: ተበዳይነትን ደግሞ ለተቀሩት የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰጥቷል:: ሙሉ ለሙሉ ሁሉ የተሟለለትና ድህነት የማይነካው ደሴት ላይ የሚኖር ህዝብ አለ እንዴ ኢትዮጵያ ውስጥ? ይህ ስርዓቱ የፈጠረው የህልም አለም ነው::

**ቅፅ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም**

## ዶ/ር ብርሃኔ ረዳኢ

በትክክል ቁጥሩን ማወቅ ይቸግራል:: አንተም የጠየከኝ ትክክለኛ ቁጥሩን ሳይሆን ግምቱን ስለሆነ ከዚህ በፊት በውይይት ላይ እንደሰማሁት ከሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ወደ 60 000 የሚሆኑ በተለያየ ደረጃ የኩላሊት ስንፈት ያላባቸው ሰዎች አሉ ተብሎ ይገመታል:: ከዚህ ቁጥር ውስጥ ምን ያህሉ ወደ ህክምናው ጣቢያ መጥተው ክትትል እያደረጉ ነው የሚለውን ማወቅ ይቸግራል:: የኩላሊት ታካሚዎች ማኅበር የያዘውን ሌሎችንም ደምረህ እስከ 400 ሰው በኩላሊት ንቅለ ተከላ ስርዓት ውስጥ የገቡ ሰዎች አሉ:: እነዚህ ግን በአንድ ዓመት የመጡ ወይም ንቅለ ተከላውን ለማካሄድ በተለያያ ደረጃ ያሉ ናቸው:: አዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ የግል ጤና ተቋማት የኩላሊት እጥበት የሚያካሄዱ አሉ፤ መረጃው ወደ አንድ ማዕከል የሚመጣበትና የሚሰበሰብበት አሰራር መኖር አለበት::

**ቅፅ 1 ቁጥር 2 ቅዳሜ መጋቢት 15 2010 ዓ.ም**

## ብርጋዲየር ጄነራል ተፈራማሞ

ማዕረግ አንሶኛል ምናምን የሚለውን አጀንዳ ጥሎ፤ በጉዞ ወቅት ልቡን የሰበረውን ክስተት መድረኩ ላይ መወርወር ጀመረ:: “ሥርዐቱ ትክክል አይደለም! የአማራ ሕዝብ እንኳን ሊለማ ቀርቶ ያለውን እያሳጣነው ነው! ይሄም የሆነበት ዋናው ጉዳይ የኢሕዴን መሪዎች ከአማራ ጋር የሚያቆራኛቸዉ ነገር ባለመኖሩ ነው:: የአማራን የልብ ትርታ የሚያዳምጡ አይደ ሉም”በሚል ፍጥጥ ብሎ ተነሣባቸው:: አማራ ክልል በዋናነት በድህነት እየተገረፈ ያለውና ወደ ልማት እንዲገባ ያልተደረገው “የኔ” የሚለው ተቆረቋሪ መሪ በማጣቱ ነው:: ከተለያየ ቦታ አማርኛ ቋንቋውን ስለተናገረ ብቻ የተሰበሰበ እንጂ ለአማራ ተቆርቋሪ መሪ የመሆን ፍላጎት ያላቸው አይደሉም … የሚል አጀንዳ ተነሣ:: ስብሰባው በከረረ ሁኔታ ተጋጋለ:: “ክልሉ እየሞተ ነው! መብራት የለም! መንገድ የለም! የመሠረተ-ልማት እጦት ተባብሷል፤ በክልሉ መሬት ላይ የመብራት መስመር ወደ ሌላ ክልል ረግጦ እያለፈ፤ የአማራ ሕዝብ ግን መብራት አያገኝም:: ስለዚህ ይሄ ሕዝብ በዚህ ሥርዐት በግልፅ የኢኮኖሚ ጦርነት ተከፍቶበታል” የሚል ጠንካራ ትችት መጣ፡

**ቅጽ 1 ቁጥር 3 ቅዳሜ መጋቢት 22 2010 ዓ.ም**
















## አቶ ልደቱ አያሌው

ዶክተር አብይ ብቻቸውን ያደርጉታል ወይ? አይመስለኝም እንደ አቶ ሽፈራው መግለጫ ከሆነ በቡድን ነው የሚሰራው፤ እርሳቸው የቡድን መሪ እንጂ ብቻቸውን የሚያደርጉት ነገር የለም ብለው ነው የተናገሩት:: ስለዚህ እነዚህ ያነሳሃቸው ጉዳዮች ሁሉ በኢህአዴግ ታምኖባቸው ወደ ተግባር መለወጥ ያለባቸው ናቸው:: የመሪው መመረጥ በጣም መሰረታዊ የሆነ ለውጥ ያመጣል ብለን መጠበቅ የለብንም:: ስለዚህ ኢህአዴግ ዝም ብ ሎ በሌሎች ጉዳዮች ዙሪየያ ጭምጭምታ መሄድን ትቶ ቀጥታ ወደ ፖለቲካው መፍትሔ መግባት አለበት::

**ቅጽ 1 ቁጥር 3 ቅዳሜ መጋቢት 22 2010 ዓ.ም**

## አቶ ቡልቻ ደመቅሳ

ለውጥ ይኖረዋል፤ ለውጡ ግን ኢህአዴግ የሚፈልገው አይነት ሰው መሆኑ ነው:: ህዝቡ የእሱን መመረጥ ይፈልገው አይፈልገው አላውቅም:: እኔ የራሴን ሃሳብና እምነት ነው የምናገረው:: የሚገርምህ ነገር ዶክተር አብይ ኦሮሞ ስለሆነ አንዳንድ ሰዎች እየደወሉልኝ “እንኳን ደስ ያለህ” ይሉኛል (ሳቅ) ነገሩ እንዲህ ቀላል ነገር አይደለም፡በቅርቡ የሚያውቁት ሲያወሩ እንደ ሰማሁት ከሆነ ችሎታና ብቃቱ ሊኖረው ይችላል::

**ቅጽ 1 ቁጥር 3 ቅዳሜ መጋቢት 22 2010 ዓ.ም**

## አቶ ተመስገን ዘውዴ

እንግዲህ ዶክተር አብይ የመቶ ሚሊየን ህዝብ ጠቅላይ ሚኒስቴር ነው የሚሆነው፤ በአሁኑ ሠዐት ትልቁ ጉዳይ አንድነታችን መሸርሸሩ ነው:: በኢህአዴግ 27 ዓመታት አገዛዝ አንድ ያጣነው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያዊታችንን ነው:: ኢትዮጵያዊነታችን ተሸርሽሯል፤ የታሪካችን የአንድነታችን መሠረት ኢትዮጲያዊነታችን ነበር:: ሁላችንም ወደ መንደራችን ተመልሰን የምናስብ ከሆነ፣ በመንደር ደረጃ የምናስብ ከሆነ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ላትኖር ትችላለች::ስለዚህ ዶክተር አብይ የሁሉም ነገር ማጠንጠኛ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ፤ ዋና ተግባራቸውም ህዝቡን ማረጋጋትና የአንድነት መሰረታችን ኢትዮትያዊነት መሆኑን በማመን ደግመው ደጋግመው ሊሰሩበት ይገባል::

**ቅጽ 1 ቁጥር 3 ቅዳሜ መጋቢት 22 2010 ዓ.ም**

## በፍቃዱ ዘሀይሉ

ዶክተር ዐብይ ወደ ላይ የመጡት በህዝብ ግፊት ነው ብዬ አስባለሁ:: እሳቸው ይመረጡልኝ ብሎ ሳይሆን ህዝባዊ ተቃውሞዎች ለእርሳቸው ትልቅ እድል ስለፈጠረላቸው ነው ብዬ ነው የማምነው:: የእርሳቸውን ያህል ኢህአዴግን ጥፋተኛ ነው ብሎ የተናገረ የኢህአዴግ አባል እስከዛሬ ድረስ አላየንም:: ይህ መልካም ጅማሮ ነው ግን በቃላት ብቻ መወሰን የለበትም:: ውጤቱ በተግባር መታየት አለበት:: ይታያልም የሚል ተስፋ አለኝ:: ተስፋዬ የሚመነጨው የኢህአዴግ አባል ስለሆኑ ሳይሆን የመጡበት መንገድ ላይ ነው ተስፋ የማደርገው:: በህዝብ ግፊት ነው ወደዚህ ደረጃ የመጡት::

**ቅጽ 1 ቁጥር 4 ቅዳሜ ሚያዝያ06 2010ዓ.ም**

## አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማሪያም

እኛ ከህወሓት ጋር የመጀመሪያው ፀባችንና ልዩነታችን የዋልድባ ገዳም ነው:: ሁለተኛው የድን ምስክር፣ የቤተልሔምን ምስክር የመሠሉ ወደ ትግራይ የመውሠድ ጥረት ነው:: የራስ ዳሽን ተራራን የተነጠቅን ሰዎች ዛሬ እንዴት የቤተልሔም ምስክር፤ የማኅበረ ሥላሴ ገዳም፤ የጎንደር መሬት ለሱዳን ተላልፎ መስጠት፤ የራስ ዳሽንን ወደ ትግራይ መከለል አግባብ አይደለም እያልኩ ነው:: ይሄ የእምነት ጉዳይ ነው:: ዝም ተብሎ የሚታለፍ አይደለም:: ደብረ ቢዘንን የመሠለ ገዳማችንና ቅርሳችንን አሳልፈን ሰጠን:: አሁን ሌሎችን አሳልፈን ልንሰጥ እየተዘጋጀን ነው:: ምንም ያልመሰላቸው ሰዎች ዝም ይበሉ፣ እኔ ግን እናገራለሁ:: የታሪክ ዝርፊያ አስፈላጊ አይደለም:: ታሪኩን ላባለ ታሪኩ ነው መተው ያለበት::

**ቅጽ 1 ቁጥር 5 ቅዳሜ ሚያዝያ 20 2010ዓ.ም**

## አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት

በቤተ ክርስትያን ዙሪያ የተሠገሠጉ ሰዎች መሰብሰብያ አድራሻቸው ውሸት ነው እያፈለቀ ያለው:: የእግዚአብሔር ቃል እንዳይነገርበት፣ ዕውነት እንዳይሰበክበት ከፓትሪያርኩ ጽ/

ቤት ጀምሮ እስከ ገጠሯ ቤተክርስትያን ድረስ የራሳቸውን ሰው በማስቀመጥ፤ ህዝበ ክርስትያኑ ጠዋት ለመሳለም፣ ፀሎት ለማድረግ ሲመጣ የሚነገረው ስለ ፖለቲካና ስብስባ እንጂ የእግዚአብሄር ቃል አይደለም:: እንግዲህ እኛ ከተያዝንበት ቀን ጀምሮ አንድ ጳጳስ ወይም ኃላፊ ከአገረ ሥብከት ወይም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የተናገረ፣ ድርጊቱን ያወገዘ ሰው የለም:: “ይሄ ገዳም እየፈረሠ ነው፤ ይሄ ገዳም እየታረሠ ነው፤ እነዚህ መነኮሳት እውነታቸውን ነው” ያለ አካል የለም:: እኛንም ማብራሪያ የጠየቅን አካል የለም::

**ቅጽ 1 ቁጥር 5 ቅዳሜ ሚያዝያ 20 2010ዓ.ም**

## ዘላለም ወርቅአገኘሁ

ማዕከላዊም ሆነ ቂሊንጦ አልያም ሌሎች እሥር ቤቶች ውስጥ የታዘብኩት አንድ ነገር ማንበብ ከማይችለው እስከ ሊቁ፤ እኛ ሰብዓዊ መብት ጥሠት፣ የዩኤን ቻርተር የምንለውና ሌሎች ነገሮች የማይገባቸው ግን እየደረሰ ያለው የአገርና የህዝብ ችግርን የተረዱ፣ ሥርዓቱ ፍፁም አምባገነን በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ መቀየር አለበት ብለው የሚያምኑና ያንን ዕውን ለማድረግ ሠላማዊ ትግል ያደረጉ፣ የሠዎች ያለ አግባብ መታሠርና መገደልን “ለምን” ብለው የጠየቁ፣ የጻፉ በርካታ ሰዎች በእሥር ቆይታዬ አግኝቻለሁ::

**ቅጽ 1 ቁጥር 6 ቅዳሜ ግንቦት 04 2010ዓ.ም**

## አድማሱ ገበየሁ (ዶክተር ኢንጅነር)

አንድ ጊዜም ቢሆን ሕዝቡን ምን እንደሚፈልግ ላዳምጥ ብሎ አያውቅም:: በተቃራኒው ሕዝቡ እንዳይደራጅ፣ ሀሳቡን በነፃነት እንዳይገልፅ፣ በተለያዩ መንገዶች በማፈን ሕዝብን ማሰቃየትና መግደልን ነው ኢህአደግ የመረጠው:: ሕዝብና ኢህአዴግ ሆድና ጀርባ የሆኑትም ለእዚህ ነው:: ሕዝቡ በታፈነ በተጨቆነ ቁጥር ማመፅና መሪው ላይ መነሳቱ የማይቀር ነው:: በኢህአዴግ ዘመን የሕዝቡን ፍላጎትና ሀሳብ እናውቃለን ባዮች የመንግስት ፕሮፖጋንዳ መጠቀሚያ የሆኑት ሬድዮና ቴሌቭዥን እንጂ ፓርቲው አልነበረም:: ኢህአዴግ ሕዝብን እንደሚለው በትክክል የሚያውቀው ቢሆንማ ኖሮ ይሄ ሁሉ ሕዝቡ እንዴት እስኪ.ቃወመው ይጠብቅ ነበር? በህዝብ ስሜት ደረጃ ካየነው ግን የአሁኑም የበፊቱም ተመሳሳይ ነው::

**ቅጽ1ቁጥር 7 ቅዳሜ ግንቦት18 2010ዓ.ም**

## አንዳርጋቸው ፅጌ

እኔ እዚህ አገር በ1983 ዓ.ም ስመጣ ኢህዴንን ወይም ሌላውን ድርጅት አይደለም የማውቀው:: ያኔ የማውቀው ህወሃቶችን ነው:: እንግሊዝ አገር ሆኜ ህወሃትን መደገፍ ፋሽን ባልነበረበት ሰአት እኔ ነበርኩ የምደግፌው:: ከእነሱ ጋር ያለኝ ግንኙነት በመርህ ላይ የተመሰረተ በከፍተኛ ወዳጅነት ላይ የተመሰረተ እንጂ በጠላትነት ላይ የተመሰረተ አልነበረም ::ግን ስህተት ሲሰሩ በአድርባይነት የማለፍ ባህሪይ የለኝም:: እኔ በምናገርበት ሰአት ላይ ራሳቸውን መመርመር ነው እንጂ የሚገባቸው በጠላትነት ፈርጀው ማየት አልነበረባቸውም:: እነሱን ሊጠቅሙ የሚችሉ ያላቀረብኳቸው ሃሳቦች የሉም:: እኔ ክርክሬ በሙሉ ድርጅቱን ይጠቅማል ፣ድርጅቱን በህዝቡ ተወዳጅ ያደርጋል በሚል መልኩ ነው አቅርብ የነበረው::ያልኳቸው ነገሮች ሁሉ በተግባር ውለው ቢሆን ኖሮ እንደ ጣኦትነት የሚመለኩበት ሁኔታ መፍጠር እንችል ነበር::

**ቅጽ1ቁጥር 8 ቅዳሜ ግንቦት25 2010ዓ.ም**

## አቶ ያሬድ ጥበቡ (ከአሜሪካ)

“ጋራንግን እንርዳው” ብለው ወደ ሱዳን ጦር መሣሪያና ወታደርም በሚልኩበት ጊዜ ታምራት ያንን ይቃወማል:: “ምን አገባህ?” ዓይነት ስሜት ነው የነበራቸው እነሱ:: ታምራት ሥልጣን ነበረው ለማለት ከባድ ነው:: በሌላ በኩል ታምራት የነርሱን ተቀባይነት ለማግኘት ሲል ከመንገዱ ወጥቶ ይሄዳል:: ለምሳሌ፡- ወደ ባሌ ወይም ሐረር ሄዶ “‘ይኼ ሽርጣም ሱማሌ’ ይልህ የነበረውን ነፍጠኛ በለው” የሚል አነጋገር መጠቀሙ በጊዜው ተዘግቧል:: ታምራት በጊዜው ከራሱ ጋር ሙሉ ለሙሉ የሚያጣላው ወቅት ላይ ነው የነበረው:: ሥልጣኑ ሳይኖረው ሹመቱ የነበረው ሰው ነው::

**ቅጽ1ቁጥር9 ቅዳሜ ሰኔ02 2010ዓ.ም**
















## ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም

ኬንያ ውስጥ ተመሳሳይ ወደ20 አማራጭ ቴሌኮምዩኒኬሽኖች አሉ:: የኛ ግን ሞኖፖሊ ነው:: ሞኖፖሊ ብዙውን ጊዜ እድገትን ያቀጭጫል:: በዚህ ምክንያት ኢትዮ ቴሌኮም ከዘመኑ ጋር አላደገም:: ስለሌሎቹ ዘርፎች ባለው ኢኮኖሚስት ስላልሆንኩ ልለፋቸው:: ግን የኢትዮጵያ አየር መንገድ 75 ዓመቱ ነው፤ ከተቋቋመ:: የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ተሸክሞ ዓለምን ይዞራል:: የውጭ ሀገር ባለድርሻ በዚህ ውስጥ መግባቱን እኔ አልደግፈውም::

**ቅጽ1ቁጥር9 ቅዳሜ ሰኔ02 2010ዓ.ም**

## አስቴር ስዩም

ቃሊቲ ለሁለት ወራት ባለቤቴ፣ ወንድሜ መጥተው እንዳይጠይቁኝ ተከልክለዋል:: እናቴ ቃሊቲ ከገባሁ በኋላ ስድስት ጊዜ መጥታ ጠይቃኛለች:: በልዩ ጥበቃ ታጅበን ለ30 ደቂቃ ብቻ ነበር የምንገናኘው፤ ለስድስተኛ ጊዜ እናቴ ስትመጣ፣ “ልጅሽ በእስር ቤት ውስጥ ፖለቲካ እየቀሰቀሰች ስለሆነ በልዩ ኬዝ ጥበቃ ስለሚያስፈልጋት ልታገኚያት አትችይም” ብለው አስለቅሰው ሕፃን ልጄን ይዛ እንድትመለስ አደረጉዋት:: “እንዳላገኛት የከለከሉኝ ልጄ ስለሌለች ነው” የሚል ነገር በውስጧ አስቀምጣ ከተመለሰች በኋላ “እስር ቤቱ ተቃጠለ” የሚለውን ወሬ በደፈናው ስትሰማ ውስጧ ያለው ነገር ተጨማምሮ ድንገተኛ የልብ ድካም ተከስቶባት ዳግም ላላገኛት፣ ዛሬ የምታስፈልገኝ እናቴ ያደረገችልኝን ውለታ ሳልመልስላት፣ ያለአባት ያሳደገችኝ እናቴን ዳግም ላላገኛት ወያኔ እናቴን ነጥቆኛል::

**ቅጽ1ቁጥር9 ቅዳሜ ሰኔ02 2010ዓ.ም**

## ጃዋር መሐመድ

በተለይ ደግሞ ሥርአቱ ወሳኝና አስፈላጊ ብሎ የሚኳዝበትን የሥልጣን ምሰሶ አቅም መስበር የታቻለበት ነበረ:: ከ300 በላይ እርሻዎች፣ ፋብሪካዎችና የተለያዩ ቦታዎች የወደሙበት፤ ሥርዓቱ አሁን ለደረሰበት የኢኮኖሚ ውድቀት ወሳኝ እርምጃ የተወሰደው ያን ጊዜ ነበር:: በሰአቱ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለእኛ ያለውን አመለካከት የለወጠበት ነው::አምስቱ የቁጣ ቀናት ከፍተኛ መሥዋእትነት የተከፈለበት ቢሆንም፣ አንዳንድ ስህተቶች የነበሩበት ትልቅ እንቅስቃሴ ነው:: ሌላኛው በቀለ ገርባን ለማስፈታት መጨረሻ ላይ ያደረግነው እንቅስቃሴ በጣም ወሳኝ ነበር::

**ቅጽ1ቁጥር10 ቅዳሜ ሰኔ16 2010ዓ.ም**

## አንዱአለም አያሌው

ኤርትራ ጋሉጅ የምትባል ከተማ ላይ ስንገናኝ እኔ ስለአቶ አንዳርጋቸው ብዙ የማውቀው ታሪክ አልነበረኝም:: ግን ሁለት ወር ለሚጠጋ ጊዜ አንድ ክፍል ውስጥ ብቻችንን አብረን ነበር የምናድረው፤ ከአንዳርጋቸው ጋር ለማሣለፍ ያንን ዕድል በማግኘቴ በጣም ዕድለኛ ነኝ:: እንዳገኘሁት ልብሴን ነው ያስወለቀኝ፤ የሲቪል ልብሴንና ጫማዬን አስወልቆ ወታደራዊ አልባሳትን እንድለብስ ትዕዛዝ ሰጠኝ:: ሁለተኛ በሕይወቴ አይቼ የማላውቀው ዲሲፕሊን አጋጥሞኛል:: በሥርዓት የሚኖር፣ ለእያንዳንዷ ደቂቃ ዋጋ የሚሠጥ፣ 24 ሰዓቱን ፕሮግራም አውጥቶ በዚያ የሚመራ ሰው እንደ እሱ በሕይወቴ ዓይቼ አላውቅም:: ለምንም ነገር የማይበገር፤ በምግብ በኩል እንኳን “ወሀከር” የሚባል እንጀራ አለ፤ ላልለመደው ሰው እጅግ በጣም አስቸጋሪ የሆነ ቀይ የማሽላ እንጀራ ነው:: ለሁለት ወር አብሬው ስኖር ከእርሱ ውጭ ሲበላ አላየሁትም:: በጣም ሆድ ያደርቃል፤ ሽንኩርትና ጨው የሌለው ምስር ወጥ ነው ከወታደሩ ጋር አብሮ የሚመገበው::

**ቅጽ1ቁጥር10 ቅዳሜ ሰኔ16 2010ዓ.ም**

## ስንታየሁ ቸኮል

ሁለት የታጠቁ ሰዎች ጠ/ሚኒስትሩና ካቢኔያቸው በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ከተቀመጡ በኋላ መድረኩ ላይ መግባት አለብን እያሉ ከጠ/ሚኒስትሩ ጠባቂዎች ጋር ይጋጩ ነበር:: “ታጥቃችሁ አትገቡም” ሲሏቸው፤ “የጥበቃ አባል ነን” የሚል ምላሽ ይሰጧቸዋል:: እነሱም “እስኪ መታወቂያ አሳዩን” ሲሉ የሰጧቸው መልስ ስለሌለ የግል ጠባቂዎቹ ተከላክለው መልሰዋቸዋል:: ሁኔታውን በግልፅ

ቦታው ላይ ስለነበርኩ ለመታዘብ ችያለሁ:: አደጋው ሆን ተብሎ ለጠ/ሚኒስትሩ የተሸረበና የተዘጋጀ፤ እሳቸው እንዳሉት በሙሉ የታገዘና ጥቅማችን ጎደለ በሚሉ ኃይሎች የተቀነባበረ እንደሆነ ግልፅ ነው::

**ቅጽ1ቁጥር11 ቅዳሜ ሰኔ23 2010ዓ.ም**

## ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

ሁላችንም እንዳየነው አንድ ወይም ሁለት ካልሆነ በስተቀር፤ የአማራ ክልልን ባንዲራም ሆነ የፌደራል መንግሥቱን ሰንደቅ ዓላማ በድጋፍ ሰልፉ ላይ አላየሁም:: ሕግ የሚከለክለው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራ ነበር በብዛት የታየው:: ስታድዮሙን ሙሉ ለሙሉ የሸፈነው የድሮ የኢትዮጵያ ባንዲራ ነው:: ይሄ በሕግ ተከልክሏል::እነዚያ ባንዲራዎች አንድ ሊያደርጉን እንደማይችሉ ዐይተን፤ በ1987 ዓ.ም. የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ የሚደምር፣ ሃይማኖታችንን በሙሉ የሚደምር፣ የተለያዩ ግለሰቦችንና ቡድኖችን የሚያግባባና ሁላችንንም አንድ የሚያደርግ ባንዲራ የቱ ነው? ብለን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ሦስት ላይ አስቀምጠልናል::

**ቅጽ1ቁጥር12 ቅዳሜ ሰኔ30 2010ዓ.ም**

## ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ

እኔ እስከማውቀው ድረስ የኮሎኔል በዛብህ ጉዳይ፤ አሁን ለመጣው ልዕካን ቡድን ስለመቀረቡ መረጃው የለኝም:: ይሄ ደግሞ፣ ኢህአዴግ በሌላ አገር ያሉ ምርኮኛ እስረኞችን ለማስለቀቅ ላለፉት 27 ዓመታት ከታየው ያለመፈለግ ስሜት ለይቼ አላየውም:: 'ኢህአዴግ እስረኞችን ልቀቁ፤ በዚህ ዙሪያ እንደራደር' ብሎ አያውቅም::እንዲያውም አንድ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሶማልያ ውስጥ ኢህአዴግ አዝምቶ ነበር:: ከአንድ ከሁለት ዓመት በኋላ፤ 'ሽብር ብላችሁ አዘመታችሁ፤ በነገሩ ምን ያህል ጉዳት ደርሷል? ምን ያህል የመከላከያ ሠራዊት አባላት ቆሰሉ? ሞቱ? ምን ያህል ወጪስ ወጣ?' የሚሉ ጥያቄዎችን በሰዓቱ የፓርላማ አባል ስለነበርሁ አንሥቼ ነበር፤ የተሰጠኝ መልስ ግን 'ለሽርሽር አልሄዱም' የሚል ነው፤ 'ዝርዝሩን የማቅረብ ግዴታ የለብንም' ነው የተባልነው::

**ቅጽ1ቁጥር12 ቅዳሜ ሰኔ30 2010ዓ.ም**

## የቀድሞው ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ዴሞክራሲን በትክክል ለማስፈን ከጅምሩ እየሠራ ነው:: የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተፈትተዋል፤ በውጭ ሀገራት የሚገኙና ርቀው በሌላ መንገድ ላይ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ራሳቸው መግባት ጀምረዋል::እነዚህን ወገኖች እሱ 'ተቃዋሚ አይደላችሁም ተፎካካሪ ፓርቲዎች ናችሁ' እያለ ነው የሚገልፃቸው፤ ያገባኛል ባይ መሆናቸውን በአደባባይ መስክሮላቸው፣ ነፃ ሆነው እንዲከራከሩ እንጂ መሽፈት አያስፈልግም እያላቸው ነው ያለው:: በጣም ትሁትና አስተዋይ ሰው ነው:: መልካም ራዕይ የሰነቀ ሰው ነው:

**ቅጽ1ቁጥር13 ቅዳሜ ሐምሌ7 2010ዓ.ም**

## ሠዓሊ ለማ ጉያ

ኢትዮ-ኤርትራ የአሁኑ ግንኙነት በእውነቱ ትልቅ ነገር ነው:: ህዝቡ ከዳር እስከ ዳር ተገናኝቷል፤ ተደስቷል:: የህዝቡን ልባዊ ፍላጎት ተረድቶ፣ እርሱን ማክበርና ማፅደቅ ብቻ ነው የሚያስፈልገው:: ጠ/ሚ ዐቢይ ቀንጆ ሥራ ጀምሯል፤ የሚያስደስትና የሚያኮራ ጅማሮ ነው የፈፀመው:: ነገር ግን ይህንኑ በአዋጅ ማጽደቅ፣ ማስደገፍ ያስፈልጋል:: ከዚህ በፊት ተናግሪያለሁ፤ የነፕ/ር መስፍን፣ ፕ/ር መረራ፣ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ እና መሰል ሊቃውንትን ምክር ባለመስማታችሁ ነው ይሄ ነገር የመጣው ብዬ በደብዳቤ ለመለስ ነግሬዋለሁ::

**ቅጽ1ቁጥር13 ቅዳሜ ሐምሌ7 2010ዓ.ም**

## ዶ/ር በረከት ብርሃኔ (የኤርትራ ተወላጅ)

በህዝቡ በኩል ሁልጊዜም ምኞትና ናፍቆት አለ:: በተለይ ከኢሮብ እስከረማ አዲቋላ ያለው ህዝብ ከኤርትራ ወንድሞቹ ጋር መቼ እንደሚገናኝ በሰቀቀን፣ በናፍቆትና በፍቅር ለዘመናት ሲሰቃይ ነው የኖረው:: አስቀድሞ ከፖለቲከኞች በፊት ሄዶ የፍቅር ድልድዩን የሠራው በድንበር ላይ ያለው ህዝብ ነው:: ስለዚህ ስጋት የለኝም:: እንዲያውም በቅርብ ጊዜ ትግራይ የዐቢይንና የኢሳይያስን ቲሸርት አድርጎ እንደሚወጣ ሙሉ እምነቴ ነው::

**ቅጽ1ቁጥር13 ቅዳሜ ሐምሌ7 2010ዓ.ም**
















## አቶ አስራት አብርሃ

ጦርነቱ ከየትም ሊነሳ ይችላል:: በትግራይ ክልላዊ መንግስትና በአማራ ክልላዊ መንግስት መካከል ብዙ ጥሩ ያልሆነ ግንኙነት አለ:: አሁን የሚዲያዎቹን ቅስቀሳ ስታየው ጥሩ ያለ መሆን ነገር አለ:: የተስፋፊነት አጀንዳም አለ:: ከወልቃይት፣ ራያ፣ መተከል ጋር ተያይዞ የሚነሳ ነገር አለ፤ እሱ ከባድ ስለሆነ ለጦርነት መቀስቀስ ምክንያት ሊሆን ይችላል::አሁን ኢህአዴግ ውስጥ ባለው ልዩነት ህወሓት 'የትግራይ ህዝብና እኔ አንድ ስለሆንን እኔን ነካችሁ ማለት የትግራይን ሕዝብ ነካችሁ ማለት ነው' እያለ ነው፤ ይሄን እያለ ባለበት ሁኔታ በዚህ ሰበብ ህወሐት ወደ ጦርነት ስላለመግባቱ ማረጋገጫ የለም፤ ጦርነት ሊያነሣ ይችላል::

**ቅጽ1ቁጥር13 ቅዳሜ ሐምሌ7 2010ዓ.ም**

## ወ/ሮ ፍቅርተ ከበደ

እውነቱን ለመናገር ከስምንት ዓመት እስሩ ይበልጥ ይህ ድጋሚ የታሰረበት የአንድ ዓመት እስር ነው የጎዳን:: ፍትህ አለ ብለን እናምናለን፤ እኛን ግን የሚሰማን አጥተናል:: ከአባቴ የበለጠ ከባድ ክስ ያለባቸውና በተመሳሳይ ነገር የተከሰሱ በሙሉ ተፈትተዋል:: እሱ ግን ተረስቷል:: የሚገርመው እነዚህ ሰዎች እንዲፈቱ፣ በቅርቡ የ700 ሰዎች ስም ዝርዝር ለይቅርታ ቦርድ ሲቀርብ የእሱም ስም ተላልፎ እንደነበር ከማረሚያ ቤት መረጃ አግኝተናል:: ግን እሱን ነጥለው አወጡና ሌሎችን ፈቱ::

**ቅጽ1ቁጥር14 ቅዳሜ ሐምሌ14 2010ዓ.ም**

## ተዋናይ መኮንን ለዐከ

ጥበብና ፖለቲካ አንድ ናቸው:: 'በማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ?' የሚባል ነገር አለ:: ፖለቲካ ላይ ቆመህ አይደል እንዴ ኢኮኖሚውን የምትመራው? አሁን ተሳሳቱ የምንላቸው ሰዎች እኮ ኢኮኖሚው መርቷቸው እኮ ነው ጉድ የሆኑት:: እነዚያ የጥበብ ሰዎች ህዝብ የሚፈልገውን ነገር ትተው መንግሥት የሚፈልገውን ለዘመናት በአደባባይ ለፈለፉ:: በፖለቲካ ውስጥ ያለው ኢኮኖሚ የጥበብ ካባቸውን ገፋፋቸው ማለት ነው::እኔ ግን የኢኮኖሚ ጉዳይ ወይም ጥቅም አይመራኝም ብያለሁ:: እንኳንም ያኔ እነሱን አልተጠጋሁ::

**ቅጽ1ቁጥር15 ቅዳሜ ሐምሌ21 2010ዓ.ም**

## ካፒቴን መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ

የቂሊንጦ እሳት ቃጠሎ የተነሣው በህወሓት ሤራ ነው:: ርካሽ የሆነና የተለመደ አውሬነታቸውን የሚያሳይ፣ ከዚህ በፊት ያደረጉት ነገር መሆኑ ይታወቃል:: 1998 ዓ.ም ላይ ሁላችሁም እንደምታውቁት የአዲስ አበባ ልጆችን በግፍ ጨፍጭፈዋል:: ቃሊቲ ዞን ስድስት ላይ ስታዲየም ሠርተውበታል:: ከዚያ ሥር እህትና ወንድሞቻችን ተቀብረው ይገኛሉ፤ ተጠያቂነት ቢኖር ያ ነገር እውን የሚሆን ይመስለኛል::የሚገርመው እኔ ከዞን ወጥቼ፤ እነ አቶ በቀለ ገርባ ጋር ከነበሩ የፖለቲካ እስረኞች ጋር ወደ ከፍተኛ ጥበቃ የተዛወርሁት ቃጠሎው ከመከሰቱ ከአራት ወራት በፊት ነው::

**ቅጽ1ቁጥር17 ቅዳሜ ነሐሴ5 2010ዓ.ም**

## አቶ ዜና ዳዊት

**(የኔክሰስ ሆቴል ም/ሥራ አስኪያጅ)**

አማራጩ በትብብር መሥራት ነው:: ሆቴል ዘርፍ ብቻ የሚሠራው ጉዳይ ስላልሆነ፤ በቱሪዝም ዘርፍ ያሉ መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ አየር መንገድና ሌሎች አካላት ተቀናጅተው በጋራ መሥራት እስካልቻሉ ድረስ፤ የሆቴሉ ዘርፍ ብቻውን አሁን የተነሡትን ችግሮች ሙሉ ለሙሉ ይቀርፋል ለማለት ያስቸግራል::እነዚህ የጠቀስኳቸው ክፍተቶች ባሉበት ቱሪስት ሲመጣ፣ አዲስ አበባን ብቻ ለማየት አይደለም የሚመጣው:: እንዲያውም አዲስ አበባ ትራንዚት ነች::

**ቅጽ1ቁጥር17 ቅዳሜ ነሐሴ5 2010ዓ.ም**

## ታጋይ አባ ወርቁ

(የአርበኞች ግንባር ም/ሊቀመንበር)

አርማጭሆ በነበርንበት ጊዜ በሰነዘርነው ወታደራዊ ጥቃት ብዛት ያለው የጦር መሣሪያ ማርከናል:: ለምሳሌ እኔ ይዤው እንቀሳቀስ የነበረው ሠራዊት ብዛት መቶ ሃያ ነበር::በምግብ ረገድ መገዛት ያለበትን ነገር ገዝተን ነው የምንጠቀመው፤ ከዚያ ውጭ እርሻ ጣቢያ እንገባለን:: በአርማጭሆ በኩል ብትሄድ የትኛውም እርሻ ጣቢያ፤ ማንኛውም መንገደኛ በልቶ ጠጥቶ የሚሄድበት ነው:: የማሽላ ዱቄት እንደ ልብ ስላለ፤ እዚያ ገብተህ፣ ገንፎህን አዘጋጅተህ በልተህ መሄድ ትችላለህ::

**ቅጽ1ቁጥር16 ቅዳሜ ሐምሌ28 2010ዓ.ም**

## ወ/ሪት ጫልቱ ታከለ

ቃሊቲ ሦስት ዓመት እንደታሰርኩ፣ የማዕከላዊ ደህንነት መጥቶ፣ 'አንቺ ምንም አላጠፋሽም፤ አዲስ በወጣው ሕግ ነው ከዐሥር ዓመት በላይ የተፈረደብሽ፤ እኛ ግን ይሄን ያህል ዓመት እዚህ እንድትቆዪ አንፈልግም፤ ወጥተሽ እንድትማሪ እንፈልጋለን' ሲለኝ፤ 'እሺ' አልኩት:: 'ግን ስትወጪ ይቅርታ ሞልተሽ መውጣት አለብሽ' አለኝ:: 'ሳላጠፋ ይቅርታ አልጠይቅም፤ እናንተ ናችሁ እኔን ይቅርታ መጠየቅ ያለባችሁ፤

**ቅጽ1ቁጥር17 ቅዳሜ ነሐሴ05 2010ዓ.ም**

## ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ

ኢህአዴግ ጋር ስንመጣ የመከላከያ ሠራዊት ግንባታው ይበልጥ አስቂኝ ነው:: ሁላችንም እንደምናስታውሰው በሽምቅ ውጊያ አሸናፊ ሆኖ ነው ወደ ቤተ መንግሥት የገባው:: እንግዲህ ኢህአዴግ በርካታ ታላላቅ ጥፋቶችን ፈፅሟል። ከእነዚህ ውስጥ በዋናነት ሊጠቀስ የሚገባው ኢትዮጵያ ብዙ ወጪ ያፈሰሰችበትን ጦር ሠራዊት:- ጄኔራሎች፣ ኮሎኔሎች፣ ሻለቆች ጀምሮ እስከ ተራ ወታደሮች ድረስ ያሉትን አባላት በጅምላ ወንጅሎና አባርሮ ሲያበቃ፤ ከበረሀ የመጡትን የሽምቅ አዋጊዎችን በአዛዥነት ቦታ ላይ ማስቀመጡ ይመስለኛል:: ሽምቅ ተዋጊ ለመሆን ከቤትህ ወጥተህ ጫካ ገብተህ መሸፈት ብቻውን በቂ ነው::

**ቅጽ1ቁጥር18 ቅዳሜ ነሐሴ12 2010ዓ.ም**

## መምህር ማን ያዘዋል አበበ

ለዚህች ቤተ ክርስቲያንና ሀገር ይጠቅማል ብዬ የማምነው ነቢየ እግዚአብሔር እንደተናገረው፣ 'ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከሕግና ሥርዓቴ ወጥታችኋል፤ ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ' ነው ያለው:: ይሄንን ማክበር የተሻለ ይመስለኛል:: በሕገ ቤተ ክርስቲያን፣ በቀኖና መሠረት ብቻ መመራት:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው፣ ዘመኑን የሚዋጅ ሕግና ሥርአት አዘጋጅቶ፣ አሁን ቤተ ክርስቲያኒቱ ያለችበትን ሁኔታ የሚመዝን፤ ጥንካሬዋን፣ ድክመቷን መልካም አጋጣሚዎቿንና ሥጋቶቿን ለይቶ ጥናት በማድረግ የረዥም ጊዜ ዕቅድ መንደፍ ያስፈልጋል:: አንዱ ዛሬ ሲሾም የሚሠራበት፤ እሱ ሲሄድ የሚመጣው ሌላ ሐሳብ የሚያመጣበት ሳይሆን፣ እንደ ዱላ ቅብብሎሽ አንዱ የጀመረውን አንዱ የሚጨርስበት ግልፅ የሆነ ተጠያቂነት ያለበት አሠራር ያስፈልጋል:: ያጠፋ የሚቀጣበትና የሚታረምበት፤ የሠራ የሚሾምበትና የሚሸለምበት ግልፅ የሆነ ሥርአት፤ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ሊመራ የሚገባው ሲኖዶስ፤ ክብሩን ቅድሚያውን ለመንፈስ ቅዱስና ለመንፈስ ቅዱስ ብቻ በመስጠት፣ የቤተ ክርስቲያን ቅን መሪዎችን የሚሾም የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ የጠራቸው አባቶችም ለጠራቸውና አዳኝ መድኃኒት ለሆነው ብቻና ለመንጋው ቅድሚያ በመስጠት የሚሠሩ መሆን አለባቸው::

**ቅጽ1ቁጥር18 ቅዳሜ ነሐሴ12 2010ዓ.ም**

## ደራሲ ሰአዳ መሐመድ

በኢትዮጵያ ሬድዮ በ'ቅዳሜ ከሰዓት' እና በእሁድ ጠዋት ፕሮግራም ላይ፣ 'ያበቃ ሕልም'፣ 'የባቡ እግሮች'፣ 'ሦስቱ መስኮቶች'፣ 'ጥልፍልፎሽ'፣ 'ያልተደፈነ ጉድጓድ' የተሰኙ፤ እንዲሁም በፋና ሬድዮ ደግሞ 'የወንዝ ድንጋይ' የተሰኘ ተከታታይ የሬድዮ ድራማዎች ጽፌ ተላልፎልኛል::በሬድዮ ድራማ ጸሐፊነት በቆየሁባቸው ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት፣ በፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር ከሌሎች ጸሐፍት ጋራ በመሆን፣ በባለ 226 ክፍል 'ስብራት' በባለ 130 ክፍል 'የረገፉ ፈትሎች' በባለ 190 ክፍል 'የብርሃን አጽናፋት' በባለ 180 ክፍል 'ምዕራፍ' የተሰኙ የሬድዮ ድራማዎች ላይ በጸሐፊነት ተሳትፌያለሁ::

**ቅጽ1ቁጥር19 ቅዳሜ ነሐሴ19 2010ዓ.ም**
















## አቶ ቸኮል ጌታሁን

የብሔር ፖለቲካ የእነ መለስ መንገድ ነው፤ እሱ ሄዶ ሄዶ ዛሬ ላይ ደርሰናል:: አሁን ላይ በዚህ ጉዳይ ያለውን ነገር እንገነዘባለን:: የእኛ ዓላማ የዜግነት ፖለቲካ ማራመድ ነው፤ ይሄ በሚሆንበት ጊዜ የብሔር ተኮር ፖለቲካ በአንድ ጊዜ የሚጠፋ አይደለም:: የብሔር ፖለቲካ ላለፉት 27 ዓመታት ተኮትኩቶ፣ አድጎ አሁን ጎልብቶ ሊበላን የደረሰበትን ነገር እያየን ነው::በመሆኑም ይሄንን የሁለቱን ልዩነት የሚፈታ መፍትሄ ለመፈለግ እንጥራለን::

**ቅጽ1ቁጥር20 ቅዳሜ ነሐሴ26 2010ዓ.ም**

## አቶ ተስፋዬ አዳል (የመፅሐፍ ሻጭ)

ክላክስ አድርገው ሁለት ሳንዱች፣ ሁለት ቡና በወተት ተራ በተራ እንዲመጣልኝ አዘዙ:: እኔ ወተትና እንቁላል ሳንዱቼን ስበላ መጽሐፉን ማየት ጀመሩ፤ ከዚያ መሃል ላይ፣ 'ይድነቃቸው ተሰማ' የሚለውን ማኀተማቸውን አገኟት:: 'ስንት ገዛሽው?' አሉኝ፤ እኔም ለማትረፍ ብዬ 25 የገዛሁትን 50 ብር አልሁ /ሳቅ/:: 'አይተኸዋል ይህን ማህተም?' አሉኝ፤ 'ጋሼ፣ እኔ አላወቅሁም' አልሁ:: 'ይገርምሃል እኮ! የቤት አይጥ ነው አውጥቶ የሸጠብኝ ይህን መጥሐፍ' ብለው፣ መቶ ብር አውጥተው ሰጥተው፤ 'ደንበኝነታችን ይቀጥላል' ብለው ሸኙኝ:: ታመው እስኪያልፉ ድረስም ደንበኛዬ ነበሩ::

**ቅጽ1ቁጥር20 ቅዳሜ ነሐሴ26 2010ዓ.ም**

## ሜሮን አለማየሁ

"ፕ/ር ብርሃኑ ለትጥቅ ትግል በረሃ ወረደ" የሚለውን ዜና መጀመሪያ የሰማሁት እዚህ እያለሁ ነበርና ያኔ በጣም ነበር ያደነቅኩት:: ምን ያህል የዓላማ ፅናት ቢኖረው ነው ይሄ ሰው፣ ከዛ የሰለጠነ ዓለም ሕይወት ወጥቶ በርሃ የገባው ብዬ አስባለሁ፤ ግንቦት ሰባትን ለመመስረት የወጣውን ውጣ ውረድ፣ ከዛ በፊት የደረሰበትን ችግር፤ አሜሪካ ውስጥ ሆኖ ለዚህ ትግል ሲል ምንም የተመቻቸ ሕይወት መኖር አቅቶት ለሀገሩ የከፈለውን መስዋዕትነት ስታይ፣ እኛ ወጣቶቹስ ለሀገራችን ምንድን ነው ማበርከት ያለብን? ብለን እንድናስብ ያደርገናል::በርሃ ሄጄ ላቡ እንደውሃ እየፈሰሰ ያለመታከት በየቀኑ ተስፋ ባለመቁረጥ የሚሰራውን ሥራ ሳይ እሱንም ሆነ ሌሎች ያገኘኋቸውን አመራሮች በጣም አክብሬያቸዋለሁ::

**ቅጽ1ቁጥር21 ቅዳሜ መስከረም2011ዓ.ም**

## ኦባንግ ሜቶ

እንዳልከው ጋምቤላ ውስጥ ወደ አምስት ብሔሮች ናቸው የሚኖሩት ግን በግልጽ ጥቃቱ የተፈፀመው አኝዋኮች ላይ ነው፤ ቤቱ የተቃጠለበት፤ አካሉ የጎደለበት አለ:: በጊዜው ዓለም በገሃድ እንዲረዳው ያደረግነው በአኝዋኮች ላይ ጄኖሳይድ (የዘር ማጥፋት ወንጀል) ነው የተፈፀመው:: በወቅቱ ከእኛ ጋር በጋምቤላ ልማት ዙሪያ የሚሰሩ ሰዎች ሞተዋል፤ ዘመዶቻችን ሞተዋል:: ከዛ በኋላ ያለውን እንቅስቃሴና በኢትዮጵያ በህወሐት መንግሥት የሚፈፀመውን የዘር ማጥፋት ተግባር ለተቀረው ዓለም ማስተዋወቅ የጀመርኩት በዛ መንገድ ነው፤

**ቅጽ1ቁጥር23 ቅዳሜ መስከረም 12 2011ዓ.ም**

## አምባሳደር ካሳ ከበደ

ከሀገር ከወጣሁም ሆነ እሳቸው ከሀገር ከወጡ በኋላ ከፕሬዝዳንት መንግሥቱ ጋር አልተገናኘሁም:: በስልክ አልፎ አልፎ እንገናኛለን፤ እንጠያየቃለን:: ስለ ሀገራችን ጉዳይ እንነጋገራለን:: አለቃዬ ነበሩ አሁንም አክብሬ ነው የማናግራቸው:: ብዙ ጓደኞቻችን አንተ ብለዋቸዋል፤ እኔ ግን እስከ ዛሬ በአንቱታዬ ቀጥያለሁ:: ሲጀመር አንተ ነበር የምንላቸው፣ ከሶማሌያ ጦርነት ድል በኋላ አንተ ይሏቸው የነበሩ የወታደር ኮርስ ሜቶቻቸው፣ በውትድርናው ዓለም በማዕረግ ቀደምት የነበሩት ሁሉ አንቱ ሲሏቸው እኛ ሲቪሎቹስ ምን አገባን ‹‹አንቱ›› ማለት አለብን ወደሚለው ሄድን፤ እሳቸውም ተቀበሉት:: እሳቸው አንተ ይሉኛል፤ እኔ አንቱ እላለሁ፤ በዛ መልክ ነበር እስከመጨረሻው ለሀገር ያገለገልነው አሁንም በበፊቱ ቀጥያለሁ::ስንገናኝ በስልክ የምንነጋገረው ስለ ኢትዮጵያ ነው፤ ሌላ በግል ጉዳያችን ዙሪያ በጋራ የሚያነጋግር አርዕስትም የለንም:: ለኢትዮጵያ በጎ ነገር ይመኛሉ፣ይፈልጋሉ ምናልባት አለቃዬ ቢሆኑም መንግሥቱን ሊያስወቅሰኝ የሚችል ነገር ቢኖር፤ አጠፋን ማለት አይወዱም::

**:ቅጽ1ቁጥር24 ቅዳሜ መስከረም19 2011ዓ.ም**

## አፈ መምህር አባ ገብረሥላሴ ጌትነት

ለሀያ ሰባት ዓመት ከሰው ርቀው ከንግግርም ርቀው ነው የቆዩት:: እንዲህ ባለ አርምሞ የቆየ ሰው ደግሞ በአንዴ ወደ ዓለም ተቀላቅሎ በተፈለገው ልክ፣ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ፤ ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ጊዜ ይፈጃል:: ከዚህ አንፃር የብፁዕነታቸው ይሁንታ እየተጠበቀ ነው::ከዛ ውጭ ቤተክርስቲያኒቷ እሳቸው መግለጫ፣ ቡራኬም መስጠት የለባቸውም፣ ልክ እንደ ፓትርያክ መታየት የለባቸውም የሚል ገደብም ፍላጎትም የላትም::

**1ቁጥር25 ቅዳሜ መስከረም 262011ዓ.ም**

## አቶ ዓለምአየሁ ኃይሌ (የታሪክ ፀሐፊ)

በዚህም በኦሮምኛ "ዌዱ" ይባላል፤ ዌዱ የሚለው በግዕዝ 'ውዳሴ' ማወደስ፣ ማመስገን ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው:: ዌዱ ተብሎ 'እሬቻ' ይከበራል:: በእሬቻ በዓል ላይ የኦሮሞ ምስጋናዎች ሦስት ነገሮች ላይ ያጠነጥናል፤ ይህም ሰላም፣ ዝናብ እና ትውልድ (ዘር) ላይ ነው:: የኹሉ መልከዓ ፈጣሪ የሆንከው እነዚህን ስለሰጠኸን እናመሰግናለን፤ አሁንም ሰላም፣ዝናብ ፣ትውልድ(ዘር) ትሰጠን ዘንድ እንለምናለን ይላሉ በጋራ::

1ቁጥር25 ቅዳሜ መስከረም 262011ዓ.ም

## ይልቃል ጌትነት (ኢ/ር)

ይሄ የልጆች ጨዋታ ነው:: ምንም ለጥያቄና ለድርድር የሚቀርብ አይደለም:: አዲስ አበባ በታሪኳ ከተመሰረተች ጀምራ የኢትዮጵያ መናገሻ ዋና ከተማ ሆኖ ነው የኖረችው:: በሕግም ሆነ በዓለም አቀፍ የምትታወቀው አዲስ አበባ ሆና ነው እንጂ በታሪክም ቢሆን ፊንፊኔ የሚባል ስም የላትም:: በሀገሪቱ ሕግም መሠረት ፊንፊኔ የሚባል ከተማ የለም:: አሁን ባለው ሕገ-መንግስት:: ስለዚህ ጎጠኞች ነን ብለው ደጋፊዎቻቸውን ለማስደሰት እንደዚህ ዓይነቱን ነገር ቢያነሱም፣ አሁን ባለውም ሆነ ከዚህ በፊት በነበረው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ፤ ኦሮሚያ የሚባል ሀገር፣ ፊንፊኔ የሚባል ከተማ የለም::

**ቅጽ1ቁጥር26 ቅዳሜ ጥቅምት03 2011ዓ.ም**

## ዶ/ር መረራ ጉዲና

አዲስ አበባ መብራት የምታገኘው ከሞላ ጎደል ከኦሮሚያ ነው፤ አዲስ አበባ ምግብ የምታገኘው ከኦሮሚያ ነው:: አዲስ አበባ ከሞላ ጎደል ውሃ የምታገኘው ከኦሮሚያ ነው:: ኦሮሚያም ብትሆን መሠረታዊ የሚባሉ በተለይም ዘመናዊ ሸቀጦችን የምታገኘው ከአዲስ አበባ ነው:: ስለዚህ የሁለቱ ሕዝቦች የጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ድርድር የማይደረግበት ምክንያት አይታየኝም::ለምሳሌ ከአዲስ አበባ ከሚገኘው ቀረጥ በተወሰነ ደረጃ ለኦሮሚያ ውሃ ልማት ለኢነርጂ ለምግብ ፕሮዳክሽን ሊውል ይቻላል:: የማንም ኪስ አይገባም ማለት ነው:: የአዲስ አበባ ሕዝብም ይህንን በማድረጉ ሊጠቀም ይቻላል::

**ቅጽ1ቁጥር26 ቅዳሜ ጥቅምት03 2011ዓ.ም**

## ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ

የአርበኞች ግንቦት ሰባት አማራን ይጠላል ወይም አማራ ጠል ነው የሚለው ክስ በተለያየ ቦታ ተነስቶ በቂ መልስ ተሰጥቶበታል:: ምንም ቅንጣት ታህል መሠረት የሌለው ተራ አመለካከት እንደሆነ ግልጽ ነው:: በተለያዩ ምክንያቶች ይሄንን ማረጋገጥ ትችላለህ:: አንደኛው ኢትዮጵያዊነት ወይም በዜግነት ላይ ያተኮረ የሚለው የድርጅቱ ፖለቲካ ባሕሪይ በአጠቃላይ የትኛውንም ብሔር ሳይለይ ይሄኛው ያኛው ሳይል የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው::ይሄ ኢትዮጵያዊነት የሚለው ከብሔር ፖለቲካ ወጣ ብሎ በሀገር ደረጃ የሚደረግ እንቅስቃሴ ማእከል ያደረገበት የአማራው ወገናችን ስለሆነ በድርጅታችን ውስጥ አብዛኛው አባል ከዚህ ክልል የመጣ ነው:: አብዛኛው የድርጅቱ አባል እና አመራር የአማራ ተወላጅ የሆነበት አርበኞች ግንቦት ሰባት ድርጅት እንዴት አማራ ጠል እንደሚሆን ለሰሚው ራሱ ግራ የሚገባ ነገር ነው::

**ቅጽ1ቁጥር27 ቅዳሜ ጥቅምት 102011ዓ.ም:**

## ግፋቸው ገ/ስላሴ

(25 ዓመት በግፍ የታሰረ)

ምን እንደሆነ አናውቅም:: ደህና ሰላም የሆነ ቁጭ ብሎ ሲያወራህ የነበረ ሰው ፣ድንገት ሆዴን ቆረጠኝ ይልና ወዲያው ሕይወቱ ያልፋል:: ለምሳሌ አንድ ታደሰ ኪዳን የሚባል ጓደኛችን የሆነውን ልንገርህ፤ በነገራችን ላይ እዛ አስር ቤት ውስጥ ሁለት ሁለት እስረኛ እየተደረገ እጅህ ተገጣጥሞ በሰንሰለት ታስሮ ነው ውለህ የምታድረው:: እኔ ራሴ ለተጎዳው እግሬ በአንድ እጀ ምርኩዝ ይዤ በአንድ እጄ ከሌላ እስረኛ ጋር ታስሬ ነው የማድረው የምውለው::ሰውነታችንን በወር ወይም በሁለት ወር ስንታጠብ ልብሴን ከላዬ ላይ አውልቄ በታሰርንበት ሰንሰለት ላይ አድርጌ ስሰጠው አብሮኝ የታሰረው ይይዝልኛል፣ ከዛ ስጨርስ ያንን ለብሼ እንደገና እሱ አውልቆ ይሰጠኝና በታሰርንበት ሁኔታ ሆነን ታጥቦ ይጨርሳል:: ይህን ያህል የከፋ ግፍ ነበር በገዛ ሀገራችን የሚፈፀምብን:

**:ቅጽ1ቁጥር28 ቅዳሜ ጥቅምት17 2011ዓ.ም**
















## ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጥ

የአ.አ ን/ም/ቤት ፕሬዝዳንት

የሴቶች ወደ አመራርነት መምጣት ጥሩ ነው፡፤ እኔ በሰራሁባቸው ቦታዎች በአመራርነትም ጭምር ከብዙ ወንዶች መካከል ሆኜ ነው:: ወንዶቹም እንደ ሴት አያዩኝ ነበር:: ዛሬ ብዙ ነገር እየተቀየረ ነው:: ብዙ ሴቶች የአመራርነት ሚናን እየተወጡ ነው:: እኛ ሀገር በተለይ የሴቶች ጥቅም በሚገባ አልታወቀም፤ በተፈጥሮም ቢሆን ሴቶች ከወንዶች የሚለዩበት ነገር አለ:: ሴት ኃላፊነት ሊሰጣት የሚገባ አካል ናት፤ ከቤተሰብ ጀምሮ ያለባትን ኃላፊነት ማየት ይቻላል::

**ቅጽ1ቁጥር29 ቅዳሜ ጥቅምት 242011ዓ.ም**

## ዶ/ር ሰይድ ኑሩ

የውጭ ብድር እና ዕዳን በተመለከተ ሊያስበረግገን የሚገባው መመለስ ችለናል አልቻልንም የሚለው ጉዳይ አይደለም:: ብድሩን አበዳሪዎቻችን ሊሰርዙልን ይችላሉ ወይም በሌላ መንገድ ልንመልሰው እንችላለን:: ለኢትዮጵያ ብድር የማግኘትና ያለማግኘት ጉዳይ ችግር ሊሆን አይችልም:: ትልቁ ጥያቄ መሆን ያለበት መክፈል ያልቻልነው ለምንድን ነው? መክፈሉ በራሱ ግብ አይደለም:: የተበደርነው በራስ ለመቆምና መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት ነው:: ለወጣቱ የሥራ ዕድል መፍጠር፤ ኢኮኖሚውን ማሳደግ፤ አጠቃላይ ሀገራዊ አቅም መገንባት፤ በየጊዜው የማይበደር ዓይነት ኢኮኖሚ ለመፍጠር መሞከር፤ የውጪ ምንዛሪ የሚያፈራ ኢኮኖሚ መፍጠር ነው፣ የብድሩ ዋና ዓላማ::

**ቅጽ1ቁጥር30 ቅዳሜ ኅዳር1 2011ዓ.ም**

## ጋዜጠኛ መታሰቢያ ሞገስ ቀጸላ

ይሄንን የብሔር ተኮር ፖለቲካ እንቅስቃሴ ያመጣው ሕወሓት ነው:: ሕወሓት ሲመጣ በብሔር ተደራጅቶ ስለገባና ሌላው በኢትዮጵያዊነት ተደራጅቶ ስለጠበቀው ሁኔታው ከእሱ ጋር ማች ስላላደረገለት፣ ሌላውን ኅብረተሰብ ከፋፍሎ ትናንሽ ማድረግ ስለነበረበት ያንን ፈፅመ:: በዛ ሲስተም ሃያ ሰባት ዓመት ሥልጣን ላይ ቆየ:: አሁን ነገር ሲቀያየር ከተወሰኑት በስተቀር ሁሉም የራሱን ብሔር ማዳን ፈለገ:: ልንጠፋ ነው መደራጀት አለብን እንደሚሉት ሁሉ፣ ያልተደራጁ ብሔች አሉ፤ ተበድለናል የሚሉ ብሔሮችም አሉ::

**ቅጽ1ቁጥር31 ቅዳሜ ኅዳር 8 /2011ዓ.ም**

## አቶ ግርማ ሰይፉ

ይቅርታ ሁለት መንገድ አለው:: አንደኛ ጥፋተኛ ነኝ ብለህ ታምንና ከዛ በኋላ እጁ ያለውን ንብረት መልሰህ ይቅርታ ጠይቀህ በአሠራር ብልሹነት ያበላሸኸውን ግልፅ አድርገህ ልትታለፍ ትችላለህ:: ግን ሰርቀህ ባገኘኸው ገንዘብ ሀገር ለማመስ ያዙኝ ልቀቁኝ ስትል ያጠፋኸውን ጥፋት እንደ ጀግንነት ስትቆጥረው ይሄ አካሄድ ተገቢ አይሆንም:: ስለዚህ ለመቀጣጫ የሚሆኑ ነገሮችን ማሳየት ያስፈልጋል::በሰብኣዊ መብት ጥሰት ላይ የተሠማሩ ሰዎች በሰብኣዊ መብት ጥሰት መሳተፋቸው ሳያንሳቸው አሁንም ልክ ነበርን ብለው እንደ ጀብዱ ሊያወሩት ከፈለጉ፣ መቀጣት አለባቸው::

**ቅጽ1ቁጥር31 ቅዳሜ ኅዳር 8 /2011ዓ.ም**

## አቶ ገብሩ አሥራት

አንዱ ሌላውን የመቆጣጠርና ግልጽነት የሰፈነበት ሥርዓት እስካልገነባን ድረስ ሌብነት ሊቀጥል ይችላል:: በኢትዮጵያ ሌብነት ፣ዘረፋ ሊስፋፋ የቻለበት ሌላው ጉዳይ ገዢው መንግሥት ሀብት ተቆጣጥሯል፤ መሬትና የመንግሥት በጀት በእጁ ነው፤ የመንግሥት ተቋማትንም አስተዳድራለሁ ብሎ ተቆጣጥሯል ስለዚህ ሥርዓቱ ለሌብነት የተጋለጠና የተመቻቸ ሁኔታ ፈጥሯል::ይሄ ጥፋት የአንድ ቡድን የሜቴክ ወይም የደህንነቱ አካል ብቻ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ አለኝ::

ቅዳሜ

**ቅጽ1ቁጥር32 ኅዳር15 2011ዓ.ም**

## ፕሮፌሰር መድኃኔ ታደሰ

አሁን በሁሉም አካባቢዎች ማለት ይቻላል፤ የብሔርተኛነት ስሜት አይሏል::የቄሮም፣ የኦሮሞ አክቲቪስቶች፣ የኦነግና የኦፌኮን ስሜት ብትወስድ ኦሮሚያ ውስጥ የብሔርተኝነቱ ስሜት ከፍ ያለ ነው:: አማራም ከላይ በጠቀስነው መንገድ ወደ ፅንፍ ብሔርተኝነት ስለተሳበ ብአዴን (አዴፓ) ከአ.ብን. ሽርክና ካልፈጠረ በስተቀር ብርቱ ፉክክር ይገጥመዋል:: ኦብነግም ከፍተኛ ኃይል ነው፤ የሶማሌ ክልልን ፕሬዚዳንት ስለቀየርክ ኦጋዴንን ልታሸንፍ አትችልም:: በሶማሌ ፖለቲካ የኦጋዴን ጎሳን ወይም ሪር አብዲሌን ካልያዝክ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ልታሸንፍ ስለማትችል ኦብነግ ዕድል አለው ማለት ነው::

**ቅጽ1ቁጥር33 ቅዳሜ ኅዳር 22 /2011ዓ.ም**

## አቶ ጋአስ አሕመድ
### (የአፋር ሰብኣዊ መብት ድርጅት ሊቀመንበር)

ሱልጣን አሊሚራህ በወቅቱ ስለ አፋር ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት ሲናገሩ “እንኳን እኛ ግመሎቻችን የኢትዮጵያን ባንዲራ ያውቁታል” ማለታቸው ወያኔን እልህ ውስጥ አስገብቶት ነበር::በጊዜው አፋሮች በመሆናቸው ብቻ ወጣቶች ተሰባስበው እንዲረሸኑ ተደርጓል:: ሬሳቸው ራሱ ተሰብስቦ በጅምላ ነበር የተቀበረው፤ ከሀገር ከመወጣቴ በፊት በ1991 ዓ.ም በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት፣ በቦታው የነበሩት ወታደሮች ካምፑን ለቀው ለአፋር ክልል የገዋኔ ፖሊሶች አስረክበው ሲሄዱ የተጠረጠሩ ቦታዎች ሲቆፈሩ የእነዛ በግፍ ተገድለው በጅምላ የተቀበሩ ሰዎች ሬሳ ተገኝቷል:: የ13 ሰዎች ሬሳ ከአንድ ጉድጓድ ያወጣንበት ሂደት ነበር::

**ቅጽ1ቁጥር34 ቅዳሜ ኅዳር29 2011ዓ.ም**

## ዶክተር አረጋዊ በርሄ (የሕወሓት መሥራች)

ድሮ ገና ለትግል ስንነሳና ድርጅቱን ስንመሰርት በዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን የትግራይ ሕዝብን መብት ማክበር ብለን ነው::በኋላ የመጡ የሕወሓት አባላቶች ግን እስከ መገንጠል የሚል ጥያቄ አንስተው ዓላማውን በጠበጡት::ትንሽ ቆይተው ደግሞ ማሌሊት የሚባል የአፋኝ ቡድን ፈጥረው ትግሉን አኮላሹት::ስለዚህ ይሄ አሁን ያለው ሕወሓት የሚባለው ድርጅት የትግራይ ሕዝብ በማይፈልገው አቅጣጫ ነው እየተጓዘ ያለው:: ስለዚህ ድርጅትና ሕዝብ አንድ ሊሆን አይችልም::

**ቅጽ1ቁጥር35 ቅዳሜ ታህሳስ 6 /2011ዓ.ም**

## አቶ አምዶም ገ/ስላሴ (የአረና አባል)

በወቅቱ ጀምሬው የነበረው የትግራይ ሕዝብና ሕወሓት አንድ እንዳልሆኑ ልዩነት እንዳላቸው መግለፅና ማስረዳት ነበር:: እነዚህ ለዓመታት ሥልጣን ላይ የቆዩ ሰዎች ዘርፈው ሀብትና ንብረት ሲያፈሩ፣ የትግራይ ሕዝብ ግን በድህነት እየተንገላታ በሀገር ውስጥም በውጭም ለስደትና ለርሃብ ተጋልጦ በሚገኝበት፣ በትውልድ ቦታው ትግራይ ውስጥ እንኳን ሠርቶ መብላት ያልቻለ ብዙ ሕዝብ እያለ፣ ሹማምንቱ ግን “ሕወሓትና የትግራይ ሕዝብ አንድ ናቸው” በማለት ሲናገሩ ይደመጣል:: ይሄ ፈፅሞ ስህተት ነው::

**ቅጽ1ቁጥር36 ቅዳሜ ታህሳስ 13 2011ዓ.ም**

## መምህርና አክቲቪስት ስዩም ተሾመ

ኦነግ እንደ ድርጅት ብቻውን የቆመ አይደለም፣ ተከፋፍሏል:: የተለያዩ ቦታዎች ተሰነጣጥቆ ሁሉም “ኦነግ ነኝ” እያለ ነው:: እንግዲህ ከእነዛ ውስጥ አንዱን ወገን ነው ለይተን እያየን ያለነው፤ በአቶ ዳውድ ኢብሳ የሚመራውን ቡድን:: ምናልባት ካስታወስክ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ኤርትራ ከሀያ ዓመት በኋላ ሄደው ለሰላም ስምምነት ንግግር ሲያደርጉ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ይህን የአቶ ዳውድ ኢብሳን ቡድን አነጋግረው እንደነበር ሰምተናል:: ከዛ በኋላ ደግሞ ሊያገኟቸው ሙከራ ሲያደርጉ እንዳልተገኙ፣ የሰላም ስምምነቱ ላይም ለመሳተፍ ፍቃደኛ እንዳልነበሩ ተገልፆ ነበር፣ በተለይም ማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ::

**ቅጽ 1 ቁጥር 37 ቅዳሜ ታህሳስ 20 / 2011 ዓ.ም**

## ኦልባና ሌሊሳ

በየቦታው የምታየውን ግጭት የተደራጁ አካሎች ተዘጋጅተው የሚፈጥሩት፣ ሕግ እናስከብራለን የሚሉ አካላቶች፣ በሕዝብ ተመርጠው የሀገርና የሕዝብ መሪ ተብሎ የሚታወቅ አካል በሚያስማራው ኃይል ነው ግጭቶች እየተፈጠሩ ያሉት:: ለምሳሌ በሱማሌ ክልልና በኦሮሚያ የተፈጠረውን ግጭት ካየኸው፣ የተደራጁ አካላት ናቸው የቀሰቀሱት:: በምዕራቡም በኩል ከተመለከትን የሰለጠኑ የፖሊስ ሥነምግባር ያላቸው፣ የፖሊስ ዩኒፎርም በለበሱ አካላትና በሕዝብ መሐከል ነው እየተደረገ ያለው::

**ቅጽ 1 ቁጥር 37 ቅዳሜ ታህሳስ 20 / 2011 ዓ.ም**











## ዶ/ር ጫኔ ከበደ (የኢዴፓ ሊ/መንበር)

ፈርሷል የሚለው ግለሰብ ፓርቲውን ከመጀመሪያው የግል ንብረቱ አድርጎ ይዞት ይጓዝ ስለነበረ ነው::ኢዴፓ የግለሰብ ንብረት የመሆኑ ጉዳይ አክትሟል:: በእኛ በኩል ግን ፓርቲው አልፈረሰም፤ ሁለተኛ በውስጥ በነበረው ክፍፍልም ቢሆን በፍርድ ቤት መብታችንን አስከብረን፣ በፍርድ ውሳኔ መሰረት የፓርቲያችን ህጋዊነት በቀጥታ ተረጋግጦልናል::

ቅጽ1ቁጥር38 ቅዳሜ ታህሳስ 27 2011ዓ.ም

## ሬ/ፕ/ር አበባው አያሌው

ይሄ ትውልድ ኢኮኖሚውን ብቻ ነው የሚመለከተው፣ የኋላ ታሪክ፣ ማንነቱን ፈፅሞ አያይም:: ሁለተኛ ደግሞ የተሰራበት ስራ ነው:: ባለፉት ሀያ ሰባት ዓመታት ኢትዮጵያዊነቱን እንዲያውቅ ሳይሆን የተደረገው፣ የብሔር ማንነቱን እንዲያውቅ ብቻ ነው በጥልቀት የተሰራበት:: የኦሮሞ ወጣት ኦሮሞነቱን ብቻ እንዲያስብ፤ ያ ወጣት አስቀድሞ ያንን ነገር ከወሰደና ከተቀበለ፣ ለእሱ ኢትዮጵያዊነት ምን ትርጉም ይሰጠዋል? የአማራው ወጣት አማራነቱ፣ የትግሬውም ወጣት ትግሬነቱን ብቻ እንዲያተኩር ካደረግክ ኢትዮጵያን በምን ሊያውቃት ይችላል?

**ቅጽ1ቁጥር40 ቅዳሜ ጥር 11 2011ዓ.ም**

## አቶ ሌንጮ ለታ

ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ውጪ እንገናኝ ነበር፤ እኛ ሀገር ቤት ተመልሰን ለመታገል እንደምንፈልግና ይሄንን እንዲያሳኩልን ጠይቀናቸው ነበር:: እስከ ጠ/ሚኒስትሩ ድረስ ነው በዚህ ላይ ውይይት ያካሄድነው:: በመጨረሻ ላይ አቶ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ “ኢትዮጵያ ብትመጣ ለአንተ ምንም ችግር አይኖርም፣ የሴኩሪቲ ሁኔታ አያሳስብህ፤ እንደውም ጥበቃ በማድረግ ዋስትና እንሰጥሃለን” አለኝ:: አስቀድመን ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ያደረግነው ውይይት ምንም አይነት ውጤት ሊያመጣ ስላልቻለ እዛው ሄደን እንወያይ በሚል ወደ እዚህ መጣን:: አዲስ አበባ በገባን በሁለተኛው ቀን ልጆች ልከው ተመልሰን በሌላ ጊዜ እንድንመጣ ነገሩን:: በዛ መሰረት በሶስተኛው ቀን ወደ መጣንበት ተመለስን::

**ቅጽ1ቁጥር40 ቅዳሜ ጥር 11 2011ዓ.ም**

## አቶ ነአምን ዘለቀ

ትልቁ የወያኔ ክህደት ይሄ ነው:: በወቅቱ ከሻዕቢያ ጋር ተደራድሮ ለኢትዮጵያ በሚጠቅም መልኩ፣ የአሰብን ወደብ ኢትዮጵያ ባለቤትም፣ ተጠቃሚም እንድትሆን ማድረግ ይቻል ነበር:: ይሄን እነ ኸርማን ኮህንም ገልፀውታል:: ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የቆመ መንግስት ቢኖር ኖሮ፤ ቢያንስ አሰብን ተደራድሮ ኢትዮጵያ በባለቤትነት እንድትይዘው ማድረግ ይቻል ነበር::የባህር በርም ሆነ ባህር ኃይል ለአንድ ሀገር ወሳኝ ነው:: አሜሪካንን አሜሪካ ያደረጋት የባህር በሯ ነው:: የባህር ኃይሏ ዝም ብሎ ነገር ሳይሆን፤ ለዓለም ዓቀፍ ንግድም፣ የኢኮኖሚ ልማትም ሆነ ሌሎች ነገሮችን በሙሉ የሚቆጣጠሩት እነኚህ ባህር ኃይሎች ናቸው:: ዘጠና በመቶ የዓለም ንግድ የሚካሄደው በባህር ላይ ነው:: በዚህ ላይ አንድ ጥናት እያደረግሁ ነው፤ በቅርቡ በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅቼ አሳትምዋለው::

**ቅጽ1ቁጥር41 ቅዳሜ ጥር 18 /2011ዓ.ም**

## ፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ

እኔ እንደመረመርኩት በታሪክ ይሄ ነገር አማራው ላይ አልተገኘበትም:: አንድም ነገር:: እንደውም የኢትዮጵያዊያን ዳር ድንበር በማስከበር፣ ነፃነቱን በማስከበር፣ ሀይማኖቱን በማስጠበቅና ከውጭ ወራሪ በመከላከል፣ ከዚህም በላይ ደግሞ በሥነ-ፅሁፍ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስዕሎችን፣ ኪነ ጥበቦችን በማራመድ፣ ታሪካችንን በመጠበቅ፣ እፅዋትን መድኃኒት አድርጎ በማግኘትና በመጠቀም፣ መፃፍና ማንበብን በመጠበቅ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብዙ ነገር ነው ያደረገው አማራ ነው::አሁን ወደ ተነሳንበት ዋና ነጥብ ስንመለስ ከጎሳና የዘረኝነት ስሜት መውጣት አለብን::

**ቅጽ1ቁጥር41 ቅዳሜ ጥር 18 /2011ዓ.ም**

# ኢ/ር ግደይ ዘርአጽዮን

ክፍፍሉ ሙሉ በሙሉ የስልጣን ጥያቄ ነው:: ሲመጣ የነበረው የስልጣን ክፍፍል ነው ነገሮችን የፈጠረው:: በስልጣን ሽኩቻው ላይ የመለስ እና የስዬ ፉክክር መሀል እንደሚወድቅ እሱ የጠበኩት ነገር ነበር:: ሁለቱም በራሳቸው መንገድ ሴራ ሲያጠነጥኑ ስለቆዩ ግጭቱ ዞሮ የሄደው ሁለቱ ላይ ነው::መለስ የጦር ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የነበረን ሰው ከዛ ቦታ አውርዶ ወደ ትግራይ ሲልከው በሁለቱ መሀል ምን እንደሚፈጠር ግልፅ ነው:: ሌላው ሙስና በጣም የታየበትና ያደገበት ሁኔታ ስለነበር ከዛ በፊት ገና ሲገቡ ጀምሮ ብዙ ቀና ታጋዮች ይሄንን የሙስና የተዘፈቀ አሰራርና አካሄድ በማየት ተቃውሟቸውን በግልፅ በማሰማታቸው እስከ ሰላሳ አራት ሺህ ታጋዮች ድረስ ለመታሰር በቅተዋል:: የተባረሩም አሉ::

**ቅጽ1ቁጥር42 ቅዳሜ ጥር 25 2011ዓ.ም**

# ፕ/ር ፍስሃጽዮን መንግሥቱ

“ፍስሃጽዮን የራሱን ድርጅት አቋቋመ” ብለው ከሰሱኝ:: እኔ በእግዚአብሔር ፊት ነው የምናገረው፤ ሌላ ድርጅት የማቋቋም ምንም ሀሳብ አልነበረኝም፤ አልሞከርኩም:: እኛ ያሰብነው ለማጠናከር ነው:: ኮ/ል ጎሹም ደካማ ጎን ካለው እሱን ለመሸፈንና ጠንካራ ፓርቲ ለማቋቋም፣ ከዘር ፖለቲካ የፀዳ ሀገራዊ ድርጅት ለመመስረት ነበር ጥረታችን:: ሌላ ፓርቲ ለማቋቋም ምንም ፍላጎት እንደሌለኝ እያወቀ፣ ለ25 ዓመታት አውሮፓና አሜሪካ ላይ “ጠንቅቄ የማውቀው ወዳጄ ነው” እያለ ሲናገር የነበረ ሰውዬ፣ እንቅስቃሴያችንን ገልብጦ “ፍስሃጽዮን ከወያኔ ጋር ተካክቷል፤ ከሻዕቢያ ጋር ይሰራል” በሚል ስም ማጥፋት ጀመረ:: ግን ማንም የሚያውቀው ሀቅ እኔ ፀረ ሻዕቢያ መሆኔን ነው::

**ቅጽ1ቁጥር43 ቅዳሜ የካቲት 02 /2011ዓ.ም**

# ጋዜጠኛ አበበ ገላው

ወደ ሀገር ቤት ስመጣ ከእኔ በላይ ብዙ ሰዎች ሥጋታቸውን ይገልፃሉ :: እኔ ግን በሥጋት አይደለም የምመጣው፤ ሀገሬ የምገባው በሥጋት ሳይሆን በኩራት ነው:: እኛ የታገልነው በመጀመሪያ ደረጃ ፈርተን ለመደበቅ አይደለም፤ ሕዝባችን በነፃነት ተንፍሶ እንዲኖር የታገልን ሰዎች ነን:: ይሄንን ራሱ ሄዶ ማየት በጣም ወሳኝ ነገር ነው::ስለዚህ እኔ ከስጋቱ በላይ እድሉን ነው የማየው፤ ህዝቡን ወጥቶ ማየቱና መገናኘቱ ትልቅ እድል ነው:: ህዝቡ ደግሞ ያ አፈና ቀርቶለት በየአደባባዩ በጥይት መቆላት፤ ወጣቶች እጅግ በሚዘገንን ኢሰብዓዊ በሆነ መንገድ ይገደሉ ይገረፉ ይታሰሩ ነበር:: ብዙ የፖለቲካ እስረኞች የአካልና የሥነልቦና ጉዳት ሰለባ ሆነዋል፤ ጥፍራቸው እየተነቀለ ሰቆቃ ደርሶባቸዋል:: ይሄ ሁሉ ዛሬ ቀርቶ ያንን ስራ የሚሰሩት ሰዎች ደግሞ ሸሽተውና ተደብቀው አንዳንዶችም ታስረው፤ ከህዝባችን ጋር መገናኘቱ ለእኔ ትልቅ ትርጉም ነው የሚሰጠው::

**ቅጽ1ቁጥር44 ቅዳሜ የካቲት9 2 011ዓ.ም**

# ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና

ጎሰኝነትን ፣ዘረኝነትን፣አድሎአዊነትን፣ኢዴሞክራሲያዊ የሆነ አሰራርን ስተች ነው የኖርኩት:: አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ የመጣው ሁኔታ ከዚህ በተቃራኒ ዘረኞችን፣ኢዴሞክራሲያዊነት፣አፈናን እና ግድያን የሚያወግዝ፣የተሰደዱ ሰዎች የተመለሱበት፣የታሰሩ የተፈቱበት፤ በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ከመቃብር የወጡበት ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው:: ይሄንን ልተች አልችልም::ከዚህ ውጭ ይሄ በደል ደርሶ፣ ይሄ ሁኔታ ተፈጥሯል ብሎ የሚያነሳ ሰው ካለ በዛ ላይ ልንከራከር እንችላለን::ከምንም በላይ ኢትዮጵያን ጫፍና ጫፍ ዘረኞች እየጎተቱ አደጋ ውስጥ ሊጥሏት በሚጣደፉበት በዚህ ወቅት፤ ሥልጣናቸውን የተነጠቁ ሰዎች በተመሳሳይ አቅም መልሶ ለመያዝ በሚወራጩበት ሰዓት፤ ተጨማሪ ችግር፣ ተጨማሪ መከራ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማትረፍ አለብኝ ብዬ አላምንም::ስለዚህ ትናንትም የማደርገው፣ ዛሬም በማደርገው ላይ ልዩነት የለውም::

**ቅጽ1ቁጥር44 ቅዳሜ የካቲት9 2 011ዓ.ም**

# ጋዜጠኛ ወንድማገኝ ጋሹ

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ የመብት ጥሰት ባይኖርም ዜጎች መብታቸውን ለማስከበር በዕውቀትና በእውነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል:: ስለዚህ ደግሞ ወሳኝ ድርሻ የሚጫወተው ሚዲያ ነው:: ሌላው ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው ሲቪክ ማህበራት፤ መንግስታዊ ያልሆኑ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ተቋማት ናቸው:: በተለይ ሚዲያ በሌላው ዓለም እንደ አራተኛ መንግስት የሚቆጠር ጠንካራ ተቋም ነው:: ሚዲያ በመንግስትና በሕዝብ መካከል ሆኖ የህዝብን ጥቅም መሰረት አድርጎ ለሕዝብ የሚሟገት ተቋም ነው:: ሚዲያ ከመምረጥ እና የመመረጥ ሥራዎች ጋር ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባር የሚፈፅም ለዲሞክራሲ ለሰብዓዊ መብት መጠበቅ ወሳኝ ሚና ሊወጣ የሚችል አንድ መሳሪያ ነው:: ስለዚህ ወደፊት በዚህ ላይ አጠናክሬ ለመስራት ነው ያሰብኩት::

**ቅጽ1ቁጥር44 ቅዳሜ የካቲት9 2011ዓ.ም**
















# ጋዜጠኛ አፈወርቅ አግደው

ዜና ሳነብም ሆነ ከሌሎች የሙያ አጋሮቼ ጋር ውይይት ሳደርግ እልህና ቁጭት የሚሰማኝ ምክንያት በውስጤ የተዳፈነ ስሜትን ስላዘልኩ ነው፤ ምርጫ አለ ሲባል ድምፅ ሰጥተው ድምፃቸውን ተሰርቀው ባዶ እጃቸውን ወደ ቤታቸው የገቡት ሰዎች ድምፅ ያንገበግበኛል::የምርጫ 97 ሰቆቃ ከውስጤ አልጠፋም::በ1997 ዓ.ም በአገሪቱ በተካሄደው ምርጫ የድምፅ ኮሮጆ ተሰርቆ ከ197 በላይ ሰዎች እንደሚታደኑ አውሬ ሲገደሉና ሕይወታቸው ሲያልፍ ይቆጨኛል:: የ14 ዓመት ልጅ ሳይቀር ባንክ ሲዘርፍ ነው የተገደለው ተብሎ ሲነገር፤ ኅብረተሰቡ በሙሉ ወደ ወህኒ ቤት ሲታጎር፤ አገራችን ምን ጉድ ፈላባት በሚል ውስጤ ይንገበገባል:: የወገኖቼ ሞት ሰቆቃ መከራ ያመኛል፤ ይሄ ወደ ውስጤ እየገባ ቁጭት ያጭርብኛል፤ ለዚህ ነው እልህና የሚተናነቀኝ::

**ቅጽ1ቁጥር44 ቅዳሜ የካቲት9 2011ዓ.ም**

# ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን

ወደ ኤርትራ ያደረኩት ጉዞ ለሶስት ዓላማዎች ነበር። አንደኛውና ዋናው የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በህወሀት ደህንነቶች ከየመን ታፍኖ መወሰድ የፈጠረብኝ እልህ ነው። ቢያንስ አቶ አንዳርጋቸው በበረሃ የነበረውን ቆይታ እዚያው ካሉ የትግል አጋሮቹ ለመስማትና ዱካውን በአካል ተገኝቶ ለማየት ፈልጌ ነበር። ሁለተኛው በህዝቡ የሚነሳ አንድ ጥያቄ የእኔም ጥያቄ ስለነበር ለእሱ ምላሽ ለማግኘት ነው። ይኸውም በኤርትራ እውን የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ አለ ወይ? በረሃ ወርደናል በሚሉ ሃይሎች የሚነገርው እውነት ነው ወይ የሚለው ጥያቄ በብዛት ይነሳ ነበር። እኔ ውስጥም ይህ ጥያቄ እረፍት ይነሳኝ ነበር። ምላሽ መገኘት አለበት የሚል እምነት ነበረኝ። ሶስተኛው የኤርትራ መንግስት ባለስልጣናትን ቃለመጠይቅ ማድረግ ነው። ስለኢትዮጵያና ኤርትራ ግንኙነት ምን ያስባሉ? ለምን የኢትዮጵያን ሃይሎች መርዳት ፈለጉ? የወደፊቱ የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት በየት አቅጣጫ እንዲጓዝ እቅድ አላቸው? የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን በማቅረብ ምላሽ ለማግኘት ነበር። ሶስቱንም አላማዎቼን ከሞላ ጎደል አሳክቼ የተመለስኩበት ቆይታ ነበር።

**ቅጽ1ቁጥር44 ቅዳሜ የካቲት9 2011ዓ.ም**

# አቶ የሺዋስ አሰፋ

የትግራይ ሕዝብም ሆነ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋይ ስለሆነ ነው እንጂ ፖለቲከኞቹ የሚረጩት መርዝ በጣም ከባድ ነው:: እውነት ለመናገር የትኛው ሕዝብ ነው ያልተበደለ? እኛ እንደውም ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚሰራ አገር አቀፍ ፓርቲ የተቸገርነው የትኛው ነው የበደለው? የአማራ ወኪል ነን የሚሉትም ተበደልን ነው የሚሉት፤ ኦሮሞም ተበደልኩ ባይ ነው፤ ትግሬም ተበደልኩ ነው የሚለው ሁሉም ሙሾ አውራጅ ነው:: ስለዚህ የሰማይ መላዕክት ናቸው ወይስ ሰይጣን ነው በዳዩ እነማን ናቸው? አገዛዙ ከሆነ ሴቱም ወንዱም በጋራ ነው የጮኸው፤ አገዛዙ ከላያችን እንዲነሳ፤ ገዢዎች ጥሩም ሠሩ መጥፎ የጋራ የሁላችንም ጉዳይ ነው የሚሆነው:: አንድ ሕዝብ ላይ “ያነጣጠረ” ብሎ መናገር ተገቢ አይደለም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እጣ ፈንታው አብሮ ነው፤ የሚበደለውም የሚጨቆነውም አብሮ ነው:: ለትግራይ ሕዝብ ዋነኛ ረጋጭና ጨቋኝ ከማንም በላይ ሕወሐት ነው::

**ቅጽ 1 ቁጥር 45 ቅዳሜ የካቲት 16 / 2011 ዓ.ም**

**ግዮን መጽሔት በአንድ ዓመት ውስጥ 45 እትሞች ለንባብ አብቅታለች፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ 119 አንድ መቶ አስራ ዘጠኝ ሰዎችን ቃለ ምልልስ አድርጋለች።**

ቁጥር 1
- አቶ እስክንድር ነጋ
- አቶ አሕመድ ሙስጠፋ
- ዶ/ር ታየ ንጉሴ
- አቶ አንዱአለም አራጌ
- ወ/ሪት ንግስት ይርጋ
- አቶ በቀለ ገርባ
- ወ/ሮ እማዋይሽ ዐለሙ
- አቶ ማሙሸት አማረ
- አቶ ተስፋሚካኤል አበበ
- አቶ አሕመዲን ጀበል
- አቶ ናትናኤል መኮንን
- ወ/ሪት ሴና ሰለሞን
- አቶ ኤልያስ ክፍሌ

ቁጥር 2
- ዶ/ር ብርሃኔ ረዳኢ
- ብርጋዲየር ጄነራል ተፈራ ማሞ (ክፍል 1)
- አርቲስት መርዓዊ ስጦት
- አቶ ዘሪሁን ገብረ እግዚአብሔር

ቁጥር 3
- ወጣት ዮናታን ተስፋዬ
- ብርጋዲየር ጄነራል ተፈራ ማሞ (ክፍል 2)
- አቶ ልደቱ አያሌው
- ዶ/ር መረራ ጉዲና
- አቶ ቡልቻ ደመቅሳ
- አቶ ተመስገን ዘውዴ

ቁጥር 4
- አቶ እስክንድር ነጋ
- አቶ አንዱአለም አራጌ
- አቶ በፍቃዱ ዘሀይሉ

ቁጥር 5
- አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማርያም
- አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት
- አቶ አልባና ሌሊሳ

ቁጥር 6
- ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ
- አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማርያም
- አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት
- አቶ ዘላለም ወርቅአገኘሁ

ቁጥር 7
- ዶ/ር አድማሱ ገበየሁ
- አቶ አግባው ሰጠኝ

ቁጥር 8 (ልዩ እትም)
- አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ
- ብ/ጄነራል ተፈራ ማሞ
- አቶ ስዩም ተሾመ
- ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ
- አቶ ፅጌ ሀብተማርያም /የአንዳርጋቸው አባት/
- ወ/ሮ አይኔ ፅጌ /የአንዳርጋቸው እህት/
- አቶ ብርሃኑ ተክለያሬድ
- አቶ ሸዋቀና አባትነህ
- ወ/ሪት እየሩሳሌም ተስፋው

ቁጥር 9
- ሬ/ፐ መረራ ጉዲና
- ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም
- አቶ ያሬድ ጥበቡ (ከአሜሪካ)
- ወ/ሮ አስቴር ስዩም

ቁጥር 10
- አክቲቪስት ጃዋር መሐመድ (ከአሜሪካ)
- አቶ አንዱአለም አያሌው

ቁጥር 11 (ልዩ እትም)
- ወ/ሪት ሲኔምራ ስዩም (በቦንብ ፍንዳታው የተጎዱ)
- ወ/ሮ አዳነች ዎብሎ (በቦንብ ፍንዳታው የተጎዱ)
- አቶ ያህያ ሂካ (በቦንብ ፍንዳታው የተጎዱ)
- አቶ አብዱራህማን ከድር (በቦንብ ፍንዳታው የተጎዱ)
- አቶ ስዩም ተሾመ
- አቶ ስንታየሁ ቸኮል
- አቶ ክንፈ ሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ)

ቁጥር 12
- ፕ/ር መድኃኔ ታደሰ
- ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
- ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ

ቁጥር 13 (ልዩ እትም)
- ዶ/ር በረከት ብርሃኔ (የኤርትራ ተወላጅ)
- የቀድሞው ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ
- ሠዓሊ ለማ ጉያ
- ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም
- አቶ አስራት አብርሃ
- አቶ አብርሃም ገ/ሊባኖስ

ቁጥር 14
- ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ
- አቶ ደግ አረገ አይናለም
- ወ/ሮ ባጠናሽ ብርሃኑ
- ወ/ሮ ፍቅርተ ከበደ

ቁጥር 15
- ተዋናይ መኮንን ላዕከ
- ካፒቴን መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ

ቁጥር 16
- አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ
- ታጋይ አባ ወርቁ

ቁጥር 17
- አቶ አብዱላሂ ሁሴን
- አቶ ጀማል ኢዲሪዬ
- አቶ ዜና ዳዊት
- ወ/ት ጫልቱ ታከለ

ቁጥር 18
- ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ (ክፍል 1)
- መምህር ማን ያዘዋል አበበ

ቁጥር 19
- ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ (ክፍል 2)
- አምባሳደር ካሳ ከበደ (ክፍል 1)
- ደራሲ ሰዓዳ መሐመድ

ቁጥር 20
- አቶ ቸኮል ጌታሁን
- አምባሳደር ካሳ ከበደ (ክፍል 2)
- አቶ ተስፋዬ አዳል
- ጋዜጠኛ ግሩም ተ/ሃይማኖት

ቁጥር 21
- ወ/ሪት ሜሮን አለማየሁ

ቁጥር 22
- አምባሳደር ካሳ ከበደ (ክፍል 3)

ቁጥር 23
- ወ/ሮ አበበች ከበደ (የቡራዩ ተፈናቃች)
- አቶ ከዝሩ ኬሌሌ (የቡራዩ ተፈናቃዮች)
- ወ/ሮ እቴነሽ (የቡራዩ ተፈናቃዮች)
- ወ/ሮ አይናለም (የቡራዩ ተፈናቃዮች)
- አቶ አባንግ ሜቶ

ቁጥር 24
- ወ/ት አዳነች ገብሬ (የቡራዩ ተፈናቃዮች)
- አቶ አቡሽ አሸናፊ (የቡራዩ ተፈናቃዮች)
- አምባሳደር ካሳ ከበደ (ክፍል 4)
- አቶ አፍሪካ ወጁ

ቁጥር 25
- አቶ የሺዋስ አሰፋ
- አቶ ስዩም ተሾመ
- አፈ መምህር አባ ገብረሥላሴ ጌትነት
- አቶ አለማየሁ ኃይሌ

ቁጥር 26
- ኢ/ር ይልቃል ጌትነት
- ዶ/ር መረራ ጉዲና

ቁጥር 27
- ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ (ክፍል 1)

ቁጥር 28
- ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ (ክፍል 2)
- አቶ ግፋቸው ገ/ስላሴ

ቁጥር 29
- አቶ አዳነ እሸቴ
- ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጥ
- አቶ አበበ ወርቁ (የወልቃይት ኗሪ)
- ወ/ት ፍሬ ይደግ (የወልቃይት ኗሪ)
- ወ/ት አዳኑ ጥላሁን (የወልቃይት ኗሪ)
- ኮፊ ጌታቸው (የወልቃይት ኗሪ)
- ዲ/ን ላሊበላ ሙላው (የወልቃይት ኗሪ)

ቁጥር 30
- ዶ/ር ሰይድ ኑሩ
- አቶ ካሳሁን ሲሳይ (18 ዓመት የታሰረ)
- ወ/ት ሳምራዊት ፍቅሩ

ቁጥር 31
- ኢ/ር ይልቃል ጌትነት
- አቶ ግርማ ሰይፉ
- ጋዜጠኛ መታሰቢያ ሞገስ ቀፀላ
- አቶ የሺዋስ አሰፋ

ቁጥር 32
- አቶ ገብሩ አስራት
- አቶ አብርሃም ዘሪሁን (የተጓዥ ኤክስፖ አዘጋጅ)

ቁጥር 33
- ፕ/ር መድኃኔ ታደሰ

ቁጥር 34
- አቶ ጋአስ አሕመድ

ቁጥር 35
- ዶ/ር አረጋዊ በርሄ (ክፍል 1)
- አቶ ታምሩ ወንድም አገኘሁ (ጠበቃና የሕግ አማካሪ)

ቁጥር 36
- አቶ አምዶም ገ/ስላሴ
- ዶ/ር አረጋዊ (ክፍል 2)

ቁጥር 37
- አቶ ስዩም ተሾመ
- አቶ አልባና ሌሊሳ

ቁጥር 38
- አቶ አንዷለም አራጌ
- ዶ/ር ጫኔ ከበደ
- አቶ ቸኮል ጌታነህ
- አቶ የሺዋስ አሰፋ

ቁጥር 39
-

ቁጥር 40
- ሬ/ፐ/ር አበባው አያሌው
- አቶ ሌንጮ ለታ

ቁጥር 41
- ፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ
- አቶ ነአምን ዘለቀ (ክፍል 1)

ቁጥር 42
- አቶ ነአምን ዘለቀ (ክፍል 2)
- ኢ/ር ግደይ ዘርአፅዮን (ክፍል 1)

ቁጥር 43
- ኢ/ር ግደይ ዘርአፅዮን (ክፍል 2)
- ፕ/ር ፍስሃፅዮን መንግስቱ (ክፍል 1)

ቁጥር 44
- ጋዜጠኛ አበበ ገላው
- ጋዜጠኛ አፈወርቅ አግደው
- ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና
- ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን
- ጋዜጠኛ ወንድማገኝ ጎሹ

ቁጥር 45
- ፕ/ር ፍስሃፅዮን መንግስቱ (ክፍል 2)
- አቶ አንዱአለም አራጌ
- አቶ የሺዋስ አሰፋ
















**ግዮን መጽሔት አንባቢያን ዘንድ መድረስ ከጀመረች ይኸው አንድ ዓመት ሞላት፡፡ በመጽሔታችን በ45 ዕትም ውስጥ ብዛት ያላቸው አምደኞችና ተሳታፊዎች ተጋባዥ ፀሐፊዎች ፅሁፍ አቅርበዋል ለማስታወሻ ይሆን ብለን ስማቸውን በቅደም ተከተል ከዚህ በታች አስቀምጠነዋል፡፡**

1. ተረፈ ወርቁ
2. ዳንኤል ክብረት
3. በፍቃዱ ዘሀይሉ
4. ታምራት መርጊያ
5. አበባው አያሌው (ሬ/ፕ)
6. አቶ ግርማ ሰይፉ
7. በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር
8. ሁሴን ከድር
9. መስፍን ጌታቸው
10. ዓባይነህ ካሴ (ዲ/ን)
11. የሱፍ ጌታቸው
12. አቶ ደረጀ መላኩ
13. ፍቃዱ ልመንህ (ፊልም)
14. አቶ ብሩክ መኮንን
15. ወ/ሪት ብሌን ዮሴፍ
16. መሐመድ እንድሪስ (ዶ/ር)
17. ስዩም ተሾመ
18. ተመስገን ደሳለኝ
19. ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
20. አካለወርቅ መንገሻ (ሬ/ፕ)
21. ኤልያስ ገብሩ
22. ክንፈ ሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ)
23. ፉአዝ መሀመድ
24. አድማሱ ገበየሁ (ዶ/ር ኢ/ር)
25. አቶ መንግስቱ ተገኝ
26. አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ
27. ሼህ ፒያር
28. በፍቃዱ አባይ
29. ዶ/ር ታየ ንጉሴ
30. ዶ/ር አሸናፊ ትርፌ
31. አቡበክር አለሙ
32. ሀይሉ አሰለፍ ገብሬ
33. ተስፋ አልታሰብ(ኢትዮጵያ)
34. ሙሀመድ ሰኢድ
35. አስማማው ሀይሉ
36. አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ
37. አቶ መታሰቢያ መልአከህይወት
38. አብይ ጣሰው
39. አቶ አዱኛ ሙጬ
40. ዳርሰማ ሶሪ
41. ሄኖክ ገለታው
42. ዶ/ር በፍቃዱ በቀለ
43. ዶ/ር ትግስቱ ገብሬ
44. ደረጄ ዘውዴ
45. ዶ/ር ጀማል መሐመድ
46. ኢ/ር ወንድሙ ነጋሽ
47. ታደሰ ወርቁ
48. ዶ/ር አበባየሁ ቶራ
49. አቶ አለሙ ኩየራ
50. ኢ/ር አብዲ አሕመድ
51. አቶ ሀይለማርያም ደንቡ
52. ቢንያም ተስፋዬ
53. አሊ አሕመድ
54. ተሾመ ሽፈራው
55. አቶ ጥላሁን መሸሻ
56. አቶ መለሰ መኮንን
57. አቶ አበባው መሀሪ
58. በምስጋና ዝናቤ
59. አቤል መንግስተ አብ
60. ዮናታን ፍስሃ
61. ዶ/ር ቴዎድሮስ ሀ/ማርያም
62. መሐመድ አወል (ሐሚድ)
63. ክንፈ ሚካኤል አበበ (አበበ ቀስቶ)
64. አንዷለም አራጌ
65. ተመስገን ዘገየ
66. ጌታቸው ወርቁ

# ግዮን መጽሔት አንደኛ ዓመት

## በየሳምንቱ ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።

ቢጨመር ፣ ቢሻሻል የሚሉትን ከወዲሁ ይጠቁሙን!




+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

www.facebooook.com/enqu2013
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu

**ኢ-ሜይል:**
enqu2013@gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com